ቀን Date ጥር 06 2018
ቁጥር Ref.No 3:1/208/18

በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ
ባሉበት

ጉዳዩ፡- <u>የኤክሳይዝ ታክስ የአሰራር ማኑዋሎችን መላክን ይመለከታል</u>፤

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 (እንደተሻሻለው) እና መመሪያ ቁጥር 1071/2017፣ 1072/2017 እና 1079/2017 አፈፃፀሙን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግና በሁሉም ቅ/ፅ/ቤቶች ወጥ የሆነ የኤክሳይዝ ታክስ አሰራር ስርዓት ለመዘርጋት የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት ከታክስ ትራንስፎርሜሽን ፅ/ቤት ጋር በመተባበር የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰር ማኑዋል፣ የኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች ማኑዋል እና የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋሎች ተዘጋጅተዋል።

ስለሆነም እነዚህ ማኑዋሎች ተግባራዊ እንደደረጉና ስራዎች በማኑዋሉ መሰረት እንዲከናወኑ እና የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰር ማኑዋል እና የኤክሳይዝ ታክስ ኢንስፔክሽን ማኑዋል ለታክስ ባለስልጣን መ/ቤቱ አመራር እና ሰራተኞች እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች ማኑዋል ደግሞ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርቱ አምራች ድርጅቶችና አስመጭዎች እንዲያውቁትና እንዲደርሳቸው እንዲደረግ እናሳስባለን።

"ከሠላምታ ጋር"

ዮሴፍ በፈራሙ
የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- **ለሚኒስትር ጽ/ቤት**
- **ለታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ**
- **ለታክስ ስርዓት ዘርፍ**
- **ለታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት**
- **ለተቋማዊ ስጋት ስራ አመራርና ስነ ምግባር ዳይሬክቶሬት**
- **ለገቢ ዘርፍ አገ/አስ/ማሻሻያ ሪፎርም ፅ/ቤት**
- **ለታክስ ትራንስፎርሜሽን ፅ/ቤት**

<u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>

በአባሪ የተዘረዘሩት

ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት

ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት

ለምስራቅ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለምዕራብ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

ለሰሜን ምዕራብ አ/አ/ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ለባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ባህር ዳር/

ለአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /አዳማ/

ለመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /መቐለ/

ለኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/

ለሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሀዋሳ/

ለጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅማ/

ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ድሬዳዋ/

የገቢዎች ሚኒስቴር

የኤክሳይዝ ታክስ ኦፊሰሮች ማኑዋል: የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር እና ግዴታዎች የአሰራር ሰርአት

የታክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት

ከታክስ ማሰታወቅ ዳይሬክቶሬት ጋር በመተባበር የተዘጋጀ

ጥቅምት 2018

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

Contents

ክፍል አንድ፡ ኤክሳይዝ ታክስ በኢትዮጵያ - 10

1.1 መግቢያ 10

1.2 ዋና ዓላማ 10

1.2.1. ዝርዝር ዓላማዎች 10

1.2.2. የማኑዋሉ ወሰን 11

ክፍል ሁለት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ሰጋቶች እና አጠቃላይ የኤክሳይዝ ጉዳዮች 12

2.1. የኤክሳይዝ ታክስ ጽንሰ-ሐሳብ 12

2.2. በአገልግሎቶች ላይ የሚጣል የኤክሳይዝ ታክስ 12

2.3. ጥሬ ዕቃዎች 12

2.4. ከኤክሳይዝ ነፃ መሆን 13

2.5. ቁጥጥር የሚደረግባቸው የኤክሳይዝ ታክስ ሰጋቶች 13

2.6. የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር አፈሰሮች ስልጣን 16

ክፍል ሦስት፣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች 17

3.1. የሀገር ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች 17

3.2. ትርጓሜዎች 17

3.3. ማጠቃለያ 18

4: የሕግ ትንተና እና የአሥራች ግዴታዎች 19

4.1. አጠቃላይ ሐሳብ 19

4.2. በሕጉ መሠረት፡ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የሚውል ዋጋ 19

4.2.1. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ 19

4.2.2. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፡ መቼ ጥቅም ላይ ይውላል? 19

4.2.3. በትክክለኛ የገበያ ዋጋ ላይ የአሥራች ግዴታዎች 20

4.2.4. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት፡ 20

4.2.5. ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የግብር ክፍዮች ግዴታዎች 21

4.2.6. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ 22

4.2.7. የአሥራች ግዴታዎች፡ 22

4.2.8. ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር 23

4.2.9. የዋጋ ዝርዝሩን ስለማቅረብ 24

4.2.10. የአሥራች ግዴታዎች፡ ማጠቃለያ 24

ክፍል አምስት፡ የተወሰነ የኤክሳይዝ ታክስ፡ መጠን እና ክብደት 25

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል 5 ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 25
5 ሀ.1. በመጠን ወይም በክብደት ላይ ብቻ (Specific Method Only) 25
5 ሀ.3. ክብደት ወይም መጠን እና በዋጋ (መቶኛ)ላይ የተመሠረተ ዘዴ ጥምረት 25
5 ሀ.4. ክብደት/ብዛት (ኪሎ ግራም/ሊትር) 26
5 ሀ.5. የአምራች ግዴታዎች፡ ክብደት/ብዛት (ኪሎግራም) 28
5 ሀ.6. መጠን/ይዘት (ለመጠጦች በሊትር እና ለሲጋራ በፍሬ) 29
5 ሀ.7. ትክክለኛው መጠን እና በልዩ ምልክት ላይ ከተቀመጠው ጋር ማነፃፀር 29
5 ሀ.8. ማጠቃለያ 29
ክፍል 5ለ፡ የኤክሳይዝ ታክስ የቁርጥ ስሌት ላይ የሚደረግ ቁጥጥር እና ክትትል 30
5ለ.1. መግቢያ 30
5ለ.2. መግቢያ 30
5ለ.3. በቁርጥ መጠን ስሌት 30
5ለ.4. ማጠቃለያ 31
ክፍል ስድስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ስለሚሰጥ ምዝገባና ፈቃድ (የአዋጁ አንቀፅ 15 እስከ 23 እና የመመሪያው 1071/2017 አን 4 እስከ 11) 32
6.1. **መግቢያ** 32
6.2. ፈቃድ የሚያስፈልገው ለማን ነው? 32
6.3. የታክስ ከፋዩ ግዴታዎች (የአዋጁ አንቀፅ 19) 33
6.4. የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት ፣ የብቃት እና ተገቢነት ፍተሻ 34
6.5. የግብር ከፋዩ ግዴታዎች፡ የፈቃድ ማመልከቻ 35
6.6. የአምራች የማምረቻ ቦታዎች (የመመሪያው አንቀፅ 9) 35
6.7. **በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ** 35
6.8. **የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቅርጽ** 36
6.9. **ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የታክስ ከፋይ ግዴታዎች** 37
6.10. ማጠቃለያ 37
ክፍል ሰባት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር: የአዋጁ አንቀፅ 25 እስከ 29 እና የመመሪያው አንቀጽ 12 እስከ 20 39
ክፍል 7ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 39
7ሀ.1. መግቢያ 39
7ሀ.2. የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ምንድነው? 39
7ሀ.3. ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታ 40

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሬኮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

7ሀ.4. የአንቀጽ 26 ተግባራዊ ተፈፃሚነት 40
7ሀ.5. ቅጣቶች 41
7ሀ.6. ማጠቃለያ 42
ክፍል 7ለ፡ በተፈቀደላቸው አምራች ፋብሪካ ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር 43
7ለ.1. አጠቃላይ እይታ 43
7ለ.2. ቁልፍ ጉዳዮች 43
7ለ.3. አንቀጽ 26፡ የቁጥጥር ሁኔታዎች 43
7ለ.4. ማጠቃለያ 45
ክፍል ስምንት፡ የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካዎች እና የአልኮል መጠጥ አምራቾች የአዋጁ አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 2 46
ክፍል 8ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 46
8ሀ.1. መግቢያ 46
8ሀ.2. የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ስለመጠቀም 46
8ሀ.3. የአልኮል መጠጦች አመራረት፡ የተለያዩ ዘዴዎች 47
8ሀ3.1. ማጣራት 47
8ሀ3.2. ማሻሻል 47
8ሀ3.3. መደባለቅ/ማዋሃድ 47
8ሀ.5. ሕጉ እና ተግባራዊ አፈፃፀሙ 47
8ሀ.6. ማጠቃለያ 48
ክፍል 8ለ፡ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያዎችን አጠቃቀም እና የአልኮል መጠጦችን የምርት ሂደት ቁጥጥር. 49
8ለ.1. በአልኮል የአመራረት ሂደት ላይ የሚደረግ ቁጥጥር 49
8ለ.2. ማጠቃለያ 49
ክፍል ዘጠኝ፡ የምርት ሂደት እና የሂሳብ አያያዝ 51
ክፍል 9ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 51
9ሀ.1. መግቢያ 51
9ሀ.2. የአዲት መከታተያ መዝገብ 51
9ሀ.3. መዝገቦች 51
9ሀ.4. የሕግ አግባብ 52
9ሀ.5. ለታክስ ባለስልጣኑ የሚቀርቡ የፀደቁ ቅጾች 52
9ሀ.6. ወርሃዊ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ 53
9ሀ.7. ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር 53

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዋተ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Document

9ሀ.8. በአምራቹ መያዝ ያለባቸው ነገር ግን ለታክስ ባለስልጣኑ መቅረብ የማይገደዱ መዝገቦች/ሰነዶች..... 53
9ሀ.9. የጥሬ ዕቃዎች መዝገብ..... 54
9ሀ.10. በሀገር ውስጥ የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች..... 54
9ሀ.11. ዕቃዎች የተመረቱበትን ቦታ የሚያሳይ ማስረጃ..... 54
9ሀ.12. የላቦራቶሪ ናሙናዎች..... 55
9ሀ.13. በምርት ሂደት ላይ የሚደርስ የብክነት/ጉድለት/ብልሽት መዝገብ..... 55
9ሀ.14. ዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ ሒሳብ መዝገብ..... 55
9ሀ.15. በተፈቀደለት አምራች እንዲያዙ የሚፈለጉ መዝገቦች ማጠቃለያ..... 56
ክፍል 9ለ፡ የምርት ሂደት ቁጥጥር እና የመዝገብ አያያዝ..... 58
9ለ.1. መግቢያ..... 58
9ለ.2. የመዝገብ አያያዝ ቁጥጥር..... 58
9ለ.3. መዝገቦች እንዴት መያዝ አለባቸው?..... 58
9ለ.4. ማጠቃለያ..... 59
ክፍል ዓሥር፡ ብክነት/ጉድለት/ብልሹቶች..... 60
ክፍል 10ሀ፡ መግቢያ፣ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች..... 60
10ሀ.1. መግቢያ..... 60
10ሀ.2. ሕጉ፡ አንቀጽ 28..... 60
10ሀ.3. ሕጉ፡ ቅጣቶች..... 60
10ሀ.4. የሚፈቀድ የብክነት መጠን አለ?..... 60
10ሀ.5. ሊከሰቱ የሚችሉ የብክነት/ጉድለት አይነቶች..... 61
10ሀ.6. የስቶክ ጉድለቶች..... 61
10ሀ.7. የኢታ ቆጠራ የመመሪያ ቁጥር 1071/2017 አንቀፅ 34 ንውስ አንቀፅ 1 -6..... 62
ክፍል10ለ: ጉድለቶችን/ብክነቶችን መቆጣጠር..... 63
10ለ.1. መግቢያ..... 63
10ለ.2. በሥራ እንቅስቃሴው ከማምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች ከፍል10ለ: ጉድለቶችን/ብክነቶችን መቆጣጠር..... 63
10ለ.3. ማጠቃለያ..... 64
ክፍል አስራ አንድ፡ የሀገር ውስጥ ኤክሳይስ ታክስ አከፋፈል ስርዓትና ተጠያቂነት..... 66
11.1. መግቢያ..... 66
11.2. የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይስ ታክስ የከፍያጊዜ እና ግዴታ..... 66
11.2.1. ሕጉ..... 66

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ሰነዶች አስተዳደር ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

11.3. የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ 67
114. ሕጉ፡ የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ 67
11.5. የኤክሳይስ ታክስ ማሳወቂያ ቅጽ 67
11.6. የኤክሳይስ ታክስ አንዴት ይከፈላል? 68
11A.7. ማጠቃለያ 68
ክፍል ዓሥራ ሁለት፡ ከተፈቀደለት ፋብሪካ የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ወጪ ስለማድረግ ..69
12ሀ: የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 69
12ሀ.1. መግቢያ 69
12ሀ.3. ከሽያጭ ሰነዶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ 70
12ሀ.4. የተረጋገጠ ሽያጭ ሳይኖር ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ 71
12ሀ.5. የኤክሳይስ ታክስ ሳይከፈል ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ 71
12ሀ.6. ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ ለመሆን መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች 72
12ሀ.7. ማጠቃለያ 72
ክፍል 12ለ፡ የዕቃ አወጣጥ ሂደቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ 73
12ለ.1. መግቢያ 73
12ለ.2. የዕቃ አወጣጥ ሂደቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ 73
12ለ.3. ማጠቃለያ 74
ክፍል ዓሥራ ሦስት፡ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች 75
ክፍል 13ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 75
13ሀ.1. መግቢያ 75
13ሀ.2. የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች 75
13ሀ.2.1. ቢራ 75
13ሀ.2.2. ወይን 75
13ሀ.3. የስሪት ሀገር ማረጋገጫ 75
13ሀ.4. የማስረጃ ግምገማ (Evidence of Review) 76
13ለ.1. ወይን እና ቢራ 77
13ለ.2. ማጠቃለያ 77
ክፍል ዓሥራ አራት፡ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች 78
ክፍል 14ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 78
14ሀ.1. መግቢያ 78

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.

14ሀ.2. ሕጉ፡ አንቀጽ 14 78
14ሀ.3. የአምራች ግዴታዎች፡ ተቀናናሽ/ተመላሽ ግብር እንዴት ይከናወናል? 79
14ሀ.4. ማጠቃለያ 79
ክፍል 14ለ፡ ተቀናናሹን መቆጣጠር 80
14ለ.1. መግቢያ 80
14ለ.2. ተቀናናሹን ማረጋገጥ 80
14ለ.3. ልዩነቶች 80
ክፍል ዓሥራ አምስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ (የአዋጁ አንቀፅ 30 እና 31 ንዑስ አንቀፅ 1-7) 81
ክፍል 15ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 81
15ሀ.1. መግቢያ 81
15ሀ.2. የሕጉ አግባብ እና የአምራች ግዴታዎች 81
15ሀ.3. ለተመላሽ የይገባኛል ጥያቄ ብቁ ስለመሆን 82
15ሀ.3.2. ተመላሽ የማግኘት መብት ያለው ሰው 82
15ሀ.3.3 ተመላሽ የሚደረግባቸው ዕቃዎች 83
15ሀ.4. የተመላሽ ሂደት 83
15ሀ4.1. ቅድመ-ማስታወቂያ 83
15ሀ4.2. በተመላሽ ቅጹ ላይ የሚኖሩ መረጃዎች 83
15ሀ.4.3. የማስታወቂያ ጊዜ 84
15ሀ4.4. የተመላሽ ጥያቄ 84
15ሀ4.5. ደጋፊ ሰነዶች 84
15ሀ4.6. የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማረጋገጫ 84
15ሀ.4.7. ዕቃዎቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ማረጋገጫ 85
ክፍል 15ለ፡ የተመላሽ ጥያቄዎችን ማረጋገጥ 85
15ለ.1. መግቢያ 85
15ለ.2. ማረጋገጫ 85
15ለ.3. ትንታኔውን ማካሄድ 86
15ለ.4. የቀረቡ ሰነዶች 86
15ለ.5. የቀረቡት ሰነዶች ላይ የሚደረግ ማረጋገጫ 87
15ለ.6. ስህተቶች 87
15ለ.7. ማጠቃለያ 88
ክፍል ዓሥራ ስድስት፡ ለመጠጥ አገልግሎት የማይውል አልኮል 89
ክፍል 16ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች 89

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

16ሀ.1. መግቢያ 89
16ሀ.2. አልኮልን በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ የሚችለው ማነው? 89
16ሀ.2.1. የአልኮል አምራቾች 89
16ሀ.2.2. የኤቲል አልኮል ለሰመጪዎች 89
16ሀ.3. መዝገቦች 90
16ሀ.4. የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ 90
ክፍል 16ለ፡ ሂደቱን መቆጣጠር 90
16ለ.1. መግቢያ 90
16ለ.2. በማረጋገጫው ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች 90
16ለ.3. ማጠቃለያ 90
ክፍል ዓሥራ ሰባት፡ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች 91
17.1. መግቢያ 91
17.2. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፣ ስለአገልግሎቶች 91
17.3. ማጠቃለያ 92
ክፍል ዓሥራ ስምንት፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸውን ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ምደባዎቻ 93
18.1. መግቢያ 93
18.2. ምደባ 93
18.3. ለምሳሌ፡- ከፍራፍሬ የሚሠሩ መጠጦች እና የፍራፍሬ ጭማቂዎች 94
18.4. ዋጋ 94
ክፍል ዓሥራ ዘጠኝ፡ የኦፊሰሮች ስልጣን እና ማረጋገጫ 95
19.1. መግቢያ 95
19.1. የማረጋገጫ ዓላማ 95
19.2. የማረጋገጫ ሥራ ጥቅሞች 95
19.3. የማረጋገጫ አፈሰር ስልጣን እና አሠራሮች ምሳሌ 96
19.4. ስህተቶች 96
19.5. ማጠቃለያ 96
ክፍል ሃያ፡ የወንጀል ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች 97
20.1. መግቢያ 97
20.2. ቅጣቶች 97
20.3. አጠቃላይ ቅጣት 98

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነድ ማዕከል ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

20.4. ማጠቃለያ 98

አባሪ አንድ፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ትርጓሜ 99

ሀ1. መግቢያ 99

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቁ.1 መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል አንድ፡ ኤክሳይዝ ታክስ በኢትዮጵያ

1.1 መግቢያ

ኤክሳይዝ ታክስ የሚጣለው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚመረቱ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡት የተወሰኑ ምርቶች ፣ ዕቃዎቹ ወይም በኢትጵያ በምሰጥ አገልግሎት ላይ ነው።

የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር እና አሰባሰብ ከውጪ በሚገቡ ላይ የሚጣል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸዉ ዕቃዎች (በጉምሩክ ዲፓርትመንት ቁጥጥር ስር) እና በሀገር ውስጥ በሚመረቱ የኤክሳይዝታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎችና ቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት ላይ የሚጣል የኤክሳይዝ ታክስን መሠረት አድርጎ በሁለት ይከፈላል። ይህ የአሠራር ማኑዋል ከሀገር ውስጥ ኤክሳይዝ ጋር በተገናኘ የቁጥጥር ጽንሰ-ሐሳቦችን እና ሂደቶችን ብቻ የሚገልጽ ነዉ ።

ይህ ማኑዋል የኤክሳይዝ ታክስ ከፋዮችን በመቆጣጠር ረገድ ጥሩ ልምድ የሚሰጥ ሲሆን የገቢዎች ሚኒስቴርን የኤክሳይዝ ታክስ ሕግ ትርጓሜን በኢትዮጵያ የኤክሳይዝ ታክስ ምህዳሩን ለመቆጣጠር ያሉትን የአደጋ ስጋቶች እና ቁልፍ የቁጥጥር ቴክኒኮችን ከሚያብራሩ ምዕራፎች ጋር ያቀርባል::

ተያያዥ የታክስ ሕጎች፡ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ 1186/2012፣ 1287/2015፣ 1007/2016፣1071/2017፣ 1072/2017 እና 1079/2017 ናቸው።

ይህ አዋጅ በመመሪያ ቁጥር 67/2013 በተገለፁት ዝርዝር የሕግ መስፈርቶች የተደገፈ ነው::

መመሪያ ቁጥር 1004/2016 በኢትዮጵያ የታክስ ቴምብሮችን ለማስተዋወቅ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች አስቀምጧል::

ይህ ሰነድ የገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁን እና መመሪያዎቹን ድንጋጌዎች እንዴት እንደሚተረጉም ያብራራል::

ማሳታወሻ፡ በተለያዩ የቁጥጥር ምድቦች ላይ የሚዩተከር ራሱን ችሎ የተዘጋጀ ማኑዋል (የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ማኑዋል) አለ::

1.2 ዋና ዓላማ

ከኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባና ፈቃድ እስከ ሪፖርት ድረስ ላለው ሂደት የተዘረጋውን የቁጥጥር ሥርዓት በመከተል የኤክሳይዝ ታክስ ሕጉን ተፈፃሚ ማድረግ እና የሕግ ተገዢነትን ማረጋገጥ::

በሁሉም የፌዴራል የገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፣ በአዲስ አበባ ከ/አስ/ እና በድሬዳዋ ከ/አስ/ ገቢዎች ቢሮ ላይ ወጥ የሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት::

1.2.1. ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ የአሰራር ማኑዋል የገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሂደቶችን እና የቁጥጥር ሥራዎችን ከእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ ስጋቶች ጋር በማያያዝ የሚያብራራ ሲሆን የተሻሉ የቁጥጥር መርሆዎችን ያቀርባል:

:

በዚህ ሰነድ ውስጥ የተቀመጡትን መመሪያዎች እና ጽንሰ-ሐሳቦች መከተል የሚከተሉትን ነጥቦች የማሳካት ወይም ለማረጋገጥ ይረዳል ::

- በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የሀገር ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርት አምራቾች ጋር በተያያዘ ወጥ እና ፍትሀዊ የሆነ አሰራር እንዲኖር ማድረግ፤ እና

- የታክስ ሕግ ተገዢነትን ለማሻሻል እና ገቢን ለማሳደግ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ባላቸው አምራቾች የሚቀርቡ መረጃዎች ላይ ጥልቅ ትንተና እና ማጣራት በማድረግ የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር ሥርዓቱ ቁጥጥር እየተደረገበት መሆኑን ማረጋገጥ::

በአጠቃላይ ይህ የአሰራር ማኑዋል ከኤክሳይዝ ታክስ የሕግ ተገዢነት ጋር በተያያዘ ቁልፍ የሆኑ ስጋቶች ለመረዳት እንዲችሉ ለገቢዎች ሚኒስቴር የኤክሳይዝ አፈሰሮች ዝርዝር መረጃ ይሰጣል:: የኤክሳይዝ ታክስ ሕግን ተፈፃሚ ለማድረግ እና ለጠቅላላው የአዲት አሠራር የተዘረጋውን የቁጥጥር ሥርዓት በመከተል ከፈቃድ አሰጣጥ ጀምሮ እስከ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ እና ክፍያ ድረስ የታክስ ሕግ ተገዢነትን ለማረጋገጥ ይረዳል::

ይህ ማኑዋል *የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ማኑዋልን* የሚያጠናክር ሲሆን ሁለቱም በአንድነት የኤክሳይዝ ታክስ የሕግ ተገዢነትን በተመለከተ ወጥነት ያለው አካሄድ በሁሉም የፌዴራል ገቢ ሰብሳቢ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ፣ የአዲስ አባባ ከ/አስ/ እና የድሬዳዋ ከ/አስ/ ገቢዎች ቢሮ መተግበሩን ያረጋግጣል::

1.2.2. የማኑዋሉ ወሰን

ይህ ሰነድ በሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አፈሰሮች መተግበር ያለበት ሲሆን ሁሉንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ባህሪያትን በመረዳት የኤክሳይዝ ታክስ ህጎችን ተፈፃሚ ማድረግ::

እንደዚሁም ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ማኑዋል እና ከኤክሳይስ ታክስ ከፋይ ማኑዋል ጋር በጥምረት መነበብ አለበት::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ያሕመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል ሁለት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ስጋቶች እና አጠቃላይ የኤክሳይዝ ጉዳዮች

2.1. የኤክሳይዝ ታክስ ጽንሰ-ሐሳብ

ኤክሳይዝ ታክስ በተወሰኑ ዕቃዎች እና አገልግሎቶ ላይ የሚጣል ታክስ ሲሆን የኤክሳይዝ ሕግ ከኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ጀምሮ እስከ ምርት ሂደት ፣ የምርቶቹን ማከማቻ መጋዘን /እንቅስቃሴ ድረስ የማንኛውንም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው የምርት እንቅስቃሴ ያጠቃልላል::

የሀገር ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በኢትዮጵያ ውስጥ ተመርተው እና በፍጆታነት ጥቅም ላይ በሚውሉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ ነው::

የኤክሳይዝ ታክስ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ምርቶች ላይ የሚከፈል ሲሆን የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስም ከሚከተሉት አንዱን በመጠቀም ይሰላል፡-

- በፋብሪካ ዋጋ ላይ የተመሠረተ የዋጋ ትመና ዘዴ (አብዛኞቹ ምርቶች ለዚህ የግብር ዓይነት ግዴታ አለባቸው)፤ (Advalorem Method)
- በመጠን ወይም በክብደት ላይ የተመሰረተ ዘዴ፤(Specific Method)
- በዋጋ ላይ የተመሠረተ ግምት እና በመጠን ወይም ክብደትን መሰረት ያደረገ የሁለቱም ጥምረት፤ (Both Advalorem and Specific)
- የአንድ የተወሰነ መጠን እና በዋጋ ላይ የተመሰረተ መጠን ከሁለት አንዱን ከፍተኛውን በመውሰድ:: (Taking the higher of the two)

ጥቅም ላይ ከሚውለው ዋጋ በተጨማሪ በአምራቹም ሆነ በታክስ ባለስልጣኑ የቁጥጥር አፈሰር ዘንድ ግልፅነት እና ግንዛቤ መኖሩን ለማረጋገጥ በሕጉ ውስጥ ያሉ የሕግ ትርጓሜዎች አስፈላጊ ናቸው::

2.2. በአገልግሎቶች ላይ የሚጣል የኤክሳይዝ ታክስ

የኤክሳይዝ ታክስ በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ ይጣላል:: ይህ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣለው በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴን በመጠቀም ሲሆን ይህም የተጨማሪ እሴት ታክስ ከመጨመሩ በፊት የደንበኛው የከፍያ ዋጋ ነው:: እነዚህም የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎቶች አይነቶች የሞባይል አገልግሎቶች (ኢንተርኔት፣ የድምፅና የፅሁፍ መልዕክት)፣ የገመድ አልባ ስልክ አገልግሎት፣ የገመድም ሆነ የገመድ አልባ ኢንተርኔት አገልግሎቶች ናቸው::

2.3. ጥሬ ዕቃዎች

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ሂደት የሚመራው በኤክሳይዝ ታክስ ሕግ ነው:: ስለዚህ በምርት ሂደቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችን ብዛት እና ዓይነት የሚያሳዩ መዝገቦች ተደራጅተው መያዝ አለባቸው:: ሁሉም አምራቾች ከእያንዳንዱ የጥሬ ዕቃ ዓይነት የሚያገኙትን ጥራት፣ ምርት፣ ተረፈ ምርት እና የገንዘብ ዋጋ እንዲገነዘቡ ይህ መረጃ ያስፈልጋቸዋል:: ለቢራ እና ለወይን አምራቹ በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች ለተሠሩ የመጨረሻ ምርቶች የቀነሰ የኤክሳይዝ መጠን ሊያስቀምጥ በሚችልበት ሁኔታ የጥሬ ዕቃዎቹን ምንጭ የተመለከተ ማስረጃም መቀመጥ አለበት::

አንዳንድ ጊዜ ጥሬ ዕቃዎችም የኤክሳይዝ ቀረጥ ግዴታ ይጣልባቸዋል:: ለምሳሌ የትምባሆ ቅጠል፣ ስኳር እና በጅምላ የቀረበ የአልኮል ግብዓት (ኢታኖል/ኤቲል) ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል:: እነዚህ ሁሉ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በማምረት ሂደቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን ይህም የመጨረሻውን የኤክሳይዝ ዕቃዎች ምርት ያስገኛል።

በአንዳንድ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ በመጨረሻው ምርት ላይ የመጨረሻው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት ጊዜ ሊቀናነስ ይችላል።

ይሁን እንጂ ይህ በትምባሆ ቅጠል፣ በስኳር እና በጅምላ የሚቀርብ የአልኮል ግብዓት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም። በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች የተሠራው የመጨረሻው ምርት ዋጋ የጥሬ ዕቃዎቹን የኤክሳይዝ ወጪ የሚያካትት መሆኑን ማረጋገጥ አለብን።

2.4. ከኤክሳይዝ ነፃ መሆን

ሁሉም የኤክሳይዝ ዕቃዎች ተመርተው ኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው እና የዕቃ ማስረከቢያ ደረሰኝ ሳይቆረጥ ከፋብሪካው መውጣት የሌለባቸው ሲሆን ነገር ግን በተፈቀደለት መጋዘን ውስጥ ተከማችተው ዕቃዎቹ ከተፈቀደለት መጋዘን እስኪወጡ ድረስ የኤክሳይዝ ታክሱ ሳይከፈልባቸው ሊቆዩ ይችላል።

የኤክሳይዝ ዕቃዎች ከተፈቀደለት መጋዘን ውስጥ ያለምንም የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ሊወጡ የሚችሉት በሚከተሉት ጥቂት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡-

- ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ፤
- ከታክሱ ነፃ ለሆነ ድርጅት ሲቀርብ፤
- በውድመት፤ እና
- የኤክሳይዝ ታክስ ወደማይከፈልበት ምርት የተቀየረ/የተለወጠ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ መሆን አለባቸው፤ **ነገር ግን** ዕቃዎቹ በትክክለኛው መንገድ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ወይም ገቢ እንደተደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ መኖር አለበት። እነዚህ ዕቃዎች ለታለመለት ዓላማ እስካልዋሉ ድረስ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሊሆኑ አይችሉም፤ ነገር ግን በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውስጥ ናቸው፤ ማለትም የዕቃዎቹ የመጨረሻ መዳረሻ/አጠቃቀም እስኪረጋገጥ ድረስ የኤክሳይዝ ታክሱ የታገደነው።

የአዋጁ አንቀጽ 8 የኤክሳይዝ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክሱን እንዲከፍሉ የማይገደዱበትን ሁኔታ ዝርዝር ይደነግጋል፡ ፡

የተፈቀደለት አምራች ዕቃዎቹ በትክክለኛው መንገድ ጥቅም ላይ እንደዋሉ የሚያሳይ ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ ማቅረብ ካልቻለ በሁሉም ዕቃዎች ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል እንዳለበት መረዳት ያስፈልጋል።

2.5. ቁጥጥር የሚደረግባቸው የኤክሳይዝ ታክስ ስጋቶች

የኤክሳይዝ ታክስ ስጋቶች የማንኛውንም የማምረት ሥራ እና እንቅስቃሴውን መደበኛ የአዲት አሠራር ይከተላሉ፡ ፡ የኤክሳይዝ ቁጥጥር አጠቃላይ የምርት ሂደት፣ ሽያጭ እና ከተፈቀደለት መጋዘን የማስወጣት ሂደትን ይቆጣጠራል። ምንም እንኳ ዕቃዎቹ ከመጋዘኖቹ በሚወጡበት ጊዜ ባይሸጡም (የነፃ ስጦታዎች/የንግድ ናሙናዎች ወዘተ.) ሂደትን ጭምር ይቆጣጠራል።

ከዚህ በታች የቀረበው ዝርዝር ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ቁልፍ የኤክሳይዝ ታክስ ስጋቶችን ያመለክታል። በዝርዝሩ ውስጥ የተጠቀሰው እያንዳንዱ ሀሳቦች የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁን ተዛማጅ ክፍሎች በማጣቀስ በሰነዱ ውስጥ በስፋት ተካቷል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ያከመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ስጋቶች ፦-

1. **የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት፡** *የፋብሪካ ዋጋ* የኤክሳይዝ ታክስን በዋጋ ላይ በተመሠረቱ ተመኖች ለማስላት ጥቅም ላይ መዋል ያለበት ሲሆን የተጻፈው የመጠን መግለጫም በአጠቃላይ ለተወሰኑ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌቶች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ዋጋውም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚቀርበው ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር፣ ወርሀዊ ወይም ዓመታዊ የጥሬ ዕቃ እና የምርት ቆጠራ እና የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቁጥጥርና መታየት አለባቸው፡፡

2. **የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባና ፈቃድ፡** በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ፈቃዱም በአምራቹ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል የሚደረግ የስምምነት ውል ነው፡፡ አምራቹ ሊያመርት የሚችላቸው ዕቃዎች ዓይነት እና ዕቃዎቹ የሚመረቱባቸውን ቦታዎች የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች በፈቃዱ ላይ ተዘርዝረው ይቀመጣሉ፡፡

3.

- **የማምረቻ ፋብሪካዎች፡** በእያንዳንዱ ማምረቻ ፋብሪካ ውስጥ ስለሚመረቱት ዕቃዎች እና በሂደቶቹ ውስጥ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ መሣሪያዎች በግልፅ በመገንዘብ አምራቹ የሚጠቀምባቸውን ሁሉንም ፋብሪካ የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች በፈቃዱ ላይ መኖር አለባቸው፡፡ ዕቃዎች የት እንደሚከማቹ እና የማምረት ሥራው የት እንደሚካሄድ በግልፅ የሚያመለክት መግለጫ ያለው ማምረቻ ህንፃውን (site plan) የሚያሳይ መቅረብ አለበት፡፡
- **የማምረት ሂደት (ሂደቶች)፡** በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጥሬ ዕቃዎች እና ትክክለኛውን ሂደት መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የተገለፀው ኤክሳይዝ ከእያንዳንዱ የተሸጠው ዕቃ ብዛት ዋጋ አንፃር ሲተነተን ከተመረቱት እና ለፍጆታ ከቀረቡት መጠኖች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለመገምገም ይረዳናል፡፡
- **ጥሬ ዕቃን ለሚጠበቀው የምርት ግምት ማዋል(Raw materials to Expected yield estimated)፡** እያንዳንዱ አምራች በሚመረተው የምርት ዓይነት፣ በመሣሪያዎች እና ጥቅም ላይ በሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች ጥራት ምክንያት በመጠኑ እንደሚለያይ ልብ ማለት ይገባል፡፡ ስለሆነም እንደ አጠቃላይ የማረጋገጫው አንዱ ክፍል ተደርጎ *ትክክለኛው* ምርት በእያንዳንዱ የፋብሪካ ጉብኝት ወቅት ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡
- **የማሸግ ሂደት (Packaging Process)፡** ማንኛውንም የጥሬ ዕቃ/የምርት ጉድለት ቆጥሮ ለማስላት የማሸግ ሂደቱን መረዳት፡፡

4. **የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካዎች እና የአልኮል መጠጥ አምራቾች፡** የኤክሳይዝ ታክስ ህግ የአልኮል ማጣሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

መሣሪያዎችን ስለመጠቀም እና የአልኮል መጠጦችን ስለማምረት በተናጠል ያስቀምጣል፡፡ የአልኮል ማጣሪያ መሳሪያዎችን ከተፈቀደላቸው የአልኮል አምራቾች ውጭ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት አንዱ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገባው ስጋት ነው፡፡

5. **የመዝገብ አያያዝ፡** ጥሬ ዕቃውን ከመቀበል ጀምሮ እስከ ማሸግ፣ ማከማቸት እና ስርጭት ድረስ ያለውን ሙሉውን የአዲት ሂደት የሚያሳዩ መዝገቦች መኖር/መያዝ አለባቸው፡፡ መዝገቦቹ መቅረብ ያለባቸውን በታክስ ባለስልጣኑ በኩል በፀደቁ ቅጾች (ወርሃዊ የዕቃ/ቆጠራ ዝርዝር ቅጽ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ እና የዋጋ ዝርዝር) እና በአዋጁ ስር ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የማረጋገጫ ሥራዎች መያዝ እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን ነገር ግን ለተቀሙ መቅረብ የማይጠበቅባቸው የውስጥ ለውስጥ መረካከቢያ መዝገቦች (ጥሬ ዕቃዎችን የመቀበል እና የመጠቀም፣ ዕለታዊ የኤክሳይዝ ሂሳብ፣ የመላኪያ ማስታወሻዎች እና ደረሰኞችን) ያካትታሉ፡፡ እነዚህ ከሌሉ ቅጣቶች መፈፀም ያለባቸው ሲሆን መዝገቦቹ እንዲተገበሩም ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

6. **በምርት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ጉድለት፡** የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በፋብሪካው ውስጥ እንዳሉ በጉድለት/ብልሽት ካጋጠመ የኤክሳይዝ ታክሱ ሊካካስ ይችላል፤ ነገር ግንይህ የሚሆነው ጉዳዩ ተገቢውን ማጣሪያ ተደርጎበት እና በማስረጃ ሲረጋገጥ ተብራርቶ ሲገለጽ ብቻ ነው፡፡

7. **የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል ግዴታዎች፡** መከፈል ያለበት የኤክሳይዝ ታክስ ከተፈቀደለት የማምረቻ/የማካማቻ ቦታ ለሚወጡ ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች መቆጠር አለበት፡፡ ዕለታዊ ሂሳቦችም መያዝ ያለባቸው ሲሆን እነዚህ መዝገቦች በሚቀጥለው ወር መጨረሻ በአንድ ወርሃዊ የታክስ ማስታወቂያ ውስጥ መቅረብ አለባቸው፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ በባንክ ወይም በተመሳሳይ የኤሌክትሮኒክ ባንክ ዘዴ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

8. **የኤክሳይዝ ዕቃዎችን ከተፈቀደ ቦታ ወጪ ማድረግ፡** ከተፈቀደ ቦታ የሚወጡ ዕቃዎች በሙሉ በማስረከቢያ ሰነድ ወጪ መደረግ አለባቸው፤ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሽያጭ ከተገቢው የማስረከቢያ ሰነድ ጋር የተያያዘ ደረሰኝ መሰጠት አለበት፡፡

9. **የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች፡** ለቢራ እና ወይን የኤክሳይዝ ታክስ መጠኑ በምርት ሂደት ውስጥ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች አጠቃቀም ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ የቀነሰ መጠንን የሚያሳይ ማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ መታየት ያለበት ሲሆን የጥሬ ዕቃዎቹን ምንጭ የሚያሳይ ማስረጃም በሚቀጥለው የማጣሪያ ጉብኝት ላይ ምርመራ ሊደረግበት ይገባል፡፡

10. **የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች፡** አንዳንድ የኤክሳይዝ ታክስ ሚከፈልባቸው ዕቃዎች

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ ሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት እንደ ጥሬ ዕቃ ያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ በጅምላ የቀረበ የኢታኖል/ኤቲል አልኮል ፈቃድ ከተሰጣቸው ቦታዎች ሲወጣ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በዚህም መሠረት በጅምላ የቀረበ ኢታኖል (የአልኮል ጥንካሬው 80% እና ከዚያ በላይ የሆነ) ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ወደ ሀገር ውስጥ የገባበትን ወይም የፋብሪካው ዋጋ 10% ነው፡፡ ይህ በአልኮል መጠጡ ላይ ተፈጻሚ ከሆነ ከተፈቀደለት መጋዘን ሲወጣ የመጨረሻው ምርት የፋብሪካ ዋጋ 80% ተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ ይኖራል፡፡ አንድ አምራች በኤቲል አልኮል፣ በትምባሆ ቅጠል እና በስኳር ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ማቀናነስ አይችልም፡፡ (ነገር ግን አንድ የልብስ አምራች ቀረጥ ተከፍሎባቸው ከዚያም ወደ ልብስ ማምረቻ ፋብሪካ ገብተው የተሠሩ እንደ ጨርቃ ጨርቅ የመሳሰሉ ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎችን ሊያቀናንስ ይችላል)፡፡

11. **የተመላሽ ሂደት፡** የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው በጥቂት ሁኔታዎች ብቻ ሲሆን መደበኛ ሂደትን መከተል እና ተመላሽ ገንዘብ የጠየቀው አመልካች ተመላሹ ትክክለኛ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የተመላሽ ሂደትን የተመለከቱ ጉዳዮች ከዚህ በታች በክፍል 16 በተሟላ መልክ ተብራርተዋል፡፡

12. **ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል አልኮል፡** አልኮል ለመጠጥነት የሚውል አልኮልን ከማምረት ውጪ ለበርካታ የምርት ሂደቶች (ለፋርማሲዩቲካል/የኢንዱስትሪ ምርት ሂደቶች) ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡ : መመሪያው አልኮሆል በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል የሚደረግበትን ሁኔታ ዝርዝር ማብራሪያ ያቀርባል፡፡

2.6. የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር አፊሰሮች ስልጣን

አዋጁ አንድ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር አፊሰር ፈቃድ የተሰጣቸውን (ወይም ፈቃድ ያልተሰጣቸውን) የማምረቻ/ማከማቻ ቦታዎችን በማንኛውም ጊዜ ለመፈተሽ እና አዲት ለማድረግ የመጎብኘት ስልጣን እንዳለው ይደነግጋል፡፡

ግጭቶች እንዳይፈጠሩ እና አምራቹም ስለጉብኝቱ እንዲያውቅ እንደነዚህ ያሉ ጉብኝቶች ብዙውን ጊዜ ከአምራቹ ጋር በመሆን ይታቀዳሉ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች መረጃ ወይም የመረጃ ትንተና ሆነ ተብሎ ዝቅ ተደርጎ የቀረበ የታክስ ማስታወቂያ እንዳለ በሚያሳይበት ጊዜ ያልተነገረ ጉብኝት ሊታቀድ ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ሦስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች

3.1. የሀገር ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 እና አዋጅ ቁጥር 1287/2015 (እንደተሻሻለው) ሠንጠረዥ አንድ በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዝርዝር ይገልፃል::

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዘርፎች:-

- የምግብ ምርት (ለምግብነት የሚውሉ የአትክልት ዘይቶች፣ ማርጋሪን፣ ስኳር እና ሽሮፕ (syrup)፣ ጨው፣ ቸኮሌት እና እና ጣፋጮች፣ ማስቲካ)፤
- መጠጦች፡ አልኮል ያላቸውም ሆነ የሌላቸው (በዱቄት መልክ የተዘጋጁ ለስላሳ መጠጦችን ጨምሮ)፤
- በጅምላ የቀረበ አልኮል፡ ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው ንፁህ አልኮል፤
- የትምባሆ ቅጠል እና የትምባሆ ምርቶች፤
- የማዕድን ዘይቶች፤
- ሽቶዎች እና መዋቢያዎች (cosmetics)፤
- ርችቶች፤
- የፕላስቲክ ከረጢቶች (ፌስታሎች)
- ጎማዎች፤
- ጨርቃ ጨርቅ እና የጨርቃጨርቅ ምርቶች፤
- ሰው ሠራሽ አበባዎች፤
- ዊግ፣ ሰው ሠራሽ ጢም፣ ቅንድብ፣ ሽፋሽፍት፤
- አስቤስቶስ፤
- ዕንቁዎች እና ሌሎች ጌጣጌጦች፤
- ተሽከርካሪዎች እና የሞተር ብስክሌቶች፤
- የቁማር ማሽኖች፣ የመጫወቻ ካርዶች እና የካርኒቫል/የበዓል መዝናኛ፤
- የትምባሆ ማጨሻ ቧንቧዎች እና ሲጋራ/የሲጋራ መጠቅለያ ወረቀቶች፤
- የቴሌኮም አገልግሎቶች፡ ይህ ማኑዋል በተዘጋጀበት ጊዜ (ግንቦት 2017) ፈቃድ ያላቸው ሁለት የኤክሳይዝ ታክስ አገልግሎት አቅራቢዎች ይገኛሉ፤ ኢትዮቴሌኮም እና ሳፋሪኮም፡፡

3.2. ትርጓሜዎች

እያንዳንዱ ምርት ላይ የሚጣለውን የታክስ ግዴታ ለመረዳት የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ትርጓሜዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው:: በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ሠንጠረዥ አንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ ትርጉሞች በተጣጣመ የሥርዓት ታሪፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋሉት የሸቀጦች ኮዶች ጋር የተገናኙ ሲሆን ምርቶችን ከውጭ ሀገር ከማስገባት/ጉምሩክ ቀረጥ አንፃር ይገልፃሉ:: ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ የተቀመጡት በተለይ በሀገር ውስጥ ምርቶች ነው::

የኤክሳይስ ታክስ ምጣኔዎች በሚተገበሩበት ጊዜ፣ በእያንዳንዱ የተፈቀደ የማምረቻ/ማከማቻ ቦታ የሚመረቱ ሁሉም ተያያዥ ምርቶች ከትክክለኛው የምርት ኮድ አንፃር መተንተን እና የእያንዳንዱን ምርት ብራንድ ዋጋ በትክክል ተረድቶ መተግበር አስፈላጊ ነው:: የምርቶች ኮዶች እና ትርጓሜዎች አንዳንድ ጊዜ ግልፅ አይደሉም፤ እናም የትኛው የኤክሳይዝ ታክስ ምጣኔ መተግበር እንዳለበት ለማረጋገጥ ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል::

ለምሳሌ ኮድ 2203.0000 "ሁሉንም የቢራ ዓይነቶች፣ የሚፈሉ መጠጦች (ሳይደር፣ ፔሪ፣ ሜድ፣ ኦፔክ ቢራ) እና ከሚፈሉ መጠጦች ጋር የተደባለቁ አልኮል ያልሆኑ መጠጦች እንዲሁም ስታውት እና ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ በዱቄት መልክ የተዘጋጀ ቢራ፣ ከ7% የማይበልጥ የአልኮል ይዘት

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ያለው ለመጠጣት ዝግጁ የሆነን ቢራ" ያጠቃልላል::

ነገር ግን ከቢራ እና ወይን ውጪ ያሉ የሚፈሉ መጠጦች (እንደ ሳይደር እና ፔሪ ያሉ) ተስማሚ በሆነው ታሪፍ ኮድ 2206 ስር ስለሚወድቁ ይህ በተለየ መልክ ለኢትዮጵያ ገበያ የተቀመጠ ትርጉም ነው::

አምራቾች በራስ ታክስ ስሌት ለኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ የሚጠቀሙበት የኤክሳይዝ ታክስ መጠን በሚገመገምበት ጊዜ የሚመረቱትን ምርቶች ምንነት እና የአመራረት ሂደቱን በተመለከተ ግልፅ ግንዛቤ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ማናቸውም ቢራ ላይ የተጨመሩ የአልኮል መጠጦች ቢራውን የአልኮል መጠጦቹ የግብር ተመን የሚከፈልበት እንዲሆን ያደርጉታል:: ከተሸከርካሪዎች በስተቀር የሁሉም ምርቶች ትርጓሜዎች ዝርዝር በአባሪ አንድ ላይ ይገኛል::

3.3. ማጠቃለያ

አብዛኞቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ሰንጠረዥ አንድ ላይ ካለው አጠቃላይ የምርት ኮድ እና ለምርቱ ከተሰጠ ትርጉም በቀላሉ ሊታወቁ ይችላሉ::

ይሁን እንጂ አንድ ዘርፍ ብዙ ምጣኔዎች (ለምሳሌ እንደ አልኮል ያሉ) ሲኖሩት ትክክለኛው መጠን ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በአመራረት ሂደቱ ላይ የሚደረግ ጥብቅ ትንተና እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በምርቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉት ጥሬ ዕቃዎች ምንጭ ያስፈልጋል::

አባሪ አንድ የኤክሳይዝ ታክስ ስለሚከፈልባቸው ዕቃዎች ትርጓሜዎች ተጨማሪ መረጃዎችን ይሰጣል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል አራት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት፡ በዋጋ ላይ የተመሠረተ ስሌት

4: የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

4.1. አጠቃላይ ሐሳብ

በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው ከሚከተሉት ዘዴዎች አንዱን በመጠቀም ነው፡-

- በዋጋ(መቶኛ) ላይ የተመሠረተ ዘዴ፤
- የዕቃውን መጠንና ክብደት መሰረት ያደረገ ዘዴ፤
- የዋጋ ላይ መሠረት እና የዕቃውን መጠንና ክብደት መሰረት ያደረገ ጥምረት፤ ወይም
- በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴ፤ እና የዕቃውን መጠንና ክብደት ከሁለቱ አብላጫውን በመውሰድ::

በአገልግሎቶች (የቴሌኮሙኒኬሽን) ላይ የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በዋጋ ላይ የተመሠረተ መቶኛ ዘዴን በመጠቀም ነው::

ይህ ክፍል የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ከተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች/ፋብሪካዎች ሲወጡ የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ መዋል ያለበትን ዋጋ ይዳስሳል - ይህም በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴ (an ad valorem method) ነው::

4.2. በሕጉ መሠረት፡ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የሚውል ዋጋ

የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረትን የሚዳስሱ የአዋጁ ተዛማጅ ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፡-

4.2.1. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

የአዋጁ አንቀጽ 3፡ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

1/ በአንድ የተወሰነ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው የሚባለው በዚያን ጊዜ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተካሄደ የጅምላ ግብይት ዕቃው ሲያስገኝ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀው ዋጋ ነው::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በአንድ የተወሰነ ጊዜ የኤክሳዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማወቅ ያልተቻለ እንደሆነ በፌዴራል የታክስ አሰተዳደር አዋጅ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት የዕቃው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይወሰናል::

4.2.2. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፡ መቼ ጥቅም ላይ ይውላል?

የገቢዎች ሚኒስቴር በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ትክክለኛ የገበያ ዋጋን ሊያስቀምጥ ይችላል፡-

- ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈል ወደ ገበያ በቀረቡ ዕቃዎች ላይ፤
- የተለየ የምርት ስያሜያቸው በወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ሳይካተት ወደ ገበያ በቀረቡ ዕቃዎች ላይ፤
- በአምራቹ የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ጥሬ ዕቃዎች፤

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ማዕከል
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation Center

በተፈቀደለት አምራች ተመርተው ለራሱ የምርት ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎችን በተመለከተ እያንዳንዱ ጥሬ ዕቃ እና ዋጋ ከተጠናቀቁ ዕቃዎች የዋጋ ዝርዝር ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ መቅረብ አለበት::

4.2.3. በትክክለኛ የገበያ ዋጋ ላይ የአምራች ግዴታዎች

"ትክክለኛ የገበያ ዋጋ" የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት የሚያገለግል ዋጋ ነው:: የተፈቀደላቸው አምራቾች በየወሩ ለፍጆታ ለሚቀርቡ እያንዳንዳቸው የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች በአንድ የተወሰነ ዋጋ ላይ ተመስርተው የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያቸውን መክፈል አለባቸው: : ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለማናቸውም ዕቃዎች ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በኤክሳይዝ ታክስ አፈሰር መሰጠት ያለበት ሆኖ ከተገኘ አምራቹ የታክስ ግዴታውን ሳይወጣ ቀርቷል ማለት ነው::

ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ኩባንያው በወርሃዊ የዋጋ ዝርዝሩ ላይ ዕቃዎቹ ወጪ ተደርገው በተገኙበት ወይም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ የተተገበረበትን የሽያጭ ቀን የሚያሳይ ደረሰኝ ባለበት ወር ውስጥ የሚያቀርበው ዋጋ ነው::

ተገቢ የሆኑትን ዕቃዎች አጠቃሎ የያዘ ምንም ዓይነት ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ካልቀረበ (ለምሳሌ:- በሕገ-ወጥ መንገድ የሚሠራ ፈቃድ የሌለው አምራች ከሆነ ወይም ፈቃድ ያለው አምራች ሆኖ የሚጠበቅበትን የዋጋ ዝርዝር ካላቀረበ)፣ የኤክሳይዝ ታክሱን ለማስላት የሚውለው ዋጋ የተመሳሳይ ዕቃዎች "መደበኛ" ዋጋ ሲሆን ይህም የምርቱን ጥራት፣ ማሸጊያውን እና ገበያውን ታሳቢ በማድረግ በሌላ ኩባንያ ለተመሳሳይ ዕቃዎች የቀረበን ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር በመጠቀም ይሆናል::

ዋናው ቁልፍ ጉዳይ አምራቹ ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ማቅረብ እና ለእያንዳንዱ ወር በእያንዳንዱ የምርት ስም እና የማሸጊያ መጠን ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋን ማስተካከል ያለበት መሆኑ ነው:: ይህም የአምራቹን የታክስ ሕግ ተገዢነትን እና የሚኒስቴር መ/ቤቱን የቁጥጥር ሥራ በእጅጉ ቀላል እንዲሆን ያደርገዋል (በተለይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መከፈል ያለባቸው ትክክለኛ ተመላሽ ገንዘቦች ተገምግመው በሚሰሉበት ጊዜ)::

4.2.4. የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት:

የአዋጁ አንቀጽ 9 እንደሚገልፀው:-

1/ *የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በሠንጠረዥ አንድ የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መሠረት የዕቃዎቹ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ በሚሆንበት ጊዜ ነው::*

2/ *ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚከተሉት ድምር ይሆናል:-*

   ሀ) *በዕቃው ላይ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚሰላው የዕቃው ዋጋ፤ እና*

   ለ) *በጉምሩክ አዋጅ መሠረት በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ::*

3/ *በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ*

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ማስከፈያ ዋጋ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

ሀ) በዕቃ አቅርቦት ላይ የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

ለ) የኤክሳይዝ ቴምብር (ካለ) ወጪ፣ ወይም

ሐ) የተመላሽ የዕቃ መያዣያዎችን ወጪ።

4/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች ዋጋ እንደሚከተለው ይሆናል

ሀ) የተመዘገበ ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተደረገ ግብይት ከሆነ ተከፋይ የአገልግሎቱ ዋጋ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ

ለ) በሌላ ማንኛውም ሁኔታ የአገልግሎቱ ትክክለኛ ዋጋ

4.2.5. ለኤክሳይዝ ታክስ ሰሌት መሠረት የግብር ከፋዮች ግዴታዎች

ይህ ክፍል የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት በኤክሳይዝ ታክስ ደረሰኝ ውስጥ ካለው አጠቃላይ የዋጋ መሠረት ጋር ስለመጣጣሙ ያብራራል። የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክሱን በሚያሰላበት ጊዜ ደረሰኙ የሚከተሉትን ማሳየት አለበት፡-

- የዕቃዎቹን ዋጋ፤
- በወርሃዊ የማረጋገጫ ዝርዝር ላይ የቀረበውን ዋጋ በመጠቀም በዕቃዎቹ ላይ ያለውን ወይም ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን፤
- እንዲሁም በዕቃዎቹ የመሸጫ ዋጋ ላይ ያለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሳይዝ ታክስ ስሌቶችን ያካተታል። በተጨማሪም በደረሰኙ ላይ መካተት ከሚኖርባቸው ነገሮች ቀን፣ ዕቃው የወጣበት ቀን ፣ መጠን እና ዋጋ ሊታይ ይገባል።

አምራቹ በዕቃዎቹ ሽያጭ ላይ የዋጋ ቅናሽ ያደረገ እንደሆነ ቅናሽ የተደረገው ዋጋ ከኤክሳይዝ ታክስ የማስከፈያ ዋጋው ተለይቶ መዘርዘር አለበት። የኤክሳይዝ ታክሱም በአምራቹ ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ላይ በቀረበው ወይም አስቀድሞ ባቀረበው ዋጋ ላይ መሰላት አለበት።

ለምሳሌ፡- አምራቹ አስቀድሞ ባሳወቀው ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር ላይ የአንድ ሳጥን ቢራ የመሸጫ ዋጋ 50 ብር ብሎ ቢሰላውቅ እና ምርቱ የተሸጠው የ10 ሣጥን ቢራ ሽያጭ ተከናወነ አንዱ ሣጥን ባለ 33cl የሆኑ 12 ጠርሙሶችን የሚይዝ ዋሊያ ቢራ ነው።

በአምራቹ በኩል በአንድ ሣጥን ለገቢዎች ባለስልጣን ገቢ የሚደረገው ዋጋ 40 ብር ነው -የ10 ሣጥን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን 400 ብር ብሎ ቢያሳውቅ። የኤክሳይዝ ታክስ ስሌቱ መሆኑ ያለበት ቀድሞ ባሳወቀው የአንድ ሳጥን ዋጋ 50 ብር በመሆኑ የ10 ሳጥን ዋጋ 500 ብር በመሆኑ ልዩነቱ 100 ብር መከፈል አለበት።

በሕጉ መሠረት የሚጠየቀው ደረሰኝ ቴምፕሌት በገቢዎች ሚ/ር በታተመው ሰነድ ውስጥ በማመሳከሪያ ቁጥር፡ 30/190/12 የተገለፀ ሲሆን፣ የሚከተለውን ይመስላል፡-

ተ.ቁ.	የዕቃው ዓይነት	መለኪያ	ብዛት/ክብደት	የፋብሪካ መሸጫ የአንዱ ዋጋ	የፋብሪካ መሸጫ ጠቅላላ ዋጋ

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ኤክሳይዝ%	
ኤክሳይዝ%	
ኤክሳይዝ%	
ድምር	
የአገልግሎት ክፍያ	
ድምር	
ተ.እ.ታ 15%	
ተ.እ.ታን ጨምሮ ጠቅላላ የመሸጫ ዋጋ	

በተጨማሪም ልዩ ማመሳከሪያ ቁጥር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ዕቃውን የሚሸጠው ሰው እና ዕቃውን የሚገዛው ደንበኛ ስም እና አድራሻ እንዲሁም ዕቃው የሚረከብበትን ቦታ አድራሻ ማካተት አለበት::

ከተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም ፋብሪካ ከሚወጡ ዕቃዎች ጋር ከተገናኙ ማናቸውም ደረሰኞች ጋር ለማስታረቅ የማስረከቢያ ሰነድ (Delivery Note) መኖር እንዳለበት ማስታወስ ያስፈልጋል::

4.2.6. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ

በአንቀጽ 11፡ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋን በተመለከተ እንደተገለፀው፡-

1/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ነው የሚባለው፡-

ሀ) አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት ለገዥው የሆነ እንደሆነ፣ ገዥው የከፈለው ዋጋ፤ ወይም

ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃው ከአምራቹ ፋብሪካ በወጣበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ::

2/ በፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በግብይቱ ደረሰኝ ላይ ተለይቶ መታየት አለበት::

4.2.7. የአምራች ግዴታዎች፡

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ

አንቀጽ 11 በተለያዩ የሽያጭ ዓይነቶች ውስጥ የኤክሳዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ መዋል ያለበትን ዋጋ ይገልፃል::

"ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ሽያጭ" ከአንድ ኩባንያ ወደ ሌላ ኩባንያ የሚደረግ ሽያጭ ሲሆን ይህም ከሚሸጠው አካል ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: በመሠረታዊ አገላለፅ ለ"ሦስተኛ ወገን" ሽያጭ ሲከናወን ነው::

አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ከአምራቹ ግንኙነት የሌላቸው ላልሆኑ አካላት የሚደረጉ ሽያጮችን አጠቃሎ ይይዛል:: ይህም ማለት ከአምራቹ ጋር ግንኙነት ላለው ኩባንያ የሚከናወን ሽያጭ ነው:: ለምሳሌ ኩባንያው የተለያዩ ክፍሎች ሲኖሩት አንደኛው አካል አምራች ኩባንያ ሲሆን ይችላል፤ ነገር ግን የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች በጅምላ ለማከፋፈል የተቋቋመ የተለየ አካል ይኖረዋል::

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በእነዚህ አጋጣሚዎች የቁጥጥር ሥርዓት ከሌለ በስተቀር የኤክሳይዝ ታክስን እና የተጨማሪ እሴት ታክስን ለማስቀረት የሽያጭ ዋጋን (በኩባንያዎች መካከል የሚደረግ ሽያጭ ዋጋ/ICSP በመባል የሚታወቀውን) ሆን ተብሎ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግን ሊያስከትል ይችላል::

እነዚህ ሽያጮች በአንቀጽ 3 በተገለፁት የ"ትክክለኛ የገበያ ዋጋ" ሕጎች ስር የተቀመጡ ናቸው:: በተለምዶ በከፍተኛ የአምራች ዘርፍ ውስጥ ያሉ ኩባንያዎች ይህ ዓይነቱን የንግድ መዋቅር የመዘርጋት እና የማንቀሳቀስ አቅም ያላቸው ስለሚሆኑ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ትንተና በሚካሄድበት ጊዜ የሽያጩ ዋጋ የዕቃዎቹ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ስለመሆኑ ማጣራት የተደረገበት መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ለዚህ ዓላማ ሲባል ትክክለኛ ገበያ ዋጋ በወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ውስጥ የተመደበው ዋጋ ሲሆን ይህም ለእያንዳንዱ ወር የእያንዳንዱ ምርት እና የአንድ ነጠላ መጠን ሽያጭ ጥቅም ላይ መዋል አለበት::

ስለሆነም አንድ ከፍተኛ ኩባንያ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች በተመሳሳይ ንግድ ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ ድርጅቶች ሲሸጥ ማለትም የቢራ አምራች ድርጅት ለቢራ አከፋፋይ ድርጅት ሲሸጥ የኤክሳይዝ ታክሱን ለማስላት የሚውለው ዋጋ ለሦስተኛ ወገን ሲሸጥ ከነበረበት ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት:: በዚህም መሠረት በእነዚህ ግብይቶች ላይ ያለውን የኤክሳይዝ ታክስ ለማስላት በወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ቅጽ ላይ ያቀረቡትን ዋጋ መጠቀም አለባቸው::በተመሳሳይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ከማምረቻ ቅጥር ግቢ ወደ ማከፋፈያ መጋዘን እየተጓጓዙ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ የወርሃዊ ዋጋን በመጠቀም መሰላት አለበት::

ስለሆነም የኤክሳይዝ ታክሱን ለማስላት ጥቅም ላይ ከዋለው ዋጋ ጋር በተያያዘ ዋናው የአምራቾች ግዴታ የዕቃው አወጣጥ ዓይነት ምንም ይሁን ምን ለእያንዳንዱ ብራንድ እና የማሸጊያ መጠን ተመሳሳይ ዋጋ መጠቀም አለባቸው::

በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የሚጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ምንም ዓይነት ሽያጭ ባልተከናወነበት ወር ውስጥ ሆኖ ዋጋው ከተመዘገበ፣ ዕቃው በቀጣዩ ወር ከተሸጠ፣ በዋጋ ዝርዝሩ ውስጥ ያለው ዋጋ ከፍ ሊል በሚችልበት ጊዜ፣ የቀረጥ ማስከፈያ ነጥቡ የፋብሪካ ዋጋ እንደመሆኑ መጠን፣ ያለምንም ሽያጭ በዕቃው መውጣት ላይ በተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ እና ዕቃው በሚሸጥበት ጊዜ የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ልዩነት በመዝገብ መያዝ አለበት::

4.2.8. ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር

የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላበትን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ እና ምክንያታዊ ዋጋ ማስቀመጥ ውስብስብ ሊሆን ይችላል::

የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ቋሚ ዋጋ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ መመሪያ ቁጥር 1071/2017 አንቀጽ 32 ሁሉም አምራቾች ለእያንዳንዱ የምርት ዓይነት እና ነጠላ መጠን የዋጋ ዝርዝር እንዲያቀርቡ ያስገድዳል::

የዕቃውን መጠን እና ዋጋውን ለማስታረቅ እንዲቻል ነጠላ መጠኑ (unit size) በአምራቹ መገለፅ አለበት:: ዋጋውም በዚያ ወር ውስጥ ከተፈቀደው የማምረቻ ቅጥር ግቢ ለሚወጡ ዕቃዎች በሙሉ ጥቅም ላይ መዋል አለበት:: ይሁን እንጂ የቀረበው ዋጋ ምክንያታዊ መሆን እና የዕቃዎቹን ዋጋ እና ተመጣጣኝ የትርፍ ህዳግን የሚሸፍን መሆን አለበት::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የዋጋ ዝርዝሩ የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛል፡-

- የምርት ኮድ ቁጥር፣
- የኤክሳይዝ ምድብ፣
- ነጠላ መጠን (በአምራቹ የሚገለፅ)፣
- የማምረቻ ወጪ፣
- የትርፍ ህዳግ፣
- የኤክሳይዝ ታክሱ የተሰላበት ዋጋ።

ይህ መረጃ የትርፍ ህዳጉ ተመጣጣኝ ስለመሆኑ እና ዋጋው ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ መተንተን የሚችሉ በርካታ መረጃዎችን ይሰጣል።

ይህን መረጃ እንዴት ማስታረቅ እና ተነቅሰው መውጣት ያለባቸውን ነጥቦች መለየት እንደሚቻል የሚያብራራ ክፍል በቁጥጥር ማኑዋሉ ውስጥ ይገኛል።

4.2.9. የዋጋ ዝርዝሩን ስለማቅረብ

ሁሉም አምራቾች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች በሙሉ ያየዘ የዋጋ ዝርዝር ማቅረብ አለባቸው።

የዋጋ ዝርዝሩ በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ላይ መቅረብ አለበት። የቀረቡት ዋጋዎች ከቀረቡበት ቀጥሎ ባለው ወር ያገለግላሉ። ለምሳሌ መጋቢት 30 የቀረበ የዋጋ ዝርዝር በሚያዚያ ወር ውስጥ ለሚወጡ/ለሚሸጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች በሙሉ የሚያገለግል ይሆናል።

4.2.10. የአምራች ግዴታዎች፡ ማጠቃለያ

አንድ አምራች በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴን በመጠቀም የኤክሳይዝ ታክስን ሲያሰላ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

- የመያዣ መጠኖችን ጨምሮ ለእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለበት ዕቃ ቋሚ ዋጋን የመጠቀም፤
- ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መቅረብ ያለበት ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ቋሚ ዋጋ ማቅረብ እና በዚያው መሠረትም ማስተካከያ ማድረግ፤
- ከተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች የሚወጡ ሁሉም ተመሳሳይ የምርት ዓይነት እና ነጠላ መጠን ያላቸው ዕቃዎች አንድ ዓይነት ዋጋ ሊመደብላቸው ይገባል። ምንም እንኳ ቅናሽ ዋጋ ከንግድ ጋር ለተያያዙ ምክንያቶች ሊቀርብ ቢችልም ለኤክሳይዝ ታክስ የሚውለው ዋጋ ቋሚ ዋጋ መሆን አለበት።
- ምንም ዓይነት ክፍያ ሳይፈፀም ዕቃዎች በሚወጡበት ጊዜ - ነፃ ናሙና ወይም ዕቃውን ወደ ሌላ የኢትዮጵያ አካባቢ የማከፋፈያ መጋዘን/ዴፖ ለማዘዋወር - ቋሚ ዋጋን በመጠቀም የኤክሳይዝ ታክሱን ማስላት አለበት። ይሁን እንጂ ዕቃዎቹ በቀጣዩ ወር ውስጥ ከተሸጡ እና ዋጋው ጭማሪ ካሳየ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ልዩነት መክፈል አለበት።
- ከተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ለመውጣት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ከልዩ የማመሳከሪያ ቁጥር ጋር ደረሰኝ እና የማስረከቢያ ሰነድ ያካተቱ መሆን አለባቸው።
- ቋሚ ዋጋን አለመጠቀም ዝቅ ተደርጎ ለተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ግምገማ እና ቅጣትን ያስከትላል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ያከመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ይህ ዘዴ የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ከተመረቱ መጠኖች ጋር የሚያገናኝ ሲሆን ይህም ከዓለም አቀፍ የኤክሳይዝ ታክስ መልካም ተሞክሮ ጋር የሚጣጣም እና የማረጋገጫ ጉብኝቶች እና የከምችት ቁጥጥር ሥራዎች ላይ እገዛ ያደርጋል::

ክፍል አምስት፡ የተወሰነ የኤክሳይዝ ታክስ፡ መጠን እና ክብደት

ክፍል 5 ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

5 ሀ.1. በመጠን ወይም በክብደት ላይ ብቻ (Specific Method Only)

በመጠን ወይም በክብደት ላይ (Specific Method) የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ብቻ የሚጣልባቸው ዕቃዎች (ይህ ሰነድ በሚዘጋጅበት ጊዜ) በኪሎ ግራም 103 ብር ተመን ያላቸው የፕላስቲክ ከረጢቶች ብቻ ናቸው::

5 ሀ.2. በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴ(መቶኛ) ወይም የዕቃውን መጠንና ክብደት ከሁለቱ አብላጫውን በመውሰድ::

ቢራ በመጠን ወይም በክብደት ላይ (Specific Method በመውሰድ የሚሰላ የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ያለው ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ነው:-

- ከውጭ ሀገር በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ከተመረተ 40% ወይም በሊትር 28 ብር፤
- በሀገር ውስጥ ከበቀለ ገብስ ብቻ ከተመረተ 35% ወይም በሊትር 23 ብር፤ ወይም
- ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% በላይ የሚያህለው በአገር ውስጥ ግብዓት በተመረተ ቢራ ከሆነ 30%፣ በሊትር 21 ብር፤ ከሁለት አንዱ

ከፍተኛው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን መወሰድ አለበት::

ሌሎች የሚፈሉ መጠጦች እና ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ የአልኮል መጠጦች (የአልኮል ይዘታቸው ከ7% የማይበልጥ) በሊትር 28 ብር (ወይም የዋጋውን 40%) መጣኔ አላቸው::

በዋጋ ላይ የተመሠረተ የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ከላይ ክፍል አራትን ይመልከቱ::

5 ሀ.3. ክብደት ወይም መጠን እና በዋጋ (መቶኛ)ላይ የተመሠረተ ዘዴ ጥምረት

- ሲጋር እና ሲጋራ - 30% ሲደመር 20 ብር በእሽግ (20 ፍሬ በሚይዝ አንድ እሽግ)::
- የሚጨስ ትምባሆ (በእጅ የሚጠቀለል ትምባሆ)፣ ሱረት:- 30% ሲደመር 644 ብር በኪሎ ግራም::

በዋጋ ላይ የተመሠረተ የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ከላይ ክፍል አራትን ይመልከቱ::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዝግብና ያስመንዝሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

5 ሀ.4. ክብደት/ብዛት (ኪሎ ግራም/ሊትር)

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ አንቀጽ 12 ጥቅም ላይ የሚውለውን ክብደት (የኤክሳይዝ ታክስ መጠኑ በኪሎግራም ሲሆን) ወይም ብዛት (በሊትር ሲሆን) ይደነግጋል:: በአንቀጽ 12 እንደተገለፀው:-

1/ *ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፣ መሠረት በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለው የዕቃዎቹን ብዛት ወይም ክብደት መሠረት ባደረገ መጠን በሚሆንበት ጊዜ ነው::*

2/ *በሚከተሉት ሁኔታዎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የሚወሰነው ከዕቃው ጋር የሚሸጠውን የዕቃውን ማሸጊያ እና በውስጡ የያዘውን ክብደት መሠረት በማድረግ ይሆናል:-*

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበት ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህ ዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡ ማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፤ እና

ለ) ማሸጊያው:-

(1) የተጣራ ክብደቱ ያልተጻፈበት ከሆነ፤ ወይም

(2) በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘት በተለምዶ የሚታወቅ ባለመሆኑ ወይም አብዛኛውን ጊዜ ይዘቱ የሚታወቅ ባለመሆኑ ትክክለኛ ብዛቱን ወይም ክብደቱን ማወቅ የማይቻል ከሆነ፤ እና

ሐ) የዕቃው ባለቤት የማሸጊያውን የተጣራ ክብደት ትክክለኛነት የታክስ ባለስልጣኑን በሚያረካ አኳኋን ማስረዳት ካልቻለ፣ የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በማሸጊያው እና በውስጡ በያዘው ዕቃ ጠቅላላ ክብደት ላይ ይሆናል::

3/ *በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች በማሸጊያው ላይ ከተገለፀው መጠን ያላነሰ ዕቃ በውስጡ እንዳለው ይቆጠራል:-*

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበት ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህ ዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡ ማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፤ እና

ለ) ማሸጊያው:-

(1) የሚይዘው የተወሰነ ብዛት ያለው ዕቃ በማሸጊያው ላይ የተጻፈበት ከሆነ፤ ወይም

(2) በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘት በተለምዶ የሚታወቅ ከሆነ::

4/ *በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) የተመለከተው ማሸጊያ የያዘው መጠን ከተወሰነው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በትክክለኛው መጠን ላይ ይሆናል::*

5/ *የታክሱ ባለስልጣን በማመረት ሂደት ለሚያጋጥም ቁርጥራጭ እና ውዳቂ የሚፈቀደውን መጠን እና*

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የሚፈቀድበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል::

መመሪያ ቁጥር 1071/2017 ተጨማሪ መመሪያዎችን ይደነግጋል፡-

አንቀጽ 20፡-

(1) የታክሱ ባለስልጣን በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት በማምረቻ ቦታዎች ሊተከሉ የሚገባቸውን የመቁጠሪያ እና የመለኪያ እንዲሁም ሌሎች መሣሪያዎችን ተፈላጊ ባህርያት በጋዜጣ እና በድረ-ገጹ ላይ ማሠራጨት አለበት::

(2) በታክሱ ባለስልጣን የሚፈቀዱት በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የጥሬ ዕቃዎችን፣ የግብዓቶችን እና የአላቂ ዕቃዎችን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው::

(3) የጥሬ ዕቃዎች እና የመጨረሻ ምርቶች ማከማቻ ጋኖች በውስጣቸው ያለውን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል::

(4) በዚህ መመሪያ መሠረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የታክሱ ባለስልጣን በሚወስነው መሠረት በምርቱ ሂደት እያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ላይ መገጠም አለባቸው::

(5) የተፈቀደለት አምራች፡-

(i) የታክሱ ባለስልጣን ለሚያካሂደው ቁጥጥር እና ስሌት በሚያመች መንገድ መቁጠሪያ እና መለኪያ ያላቸውን ጋኖች ወይም ማከማቻዎች የማዘጋጀት፣ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን በየጊዜው የማረጋገጥ፣ እና

(ii) በመቁጠሪያ እና በመለኪያ መሣሪያዎች ላይ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ የተደረገውን ጥገና/እድሳት የሚያሳይ መዝገብ የመያዝ እና መሣሪያዎቹ በትክክል የሚሠሩ ስለመሆናቸው ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መፈተሻቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት::

በአንቀጽ 38 የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት ስለመመዝገብ

(1) የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወነው በዋጋው መቶኛ ወይም በቁርጥ ወይም በሁለቱም ቢሆንም የተመረተው ምርት ብዛት በትክክል ሊመዘገብ እና ሪፖርት ሊደረግ ይገባል::

(2) በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ወይም ለማከማቸት ጥቅም ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች እንዲሁም የማምረቻ እና የማከማቻ ቦታዎች የዕቃዎቹን ብዛት እና ዓይነት በትክክል ለማወቅ የሚያስችሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች ያላቸው መሆን አለባቸው::

(3) በእያንዳንዱ ፋብሪካ በምርት ሂደት ሊያጋጥም የሚችለው ተቀባይነት ያለው የብክነት መጠን በታክሱ ባለስልጣን ይወሰናል::

በአንቀጽ 39 እንደተግለፀው፡- የፈሳሽ ዕቃዎችን ብዛት ስለመለካት

(1) የፈሳሽ ዕቃዎች ብዛት የሚለካው በሁለት ቁልፍ ደረጃዎች ይሆናል፤ እነዚህም፡-

(ሀ) በምርት ሂደት ውስጥ ፈሳሹ በጥቅል ተከማችቶ በሚገኝበት ጊዜ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና የቅርጉ ሚኒስቴር ቁ.1 ቤተ መዛግብትና ሰነድ ማዕከል Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

(ለ) ፈሳሹ በሚታሸግበት ጊዜ፤

(2) የተፈቀደለት አምራች በጥቅል ተከማችቶ የሚገኘው ፈሳሽ እና የታሸገው ፈሳሽ ብዛት እስከተቻለ ድረስ እኩል መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት::

(3) ፈሳሽ ምርቱን በማሸግ ሂደት የሚባክነው መጠን በትክክል ተመዝግቦ መያዝ አለበት::

(4) የተፈቀደለት አምራች የማሸግ ተግባር ከመከናወኑ በፊት እና ከተከናወነ በኋላ ፈሳሹን የሚለካ አስፈላጊውን ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሣሪያ በፋብሪካው ውስጥ መግጠም እና የቆጣሪውን ንባብ በየጊዜው መውሰድ አለበት::

(5) የተፈቀደለት አምራች ፈሳሽ የሚለካውን ቆጣሪ ወይም ሌላ የመለኪያ መሣሪያ ትክክለኛነት በየጊዜው ማስመርመር እና የታክሱ ባለስልጣን በሚጠይቅበት ጊዜ የምርመራው ውጤት እንዲሰጠው ማድረግ አለበት::

(6) ፈሳሽ ምርት ዓሥር ሊትር ወይም ከዚያ በታች በሆነ ቆርቆሮ፣ ጠርሙስ ወይም ሌላ አነስተኛ ማሸጊያ በሚታሸግበት ጊዜ የታክሱ ባለስልጣን የኤክሳይዝ ታክሱ በእያንዳንዱ ማሸጊያ ውስጥ ባለው ፈሳሽ ትክክለኛ መጠን ላይ ተመስርቶ እንዲከፈል ሊያደርግ ይችላል::

(7) በንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም የተፈቀደለት አምራች የሚጠቀምበት ብዛትን የመቆጣጠሪያ ዘዴ "የአማካኝ ይዘት" ከሆነ የታሸገው ፈሳሽ አማካኝ ይዘት በቆርቆሮው ወይም በጠርሙሱ ወይም በህትመቱ ወይም በብረት በርሜል ወይም በእንጨት በርሜል የታሸገ በሚሆንበት ጊዜ በደረሰኙ ወይም በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ ከተመለከተው ያነሰ ሊሆን አይችልም::

(8) የአማካኝ ይዘት ዘዴ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ በጥቅል የተያዘው ፈሳሽ ልኬት፣ የታሸገበት ዕቃ ብዛት እና የማሸጊያው የመያዝ አቅም በትክክል መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ልኬት ከሁለት በመቶ ያልበለጠ ብክነት ሊኖር እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባት የታሸገው ምርት በጥቅል ከተያዘው ፈሳሽ ጋር እኩል መሆኑን ማሳየት አለበት::

(9) እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በፈሳሽ ማከማቻው የተያዘው ፈሳሽ ብዛት ወደ ማሸጊያ ከተላለፈው ብዛት ያልበለጠ መሆኑን ለማረጋገጥ በማሸጊያዎች የመሙላቱ ሂደት ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ አለበት::

(10) የተፈቀደለት አምራች የታክሱ ባለስልጣን ለሚያከናውነው የክትትል ሥራ አጋዥ እንዲሆን በቁጥጥር ሥራው የተገኘውን ውጤት መመዝገብ እና ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል:: በተደጋጋሚ ከመጠን በላይ ፈሳሽን የመሙላት ተግባር መከናወኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ያለ እንደሆነ የተፈቀደለት አምራች ተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል::

5 ሀ.5. የአምራች ግዴታዎች፡ ክብደት/ብዛት (ኪሎግራም)

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ከተፈቀደለት ቦታ ወጪ በሚደረግበት ጊዜ እና የመጨረሻው የማሸግ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ በልዩ ምልክቱ (ሌብል) ላይ በማሸጊያው ውስጥ ያለውን የምርቱን ክብደት የሚገልፅ ማስታወሻ መያዝ አለበት::

በልዩ ምልክቱ (ሌብል) ላይ ክብደቱ/ብዛቱ ያልተጠቀሰ ከሆነ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ትክክለኛውን ይዘት ሊመዝን ወይም ሊለካ እና በክብደቱ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ሊጠይቅ ይችላል:: ይሁን እንጂ በአብዛኛው በምርቱ ልዩ ምልክት ላይ የተገለፀውን ክብደት እንቀበላለን::

የፕላስቲክ ከረጢት (ፌስታል) የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወነው የፕላስቲክ ከረጢቶቹ በሚሠራጩበት መጠቅለያ/ጥቅልል ክብደት ላይ ተመሥርቶ ነው::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ የተጠበቀ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

አግባብነት ያላቸውን የፍተሻ ሥራዎች በምናካሂድበት ጊዜ ጥሬ ዕቃዎችን መመዘን እና የመጨረሻውን ምርት መለካትን ጨምሮ በማንኛውም የምርት ሂደት ዕቃዎች እንዴት እንደሚመዘኑ መረዳታችን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡
:

5 ሀ.6. መጠን/ይዘት (ለመጠጦች በሊትር እና ለሲጋራ በፍሬ)

የአልኮል እና አልኮል አልባ መጠጦች መጠን/ይዘት ሊለካ የሚገባው በሊትር ሲሆን መጠን/ይዘት ደግሞ በፍሬ ነው፡፡

በተጨማሪም የሚፈሉ የአልኮል መጠጦች በውስጣቸው ያለው የአልኮል ይዘት ከ7% ሲበልጥ የተለየ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ እንዳላቸው መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ስለሆነም አንድ አምራች የአንድን ምርት የአልኮል ጥንካሬ (በተለይ ወደ 7% እና ከዚያ በላይ የተጠጋውን) የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ መቻል አለበት፡፡

በአጠቃላይ በልዩ ምልክቱ ላይ የተለጠፈው ብዛት ዝቅ ተደርጎ የተገለፀ እንደሆነ የሚያሳምን ምክንያት ከሌለ በስተቀር የተለጠፈው መጠን እውነተኛ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

የሲጋራ የቀረጥ ማስከፈያ መጠን 20 ፍሬ ሲጋራዎችን በሚይዝ አንድ እሽግ ላይ ተመሥርቶ የሚሰላ ነው፡፡

5 ሀ.7. ትክክለኛው መጠን እና በልዩ ምልክት ላይ ከተቀመጠው ጋር ማነፃፀር

ምንም እንኳን የኤክሳይዝ ታክስ ለአብዛኞቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴን በመጠቀም የሚጣል ቢሆንም አንዳንድ ምርቶች በሁለት መንገድ የሚጣል የታክስ ሥርዓት ይተገበርባቸዋል (ሲጋራ በዋጋ ላይ የተመሠረተ ሲደመር ቁርጥ ተመን ይጣልበታል)፡፡ የአልኮል ይዘታቸው እስከ 7% የሚደርስ ቢራ፣ ሌሎች የሚፈሉ መጠጦች እና ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ መጠጦች በቁርጥ ዘዴ ላይ ተመሥርቶ በሊትር የሚሰላ መጣኔ አላቸው፡፡

ሆኖም የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት/ምርት ዋጋ ከብዛት አንፃር በሚያስተካክለው የዋጋ ዝርዝር መስፈርት ምክንያት ብዛቱንም ከኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያው ጋር ማስታረቅ ይቻላል፡፡

የቁጥጥር ሥራውን ቀላል ለማድረግ በልዩ ምልክቱ ላይ የተለጠፈውን ይዘት መቀበል የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ባለ 600 ሚሊ ሊትር ጠርሙስ ቢራ በልዩ ምልክቱ ላይ እንደተለጠፈው 600 ሚሊ ሊትር እንዳለው ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ነገር ግን ናሙና ከተወሰደ እና በእያንዳንዱ ጠርሙስ ውስጥ ያለው 650 ሚሊ ሊትር ሆኖ ከተገኘ በእያንዳንዱ ጠርሙስ ውስጥ ላለው ተጨማሪ 50 ሚሊ ሊትር የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ማከናወን እንችላለን፡፡ በተመሳሳይ የሲጋራ እሽጎች ሲፈተሹ 22 ሲጋራዎችን ይዘው ከተገኙ በተጨማሪዎቹ ሲጋራዎች ላይ ተጨማሪው ታክስ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

5 ሀ.8. ማጠቃለያ

መከፈል ያለበትን የኤክሳይዝ ታክስ ለመወሰን እና ለማንኛውም ተመላሽ የኤክሳይዝ ታክስ እንዴት እንደሚሰላ በግልፅ ማስቀመጥ ወሳኝ ነው፡፡

ዋጋው (በዋጋ ላይ ለተመሠረተ ተመን) እና መጠኑ/ይዘቱ/ክብደቱ (ለቁርጥ የታክስ ተመን) በግልፅ ግንዛቤ ሊወሰድባቸው እና በማስረጃ ሊደገፉ ይገባል፡፡

የሽያጭ መጠኖች በየወሩ አዲት መደረግ ያለባቸው ሲሆን ትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን መመዝገቡን ለማረጋገጥ ደረሰኞች መተንተን አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ማናቸውም ከክፍያ ነፃ የሆኑ ከማምረቻ ቦታ ዕቃዎችን የማውጣት ተግባራት የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ የተገለፀበት ደረሰኝ ሊኖራቸው ይገባል:: የማስረከቢያ ሰነዶቹም በሁሉም የማስወጣት ተግባራት ላይ መኖር አለባቸው::

ለሲጋራ የሚጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ በአንድ እሽግ ውስጥ ካሉት ሲጋራዎች ቁጥር አንፃር መሆን አለበት፡ :

ለክብደት እና ብዛት ግምት በልዩ ምልክቱ ላይ የተገለፀው መጠን እንደ አጠቃላይ ትክክለኛ መጠን ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ሲሆን፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ልኬቶች በፋብሪካ ጉብኝት ወቅት በየጊዜው መፈተሽ ይኖርባቸዋል::

ክፍል 5ለ፡ የኤክሳይዝ ታክስ የቁርጥ ስሌት ላይ የሚደረግ ቁጥጥር እና ክትትል

5ለ.1. መግቢያ

ይህ ክፍል የሚከተሉትን ጉዳዮች ያብራራል:-

- በአምራቾች ዘንድ ትክክለኛው መጠን ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ እንደምንችል፤
- መጠኑ እንዴት ክትትል ሊደረግበት እንደሚችል፤ እና
- በክትትል ሂደቱ ውስጥ እገዛ ስለሚያደርጉልን የመረጃ ምንጮች::

5ለ.2. መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች በዋጋ ላይ የተመሠረተ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የሚሰላባቸው ሲሆን ይህም ከላይ በክፍል አራት ተዳስሷል::

ይሁን እንጂ:-

- የፐላስቲክ ከረጢቶች (ፌስታሎች) በኪሎ ግራም የተቀመጠው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ይከፈልባቸዋል፤
-
- ሲጋራ በዋጋ ላይ የተመሠረተ ዘዴን እና የቁርጥ መጣኔን የያዘ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የተጣለበት ሲሆን ይህም 20 ፍሬ ሲጋራዎችን በሚይዝ አንድ እሽግ ላይ በተቀመጠው ተመን ላይ ተመስርቶ የሚሰላ ነው::

5ለ.3. በቁርጥ መጠን ስሌት

የኤክሳይዝ ታክስ የቁርጥ መጣኔ ስሌት ከሚከተሉት በአንዱ ዘዴ ይከናወናል:-

- በኪሎ ግራም፤
- በሊትር፤ ወይም
- 20 ፍሬ ሲጋራዎችን በሚይዝ አንድ እሽግ::

አምራቾች ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ለማስላት በእያንዳንዱ ማሸጊያ/መያዣ ላይ የተለጠፈውን መጠን መጠቀም ይችላሉ:: ስለሆነም ለፐላስቲክ ከረጢቶች አንድ ጥቅል እንደ አንድ መጠን ክብደት ተደርጎ ይወሰዳል፤ ይህም ዕቃው ከፋብሪካ ሲወጣ የኤክሳይዝ ታክሱ የሚሰላበት ይሆናል:: ለአልኮል መጠጦች የቁርጥ መጣኔን የሚጠቀሙ በጣም ጥቂት የምርት ዓይነቶች ይኖራሉ (ካሉ)፤ እንዲሁም ከሲጋራ ማምረቻው የሚወጣ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

እያንዳንዱ የሲጋራ እሽግ የኤክሳይዝ ታክሱ የቁርጥ መጠን ስሌት መነሻ ይሆናል::

የሲጋራ እሽጎች ናሙና በትክክል 20 ፍሬ ሲጋራዎችን መያዙን (እንዲሁም ለምሳሌ 22 ሲጋራዎችን አለመያዙን) እና የፕላስቲክ ከረጢቶች ጥቅልል የተገለፀውን ክብደት በትክክል መያዙን ማረጋገጥ አንችላለን::

ሲጋራዎች ከ20 ያነሱ (ወይም የበለጡ) ሲጋራዎችን በያዙ እሽጎች ውስጥ የሚሸጡ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ የቁርጥ መጠን ተመጣጣኝ ድርሻ (pro-rata-ed) መሆን አለበት::

ለምሳሌ 10 ሲጋራዎችን የያዘ አንድ እሽግ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋን በመጠቀም የተሰላው የኤክሳይዝ ታክስ ሲደመር በእሽግ 3 ብር (20 ሲጋራዎችን በያዘ አንድ እሽግ ላይ በሚጣለው 6 ብር ፈንታ) ይጣልበታል::

5ለ.4. ማጠቃለያ

ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውልባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በዋጋ ላይ ለተመሠረተ የኤክሳይዝ ታክስ ከሚሰጠው የዋጋ ግምት ያነሰ ትኩረት ለእነዚህ ማጣራቶች ሊሰጥ ይችላል: :

ይሁን እንጂ እነዚህ ማጣራቶች በየጊዜው መካሄድ አለባቸው:: 20 ሲጋራዎችን የሚይዝ አንድ እሽግ ግዢ በሚፈፀምበት ጊዜ እንኳን በውስጡ 20 መያዙን ማረጋገጥ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ ማንኛውም የሲጋራ ፓኮ ከ20 ፍሬ በላይ ከያዘ ሪፖርት ማድረግ ይኖርብናል:: ምክንያቱም በተጨማሪዎቹ ሲጋራዎች ላይ የተሰላ የኤክሳይዝ ታክስ መጠን አይኖርምና::

በተጨማሪም በማንኛውም ሌላ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ላይ የተለጠፈውን ብዛት/መጠን ማረጋገጥ እና የተለጠፈው መጠን ከሌሎች ተመሳሳይ ማሸጊያዎች ጋር ሲነፃፀር ትክክል ስለመሆኑ ትንተና ማካሄድ ይኖርብናል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 መዛግብትና ሰነዶች አስተዳደር
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ስድስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ስለሚሰጥ ምዝገባና ፈቃድ (የአዋጁ አንቀፅ 15 እስከ 23 እና የመመሪያው 1071/2017 አን 4 እስከ 11)

6.1. መግቢያ

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ለኤክሳይዝ ታክስ የቁጥጥር ሥራዎች ሁሉ መሠረት ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ፈቃድ በአምራቹ እና በገቢዎች ሚኒስቴር መ/ቤት መካከል የሚኖር የውል ስምምነት በመሆኑ መከበር ይኖርበታል፡፡

ማናቸውም ማሻሻያዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መገለፅ ያለባቸው ሲሆን ማንኛውም አዲስ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በፈቃድ ምዝገባ ማመልከቻ ላይ የተዘረዘሩት ስለመማላታቸው መጣራት ወይም መረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

ፈቃዱ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደለት ሰው ስም፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የሚመረቱበት እና የሚከማቹበት ፋብሪካ (ወይም ፋብሪካዎች) አድራሻ እና ዝርዝር መረጃዎች በሙሉ፤
- በእያንዳንዱ የማምረቻ ቦታ ምን ሊከናወን እንደሚችል ዝርዝር ማብራሪያ፤
-
- ከግብር ከፋይ መለያ ቁጥር በተጨማሪ ልዩ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥር፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ማናቸውንም ዕቃዎች ለማምረት የሚፈልግ ማንኛውም ግብር ከፋይ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡ የፈቃድ ጉዳይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሲሆን አመልካቹ "ብቁ እና ተገቢ" መሆኑን ለማረጋገጥ ለአዲስ ግብር ከፋይነት የሚቀርቡ ማመልከቻዎች መተንተን እና መረጃዎችም መፈተሽ አለባቸው፡፡ ይህም ማለት ድርጅቱ (ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ከሆነ ማናቸውም ዳይሬክተሮች) በማጭበርበር ድርጊት ያልተሳተፈ እና ሊከፈሉ የሚገባቸውን ታክሶች በሙሉ የከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ግብር ከፋዩ የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታዎቹን መወጣት እንደሚችል እና የአንድ የተወሰነ ኩባንያ ዳይሬክተሮች ጥሩ የንግድ ሥራ ሪከርድ እንዳላቸው በገቢዎች ሚኒስቴር እስካልተረጋገጠ ድረስ ፈቃድ መሰጠት የለበትም፡፡

አመልካቹ ለታክስ ባለስልጣኑ በአካል ከመቅረቡ፣ የቢዝነስ ሞዴሉ ከመፈተሹ እና የማምረቻ ቦታዎች ከመጎብኘታቸውና ከመገምገማቸው በፊት ፈቃድ መሰጠት የለበትም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱ ለዓላማው ተስማሚ መሆኑን እና አስፈላጊ የሆኑ ተዛማጅ መዝገቦችን እና ቅጾችን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ለማረጋገጥ የተተነተነ እና መሆን አለበት፡፡

6.2. ፈቃድ የሚያስፈልገው ለማን ነው?

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ አንቀጽ 15 ለሚከተሉት ሥራዎች የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል፡-

- በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት፤
- የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማቅረብ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶችን ማቅረብ
- የፋይናንስ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ በሚጥልባቸው ሌሎች የሥራ ዘርፎች መሠማራት፡፡ (ይህም የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ከታክስ ነፃ በሆነ አቅርቦት ሊገዛ የሚችልን ማንኛውንም ሰው ሊያካትት ይችላል፤)፡፡

በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) እንደተገለፀው ፈቃድ ሳይኖረው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎቶችን በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው በዕቃዎቹ ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡ በአንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል የሚገደድ ማንኛውም ሰው በታክስ ባለስልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ ታክሱን ወዲያውኑ መክፈል ያለበት ሲሆን በተጨማሪም የተጣለበትን ቅጣት እና ወለድ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በኤክሳይዝ ታክስ መመሪያ ቁጥር 1071/2017 እንደተገለፀው፡-

- የመመሪያው አንቀፅ 8 ንዑስ አን 2-5 ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በስተቀር የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን አይችልም፡-

  - የሲጋራ ማምረቻ ወረቀት እና የሲጋራ ማሽኒያ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፤
  - ጥሬ ወይም በምርት ሂደት ያላለፈ ትንባሆን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፤
  - ኤታኖል ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፤

የሲጋራ ማምረቻ ወረቀት እና የሲጋራ ማሽኒያ ዕቃዎች እንዲሁም ጥሬ ወይም በምርት ሂደት ያላለፈ ትንባሆ አስመጪ ሆኖ ሊመዘገብ የሚችለው የትምባሆ ምርቶችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡፡

የአልኮል መጠጦችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጣቸው አምራቾች ብቻ ኤታኖል ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚችሉ ሲሆን የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ምርቶች ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚችሉት የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ ባለቤት ለመሆን የተመዘገቡ ሰዎች ብቻ ናቸው፡ :

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ምርቶች ማምረት ለመጀመር የሚፈለግ ማንኛውም አዲስ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ የኤክሳይዝ ታክስ ማመልከቻ ቅጽን ማቅረብ አለበት፡፡

በማመልከቻ ቅጹ ላይ የቀረቡት መረጃዎች በሙሉ መተንተን ያለባቸው ሲሆን፣ ሁሉም ዳይሬክተሮች በሌሎች ኩባንያዎች ውስጥ የተሠማሩ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ በገቢዎች ሚኒስቴር ሲስተም ላይ መጣራት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ፋብሪካው የሚገኝበትን ቦታ በተመለከተ ተጨማሪ የማጣራት ሥራዎች መከናወን አለባቸው፡ :

አመልካቹን ለማግኘት እና የማምረቻ ቦታውን (የኤክሳይዝ ታክስ ለሚከፈልባቸው ዕቃዎች) እና ዋና መሥሪያ ቤቱን (ለአገልግሎቶች/ቴሌኮሙኒኬሽን) ለመፈተሽ በአካል ጉብኝት ሳይደረግ ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም፡፡

6.3. የታክስ ከፋዩ ግዴታዎች (የአዋጁ አንቀፅ 19)

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁጥር 1 ቤተ መዛግብትና የክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት (ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርብ) ማንኛውም ሰው ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ እና ወቅታዊ የተደረገ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ መያዝ አለበት::

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሳይኖረው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ሲያመርት የተገኘ ማንኛውም ሰው በአካል በተያዙት ዕቃዎች ላይ ወዲያውኑ የኤክሳይዝ ታክሱን መክፈል ያለበት ሲሆን፣ ለቅጣትም ይዳረጋል::

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ አመልካቹ ማመልከቻውን በሚያቀርብበት ጊዜ ሊያመርታቸው ባቀዳቸው ምርቶች ላይ ብቻ የተገደቡ ይሆናሉ:: እንዲሁም ፈቃዱ መከበር ላለባቸው ሁኔታዎች ተገዢነት ይኖረዋል::

6.4. የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት ፣ የብቃት እና ተገቢነት ፍተሻ

የአዋጁ አንቀጽ 16 አንድ ሰው ፈቃድ ለማግኘት በተደነገገው መሠረት እና ተገቢውን ቅጽ በመጠቀም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ እንዳለበት ይገልፃል::

የአዋጁ አንቀጽ 17 የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸው ከተረጋገጠ ማመልከቻ ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል ይገልፃል:

-

- አመልካቹ በዚህ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት በታክስ መሰወር ወይም በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤
- አመልካቹ በማናቸውም ሕግ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤
- አመልካቹ የከሰረ ወይም ዕዳውን ለመክፈል ያልቻለ ከሆነ፤ ወይም በኪሳራ ምክንያት ሀብቱ በመጣራት ላይ ያለ ወይም ባለአደራ የተሰየመበት ከሆነ፤
- አመልካቹ በማናቸውም የታክስ ሕግ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፤ ወይም በማናቸውም የታክስ ሕግ የቲጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ ኪሆነ፤ ወይም
- አመልካቹ በታክስ ባለስልጣኑ በተጠየቀው መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታውን ለመወጣት ያልተስማማ ከሆነ፤
- በማመልከቻው ላይ የተጠቀሰው ፋብሪካ፣ ማምረቻ ወይም መሣሪያ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ወይም ለመከታተል በቂ ካልሆነ::

በተጨማሪም ይህ መመዘኛ ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው የሚመለከት ሲሆን፣ ተፈፃሚ የሚሆነው የታክስ ባለስልጣኑ ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መስክ ውስጥ የሚሠማራ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ያለው በሚሆንበት ጊዜ ነው::

አንቀጽ 17 በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋብሪካው ቅጥር ግቢ ተስማሚ ስለመሆኑ መመርመር እንዳለበት ይገልፃል:: በተለይም አመልካቹ ሁሉንም ማምረቻዎች እና መሣሪያዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማሳወቅ ያለበት ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱም ማመልከቻው ለቀረበባቸው ተግባራት ተስማሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት:: በዚህም መሠረት ማንኛውንም ስርቆት ለመለየት በሚያስችል ሁኔታ ግቢው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቁጥጥር የሚደረግበት መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: ለምሳሌ መግቢያ እና መውጫ መኖሩን ማረጋገጥ ያለብን ሲሆን ይህም የገቢ እና ወጪ እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ለመቆጣጠር ያስችላል::

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

አንቀጽ 17 የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከተሉትን እንደሚያደርግ ይገልፃል፡-

- ከፈቃድ ጋር በተያያዘ አስፈላጊ መስሎ ከታየው የውል ቃሎች እና ሁኔታዎች ወይም ገደቦች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል፤ እንዲሁም
- ማመልከቻው ውድቅ የተደረገ ከሆነ፣ ተቀባይነትን ካገኘ ወይም ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ መግለፅ አለበት::

6.5. የግብር ከፋዩ ግዴታዎች፡ የፈቃድ ማመልከቻ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራቾች የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት በኤክሳይዝ ታክስ መመሪያ ቁጥር 1071/2017 አንቀጽ 8 ላይ የተደነገገ ሲሆን ይህም የአምራችነት ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ሚከተሉትን ማቅረብ እንዳለበት ይገልፃል፡-

- አመልካቹ የሚጠቀምባቸውን የአመራረት ሂደቶች የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ፣ ይህም እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሣሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ ኮንቴይነሮች እና መገጣጠሚያዎችን ይጨምራል::
- የአሠራር ሂደቱን የሚገልፅ የጽሑፍ ማብራሪያ፤
- ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የማምረቻ ሕንፃ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እንዲሁም የሕንፃውን ሁኔታ እና አካባቢውን፤
- የእያንዳንዱን በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሣሪያ የማምረት አቅም በዝርዝር፤
- የማምረቻ መሣሪያዎችን ማስረጃዎች እና መግለጫዎች፤
- በአዋጁ ወይም በዚህ መመሪያ ይህንን ፈቃድ ለማግኘት እንዲሟሉ የሚጠበቁ መሣሪያዎችን፣ የአመራረት ሥርዓት ወይም ሌላ ተፈላጊ ሁኔታን የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች፤

6.6. የአምራች የማምረቻ ቦታዎች (የመመሪያው አንቀፅ 9)

አንድ አምራች ለአዲስ ፈቃድ ወይም በነባር ፈቃድ ተጨማሪ ፋብሪካ ለማቋቋም ማመልከቻ ሲያቀርብ አካላዊ ጥበቃው ጠንካራ መሆኑን፣ የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱ አስተማማኝ መሆኑን እና ጥቅም ላይ የሚውሉት መሣሪያዎች አመልካቹ በማመልከቻው ላይ ከዘረዘራቸው ምርቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የማምረቻ ቦታዎቹ ካልተጎበኙ በስተቀር ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም::

በነባር ፈቃድ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ማሻሻያዎች እንደ ማንኛውም አዲስ ማመልከቻ መቆጠር አለባቸው::

6.7. በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ

በመመሪያ ቁጥር 1071/2017 አንቀጽ 16 በተደነገገው መሠረት የተፈቀደለት አምራች፡-

- የታክሱ ባለስልጣን በሚጠይቀው መሠረት በማምረቻ ቦታው ዋና የመግቢያ በር እና በሌሎችም አስፈላጊ ቦታዎች ላይ በአማርኛ እና በአካባቢው የሥራ ቋንቋ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ" እና የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ጽሑፍ ታፔላ መለጠፍ አለበት::
- በምርቱ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተላለፊያ መስመሮች በቋሚነት የተገጠሙ እና መላውን ርቀት በትክክል ለመመርመር የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት::
- የማከማቻ እና የማስተላለፊያ መስመሮች ኢንዱስትሪው የሚጠይቀውን ደረጃ የሚያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሚመረቱባቸው፣ ለሽያጭ በሚዘጋጁባቸው ወይም በሚከማቹባቸው መሣሪያዎች ላይ በዘይት ቀለም ምልክት ማድረግ አለበት::
- የታክሱን ባለስልጣን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ለክትትል እና ቁጥጥር በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ የተገጠመላቸው እንዲሆኑ ማድረግ አለበት::
- የታክስ ባለስልጣኑን የኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ እና ቁጥጥር ማቀላጠፍ በሚያስችል መንገድ መሣሪያዎችን ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ እንዲቻል አድርጎ ማዘጋጀት አለበት::
- የታክሱን ባለስልጣን በሚያረካ ሁኔታ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን:-

በእያንዳንዱ የማምረት ሂደት የምርት ርክክብ የሚፈፀምባቸው የማስተላለፊያ መስመሮች በተለያየ የዘይት ቀለም እንዲቀቡ እና ቀለሙ እንዳይደበዝዝም በየጊዜው እንዲታደስ ማድረግ፤ እንዲሁም ለፍተሻ እና ቁጥጥር በሚያመች ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ መግጠም አለበት::

የተፈቀደለት አምራች የሚከተሉትን የቀለም ኮዶች በመጠቀም ቅደም ተከተሉን በጠበቀ እና በተሟላ መንገድ የማስተላለፊያ መስመሮቹን መቀባት ይኖርበታል:-

- የአልኮል መጠጦች: ቀይ፣
- ቢራ: ሰማያዊ፣
- ሞላሰስ: አረንጓዴ፣
- የሚጠራ ወይን: ቡናማ፣
- ውሃ: ቢጫ፣
- ናፍታ: ጥቁር፣

የአመራረቱን ሂደት ወይም ሥርዓቱን መለወጥ፣ ማከማቻ ወይም መሣሪያ መጨመር የሚቻለው ከታክሱ ባለስልጣን አስቀድሞ ፈቃድ ሲሰጥ ብቻ ነው::

በተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ውስጥ የአስተዳደር ሥራዎች የሚከናወኑበት ቢሮ፣ የማምረቻው ቦታ፣ የጥሬ ዕቃ መጋዘኑ እና የምርት መጋዘኑ የተለያዩ መሆን አለባቸው:: በዚህም መሠረት ለእያንዳንዱ ተግባር የተመደበው ቦታ ጥበቃ የሚደረግለት፣ አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስን በሚገባ ለመሰብሰብ እንዲቻል ለይቶ ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ የሚያስችል አካል የተገጠመለት መሆን አለበት::

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የተፈቀደለት አምራች እና አስመጪ የሚያመርታቸውን ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ዕቃዎች የሚያከማችበት በታክሱ ባለስልጣን የተፈቀደ የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል::

6.8. የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ቅርጸ

በአዋጁ አንቀፅ 18 እንደ አጠቃላይ ፈቃዱ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል:-

- ፈቃድ የተሰጠውን ሰው/ኩባንያ፤
- አምራቹ ለማምረት ፈቃድ ያገኘባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ምደብ ወይም ምደቦች፤ እና
- አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደለትን ፋብሪካ ወይም ፋብሪካዎች፤
- ሌሎች ሊደነገጉ የሚችሉ ማናቸውም ሁኔታዎች::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቴክ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በፈቃዱ ላይ ስሙ በተጠቀሰው ሰው ተገቢ በሆኑት ፋብሪካዎች ሊመረቱ የሚችሉት በፈቃዱ ላይ የተዘረዘሩት ዕቃዎች ብቻ ናቸው::

ማንኛውም ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል:: ምንም እንኳን ማንኛውም ግዴታን ያለመወጣት ተግባር ሲገኝ በየዓመቱ የሚሰጥ ማረጋገጫ ለዓመታዊ እድሳት እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊቀመጥ ቢችልም በማረጋገጫው ላይ "የሚያበቃበት ቀን" መኖር የለበትም::

6.9. ፈቃድ ከተሰጠ በኋላ የታክስ ከፋይ ግዴታዎች

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 19 ፈቃድ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ግዴታዎችን የሚዘረዝር ሲሆን ሰው/ድርጅት የሚከተሉት የመፈፀም ግዴታዎች አሉባቸው:-

- የተሰጠውን ፈቃድ ዋና ቅጂ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ዋና የሥራ ቦታ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ፤ እንዲሁም የፈቃዱን ኮፒ በፈቃዱ ላይ በተጠቀሱት ፋብሪካዎች ሁሉ መለጠፍ፤

- ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች ለታክስ ባለስልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት:-

  - ፈቃድ የተሰጠበትን ሥራ ያቆመ እንደሆነ፤
  - የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነውን ዋና ተግባር ወይም ተግባራት መጠሪያ፣ አድራሻ፣ ሥራውን የሚያከናውንበትን ቦታ፣ ባለቤትነት፣ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የሥራውን ባህሪ የለወጠ እንደሆነ፤
  - የተፈቀደለት አምራች የሥራውን እንቅስቃሴ ለተወሰነ ጊዜ በጊዜያዊነት ያቋረጠ እንደሆነ፤ ወይም
  - የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት በሚጠቀምበት በፈቃዱ በተመለከተው ፋብሪካ ወይም ማምረቻ እና መሣሪያ ላይ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ::

የሥራ እንቅስቃሴው ባልታቀደ ሁኔታ በጊዜያዊነት ከተዘጋበት ቀን ጀምሮ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ ወይም ሌላ ማንኛውም ለውጥ ከመደረጉ ቢያንስ ሰባት ቀናት ለሰፉድም ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቂያ እንዲደርስ መደረግ አለበት::

ሙሉ በሙሉ አዲስ ፋብሪካ በሚከፈትበት ጊዜ፣ እንደ አዲስ ማመልከቻ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማስታወቂያ እንዲደርስ መደረግ አለበት:: የማምረቻ ቦታውን ለመጎብኘት እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ እና በኤክሳይዝ ቁጥጥር ስር ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች አመራረት እና ማከማቻ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አስፈላጊ ሲስተሞች እንዳሉት ለማረጋገጥ እንዲቻል ፋብሪካው ማምረት ከመጀመሩ ቀን ቢያንስ 30 ቀናት አስቀድሞ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማሳወቅ ያስፈልጋል::

የማምረቻ ቦታው በፈቃዱ ላይ ሳይካተት በፊት ፋብሪካ ማምረት ከጀመረ ጊዜ በተያዙት ዕቃዎች ላይ ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል ያለበት ሲሆን ቅጣትም ተፈፃሚ ይሆናል::

6.10. ማጠቃለያ

አዲስ ማመልከቻን የመተንተን ሂደት በኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ውስጥ ተብራርቷል::

እንደ አጠቃላይ መስተዋል ያለበት ዋናው ጉዳይ ፈቃዱ በገቢዎች ሚኒስቴር እና በነጋዴው/ግብር ከፋዩ መካከል የሚደረግ የስምምነት ውል መሆኑን ነው:: ስለሆነም የነጋዴውን እና የማምረቻ ቦታዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች መሟላት እና ማናቸውም ለውጦች ለውጡ ከመከናወኑ በፊት መገለፅ አለባቸው::

እንደ ቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅቶች ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት አገልግሎት ሰጪዎች የሚያቀርቡት

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 የሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዓይነቶች በፈቃዱ ላይ የሚካተቱ ይሆናል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ሰባት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር: የአዋጁ አንቀፅ 25 እስከ 29 እና የመመሪያው አንቀጽ 12 እስከ 20

ክፍል 7ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

7ሀ.1. መግቢያ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ላይ በተፈቀደ የማምረቻ ቦታነት በተመለከተው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎችን በሚያመርት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲቆዩ "በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር" ስር ናቸው፡፡ ይህም ማለት ምንም እንኳ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ ያለባቸው ቢሆንም ዕቃዎቹ ጥቅም ላይ እስኪውሉ ወይም ከፋብሪካው እስኪወጡ ድረስ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አያስፈልገውም፡፡

"በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር" የሚለው አገላለፅ በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ ተሰልቶ ከተከፈለ በኋላ ወደ ፋብሪካው የተመለሱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችንም ያጠቃልላል፡፡ በዚህም መሠረት ታክስ የተከፈለባቸው ዕቃዎች በግልፅ ተለይተው መታወቅ ያለባቸው ሲሆን የተከፈለባቸውን ታክስ የሚያረጋግጥ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማስረጃ መኖር አለበት፡፡

7ሀ.2. የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ምንድነው?

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 25 በተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውስጥ መከበር ያለባቸውን ደንቦች እና ግዴታዎች እንደሚከተለው ይደነግጋል፡-

- **አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (1)፡** በፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ሰሙሉ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡

- **አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ (2)፡** የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በፋብሪካ ላይ ፣ በአከፋፋይና በጅምላ ሽያጮች ድረስ ባሉት የገበያ ሰንሰለት ድረስ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረገው በሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ይሆናል፡-

    - በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከፋብሪካ እስከሚወጡ

    - ዕቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጭ እስከሚላኩ (ይሁን እንጂ ወደ ውጭ ስለመላካቸው ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አለበት)፤

    - ዕቃዎቹ ከአገልግሎት ውጭ ወይም እስከሚወገዱ ድረስ (ለመወገዳቸው ማስረጃ ካልቀረበ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አለበት፤ ወይም የተወገዱት የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ከሆኑ የተመላሽ ሂደቱ ከታች በክፍል 14 የተገለፀውን የተከተለ ካልሆነ ጥያቄው ውድቅ መደረግ አለበት)፡፡

    - ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋሉ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ያክመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1 ★

በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አለበት::

7ሀ.3. ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1-3 የተፈቀደለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች ሊወጣቸው የሚገቡ ግዴታዎችን ዝርዝር ይደነግጋል::

የኤክሳይዝ ታክስ መመሪያው በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ ስለሚከናወኑ ምልክት የማድረግ፣ የማከማቸት፣ የመዝገብ አያያዝ እና የልኬት መመዘኛዎችን የተመለከቱ ተግባራትን በዝርዝር ያቀርባል::

አንቀጽ 26 የተፈቀደለት አምራች የሚከተሉትን ግዴታዎች መወጣት እንዳለበት ይደነግጋል:-

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ)፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም ጥሬ ዕቃዎችን ለመመዝገብ፣ ክብደታቸውን ለመመዘን፣ ለመቁጠር ወይም ለመለካት እንዲችል በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች እንዲኖሩ እና በሚገባ እንዲጠበቁ የማድረግ፤
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ)፡ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የተሟላ ቁጥጥር ለማድረግ በሚያስችል መንገድ የማስቀመጥ፤
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ)፡ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የጥሬ ዕቃዎችን ምዝገባ ማካሄድ፣ በተለይም በማምረት ሂደት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፋብሪካው የተረከባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና ግብዓቶች በእነዚህ ቅጾች ላይ መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (መ)፡ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማከናወን፣ እና በዚሁ ቅጽ ላይ በፋብሪካው የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና ከፋብሪካው የወጡ ጥሬ ዕቃዎችን መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ)፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የማረጋገጥ፤
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ረ)፡ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ እንዲሟሉ የሚጠየቁ ሁኔታዎችን የማሟላት፤ እንዲሁም አምራቹ አዋጁን ለመደገፍ ለሚወጡ ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ደንቦች ተገዢ የመሆን ግዴታ ቁጥሎበታል:: አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2 የታክሱ ባለስልጣን በሚያወጣው መመሪያ ተፈላጊ የሆኑ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መሳሪያዎችን ተፈላጊ ባህሪያት ሊወስን ይችላል::
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (3) (ሀ)፡ የታክስ ባለስልጣኑ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ናሙና ከአምራቹ በነፃ የመውሰድ መብት ያለው ሲሆን፣ እነዚህ ናሙናዎች የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሊወገዱ ወይም ለአምራቹ ሊመለሱ ይችላሉ::
- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (3) (ለ)፡ የታክስ ባለስልጣኑ አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልባቸውን ናሙናዎች እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል::

7ሀ.4. የአንቀጽ 26 ተግባራዊ ተፈፃሚነት

የአንቀጽ 26 (እና የአንቀጽ 25) ድንጋጌዎች በሚገባ በግልፅ የተቀመጡ ናቸው:: ማንኛውም ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ፈቃድ እንዲሰጠው በገቢዎች ሚ/ር የሚቀርብ ልዩ መብት ነው:: በተፈቀደለት ፋብሪካ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ እስኪወጡ ድረስ ያለ ኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ እንዲቆዩ ማድረግ መቻል ፈቃድ የሚያስገኘው ጥቅም ነው:: ስለዚህም ፈቃዶች እዚህ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ጋር የተሰናሰኑ ሲሆን አንቀጽ 26 እነዚህን አንኳር ሁኔታዎች ይደነግጋል (ከላይ ክፍል 7ሀ3ን ይመልከቱ)::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

እንደ አጠቃላይ እያንዳንዱ የፋብሪካው ቦታ ዓላማውን በግልፅ መቀመጥ እና ሁሉንም የማከማቻ ቦታዎች እና ምን ዓይነት ሥራዎችን እንደሚያከናውኑ ወይም በእያንዳንዱ አካባቢ የተከማቹ ዕቃዎችን በሚያሳይ የማምረቻ ቦታ (site plan) ላይ በግልፅ ምልክት መደረግ አለበት፡፡ በማምረቻ ቦታ እና በፈቃዱ ላይ የሚደረጉ ማናቸውንም ለውጦች በተመለከተ ለውጡቹ ከመከናወናቸው በፊት ማሳወቅ ይገባል፤ ለውጡቹን ለማመልከትም አዲስ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

7ሀ.5. ቅጣቶች

የአዋጁ አንቀጽ 38 አስተዳደራዊ ቅጣቶች

ፈቃድ ሳይኖረው በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ ፣ ሀ እና ለ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ሰው የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል፡-

- የአዋጁን አንቀጽ ሀ ተፈፃሚ የሚሆንበትን በሚመለከት ፈቃድ ቢሰጠው ኖሮ ሊከፍል ይገባ የነበረውን ኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ
- የአዋጁ አንቀጽ 38 ለ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሰው በሚመለከት የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው በሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን ኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ
- በፍቃዱ ላይ ከተመለከተው ቦታ ውጭ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ የተሰማራ የኤክሳይዝ ታክስ ከፋይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን እጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል፡፡
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ወጪ ካደረገ በእቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን እጥፍ ሊከፍል ይገባል
- በዚህ አንቀጽ የተደነገጉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ በታክስ አስተዳደሩ ላይ የተገለጹት አስተደዳራዊ ቅጣቶች ማለትም በወቅቱ ባለማሳውቅ አንቀጽ 104 እና በወቅቱ ባለመክፈል አንቀጽ 105 ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (4) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ከነበሩበት ቦታ የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈል እንዲወጡ ያደረገ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ቅጣቶች እንደሚጣሉበት ይገልፃል፡-

- ከ5 እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት፤ ወይም
- ከብር 100,000 እስከ 200,000 የገንዘብ ቅጣት፡፡

ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁ እና አዲስ ፈቃድ ሳይሰጥ የማከማቻ ቦታዎች ከተቀየሩ ዕቃዎቹ በተፈቀደ ቦታ ላይ ሊቀመጡ አይችሉም፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁጥር 1 ታክስ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

7ሀ.6. ማጠቃለያ

የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር አንድ የተፈቀደለት አምራች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ሆኖ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት እና ዕቃዎቹን ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ እስኪወጡ ድረስ ያለምንም የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማከማቸት የሚችልበት ልዩ መብት ነው።

በጥፋቶች ላይ ጥብቅ ሁኔታዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤ ስለሆነም አምራቾች ለእነዚህን ሁኔታዎች ተገዢ መሆን አለባቸው። እንዲሁም የገንዘብ ቅጣቶች ወይም የበለጠ ጥብቅ ሁኔታዎች በፈቃዳቸው ላይ (ቀደም ሲል የነበረ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያን ጨምሮ) ተፈፃሚ ይሆናሉ።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ቤተመጻሕፍት ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል 7ለ፡ በተፈቀደላቸው አምራች ፋብሪካ ላይ ስለሚደረግ ቁጥጥር

7ለ.1. አጠቃላይ እይታ

የተፈቀደላቸው አምራቾች በአንቀጽ 25 እና 26 ለተቀመጡት ግዴታዎች በሙሉ ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡ ግዴታቸውን መወጣታቸውን መቆጣጠር የምንችልበት የተሻለው መንገድ አስፈላጊ የሆኑ መዝገቦችን የሚይዙበትን ሁኔታ ለመረዳት ጉብኝቶችን ማካሄድ ይጠበቃል፡፡ ይህም የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱን ለመረዳት (እያንዳንዱ አምራች የተለየ ዘዴ ይኖረዋል) እንዲሁም መዝገቦቹ አዲት መደረግ የሚችሉ እና መግለጫዎቹ ትክክለኛነታቸው መጣራቱን ለማረጋገጥ ይረዳናል፡፡

7ለ.2. ቁልፍ ጉዳዮች

የመዝገብ አያያዝ ሥርዓቶች እና ዘዴዎች ከሌሎች አምራቾች ጋር ሲነፃፀሩ በተለይ በተመሳሳይ ኢንዱስትሪ ከሌሎች አንፃር ዝቅተኛ የመዝገብ አያያዝ ላላቸው መልካም ተሞክሮዎችን ማካፈል እንዲቻል የሚከተሉት ጉዳዮች በእያንዳንዱ ፋብሪካ ውስጥ መመርመር አለባቸው፡፡

ፋብሪካው ስፋት ቢኖረውም በሁሉም አምራቾች የሚያዙ መዝገቦች ተመሳሳይ የአዲት መንገድ መከተል አለባቸው፡፡ አንዳንዶቹ መዝገቦችን ውስብስብ በሆኑ የታክስ እና የመጋዘን አስተዳደር ሶፍትዌር ሲስተሞች መጠቀም የሚችሉ ሲሆን አንዳንዶቹ በኤክሴል እንዲሁም ሌሎች የማኑዋል መዝገቦችን ሊይዙ ይችላሉ ፡፡ ማናቸውም መዝገቦች ያልተያዙ ከሆነ፣ ወይም ከእነዚህ ጉዳዮች አንዳቸውም ያልተሟሉ ከሆነ፣ የሚጣለውን የቅጣት ደረጃ ወይም የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ ለመወሰን ጉዳዩ ወደ ከፍተኛ አመራር ደረጃ መመራት አለበት፡፡

በቀጣዩ ጉብኝት አፈሰሩ ስህተት የነበሩ ነገሮች በሙሉ መስተካከላቸውን እና ግዴታዎች መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ የማጣራት ሥራዎችን ማከናወን አለበት፡፡

በሥራቸው ላይ ከፍተኛ ስኬት ማስመዝገብ የሚፈልጉ ማንኛውም የንግድ ሥራዎች እነዚህን መዝገቦች የራሳቸው የንግድ ፍላጎት አካል አድርገው መያዝ አለባቸው፤ ይህ ካልሆነ ለማደግ፣ ለሠራተኞቻው ክፍያ ለመፈፀም እና በመረጡት ገበያ ውስጥ ቦታ ለማግኘት በቂ የሆነ ትርፍ የሚያስገኝላቸውን የእያንዳንዱን ምርት ዋጋ ለመወሰን አይችሉም፡፡ ከእነዚህ መስፈርቶች አንዳቸውንም ለማሟላት አለመቻል እንዲሁም አዋጁን ለሚደግፉት መመሪያዎች እና የአምራች መመሪያ ተገዢ ያለመሆን ቅጣትን ያስከትላል፡፡

7ለ.3. አንቀጽ 26፡ የቁጥጥር ሁኔታዎች

አንቀጽ 26 የተፈቀደለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች በእያንዳንዱ ፋብሪካ ውስጥ ሊወጣቸው የሚገቡ ግዴታዎችን ይዘረዝራል፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ዝርዝር እያንዳንዱን የአንቀጽ 26 ንዑስ ክፍል በመውሰድ ቁጥጥርን ለማረጋገጥ ምን መፈለግ እንዳለብን እና የሕግ ተገዢነትን እንዴት ማስታረቅ እንዳለብን ማብራሪያዎችን ያቀርባል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቅጂ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ)፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም ጥሬ ዕቃዎችን ለመመዝገብ፣ ክብደታቸውን ለመመዘን፣ ለመቁጠር ወይም ለመለካት እንዲችል በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ መሣሪያዎች እንዲኖሩ እና በሚገባ እንዲጠበቁ የማድረግ፤

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ)፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ተዟዙሮ ለመቃኘት በሚያስችል አግባብ በተናጠል መቀመጥ ያለባቸው ሲሆን ይህም በእያንዳንዱ ቦታ ያሉ ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ተለይተው እንዲቆጠሩ እድል ይሰጣል፡፡ በማምረቻ ቦታው ላይ የማከማቻ ቦታዎችን ንድፍ በማስቀመጥ ምን ያህል የመጨረሻ ምርቶቹ ዓጥኖች ወይም ማሸጊያዎች በእያንዳንዱ ቦታ ሊቀመጡ እንደሚችሉ ይገንዘቡ፡፡ በእያንዳንዱ ቦታ የተቀመጡ ምርቶችን ብዛት በቀላሉ መቁጠር ካልቻሉ (ጥሬ ዕቃዎችንም ቢሆን) ማስታወሻ በመያዝ ግዴታን ለመወጣት የሚያስፈልጉትን ለውጦች ለአምራቹ መደበኛ በሆነ መንገድ ማሳወቅ አለብዎት፡፡ እያንዳንዱ ቦታ የማከማቻ ቦታ ቁጥር (ሀ1፣ ሀ2፣ ሀ3 ወዘተ.) የተሰጠው መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሐ)፡ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የጥሬ ዕቃዎችን ምዝገባ ማካሄድ፣ በተለይም በማምረት ሂደት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፋብሪካው የተረከባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና ግብዓቶች በእነዚህ ቅጾች ላይ መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፡፡ ይህ መከናወን ያለበት መዝገብን የማስታረቅ አስፈላጊ ሥራ ነው፡፡ ዕቃዎችን የመረከብ ሂደት በሙሉ የመረከቢያ ቀን እንዲሁም የዕቃዎቹን ብዛት እና ዓይነት የሚያሳይ መለያ ቁጥር ባለው የማስረከቢያ ሰነድ መከናወን አለበት፡፡ የመጨረሻው በእጅ የሚገኝ ክምችት (Physical Stock Take) ላይ የሚታየውን ብዛት እንደ መለኪያ በመጠቀም ከቀረበው የክምችት ቅጽ አንፃር ሁሉንም ርክክብ መገምገም ይኖርብናል፡፡

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (መ)፡ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማከናወን፣ እና በዚሁ ቅጽ ላይ በፋብሪካው የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና ከፋብሪካው የወጡ ጥሬ ዕቃዎችን መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፡፡

- ይህ የአዲት መከታተያ መዝገብን የሚያስቀጥል ሲሆን ከአንድ የተወሰነ ቦታ መጥተው ከተረከቡ ጥሬ ዕቃዎች ጋር የማስታረቅ ሥራ ሊከናወንበት ይገባል፡፡ ለምሳሌ በመጨረሻው በእጅ ያለ ክምችት ላይ ያሉ የጥሬ ዕቃዎችን እና የመጨረሻ ምርቶችን የክምችት ቁጥር ይገምግሙ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ፣ የቀረቡትን የክምችት ቅጾች እና የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች ይተንትኑ፤ ይህም በክምችት ውስጥ ካሉ ጥሬ ዕቃዎች በአምራቹ ሊመረት የሚችለውን እና ከዚያ ቀን ጀምሮ በምርት ሂደት ጥቅም ላይ የዋለውን መጠን ያሳያል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነዶች ማዕከል ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሠ)፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ ስለሆነም በዚያ ወር የቀረቡትን ዕቃዎች ዋጋ የሚያሳይ የኤክሳይዝ ታክስ ደረሰኝ ለሁሉም ጥቅም ላይ ለዋሉ ፍጆታዎች መዘጋጀት አለበት፡፡ ዋጋውም ለትክክለኛው የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህም ለእያንዳንዱ የምርት ዓይነት ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ዋጋ በትክክል መተንተኑን እና የተገለፀው ዋጋም ሁሉንም የዕቃዎች ዋጋ የሚያጠቃልል መሆኑን ያረጋግጡ፡፡ ምንም ዓይነት ቅናሽ የተደረገ ዋጋ ለኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም ላይ እንዲውል አይፍቀዱ፡፡ በዋነኛው መረጃ (Master Data) እና በይፋዊ የዋጋ ዝርዝር መግለጫ ቅጹ ላይ ያለው ዋጋ ብቻ ለሁሉም የዕቃ ማውጣት ተግባራት ጥቅም ላይ መዋል አለበት፡፡

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (1) (ረ)፡ በኤክሳይዝ ታክስ መመሪያ የሚወጡ እንዲሟሉ የሚጠየቁ ሁኔታዎችን ማሟላት፡፡ አምራቹ አዋጁን ለመደገፍ ለሚወጡ ማናቸውም መመሪያዎች ወይም ደንቦች ተገዢ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ ልኬቶች በሚወሰዱባቸው ሁሉም ቁሳቁስ ላይ ባለቀለም ኮድ ቱቦዎች (colour coded pipes) እና ትክክለኛ የመለኪያ መሣሪያዎች እንዲገጠሙ ማድረግ፡፡

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (3) (ሀ)፡ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ናሙና ከአምራቹ በነፃ የመውሰድ መብት ያለው ሲሆን፣ እነዚህ ናሙናዎች የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሊወገዱ ወይም ለአምራቹ ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

  በእያንዳንዱ ማሽኒያ ውስጥ ትክክለኛው የምርት መጠን መኖሩን ለማረጋገጥ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ናሙናዎችን መውሰድ ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ በአንድ እሽግ ውስጥ ያሉት ሲጋራዎች ቁጥር ከመለያው ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ትክክለኛው የቢራ መጠን ከማሸጊያው ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡

- አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (3) (ለ)፡ የታክስ ባለስልጣኑ አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልባቸውን ናሙናዎች እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ነገር ግን እነዚያ ናሙናዎች ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ ሲሆን የዕቃዎቹን ጥራት ለመፈተሽ ለላቦራቶሪ ምርመራ ብቻ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም የላቦራቶሪ ትንተና መዝገቦችን ያረጋግጡ፡፡ የላቦራቶሪ ትንተና ናሙናዎች ያለ ኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ የተፈቀዱ ሲሆን ለፍጆታነት የዋለ ማንኛውም ምርት ግን የምርቱ ዓይነት ለፍጆታነት ሲሚውልበት ዋጋ የኤክሳይዝ ታክስ ሊከፈልበት ይገባል፡፡

7ለ.4. ማጠቃለያ

ከጥሬ ዕቃዎች የማከማቻ ቦታ ጀምሮ እስከ ማምረት፣ ማሸግ፣ ማከማቸት እና ማስወጣት ድረስ ጥሬ ዕቃዎችን ለመከታተል የሚያስችል ግልፅ የአዲት መከታተያ መዝገብ መኖሩን በማረጋገጥ የሁሉንም የተፈቀደላቸው አምራቾች የመዝገብ አያያዝ ሥርዓትን በተመለከተ ማስታወሻ ይያዙ፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ያስመንትሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ሰምንት፡ የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካዎች እና የአልኮል መጠጥ አምራቾች የአዋጁ አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 2

ክፍል 8ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

8ሀ.1. መግቢያ

ኤቲል አልኮል (ኤታኖል) ከፍተኛ ጥንካሬ ያለውን ጥሬ አልኮል (በተለምዶ ከ96% በላይ) ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል ሲሆን፣ የአልኮል መጠጦች ደግሞ ሙሉ በሙሉ ከተጣራ አልኮል የተዘጋጁ ወይም አልኮል የነበራቸው የፈሉ ምርቶች የተጨመሩባቸው የአልኮል መጠጦች ናቸው::

ኤቲል አልኮል የአልኮል መጠጦችን ከማምረት ሥራ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው የምርት ሂደቶች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል:: ለምሳሌ በሆስፒታሎች ውስጥ ለፅዳት አገልግሎት፤ ለኢንዱስትሪ የማምረት ሂደቶች፤ የመዋቢያ ዕቃዎችን፣ ሽቶዎችን፣ የቤት ውስጥ የፅዳት ዕቃዎችን እና ስክሪን ማፅጃዎችን ለማምረት ያገለግላል::

የአልኮል መጠጦቹ ለመጠጥነት ከሚያገለግል አልኮል ውጪ ለማንኛውም ጥቅም የሚውሉ ከሆነ በመጠጥነት ለሰው አገልግሎት የማይውሉ (denatured) ሆነው መቅረብ ያለባቸው ሲሆን (የኬሚካሎች መጨመር በሚሰጡት ጥቅም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ ለህክምና ዓላማዎች ጥቅም ላይ ካልዋሉ በስተቀር)፣ በዚህ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ ላይጣልባቸው ይችላል::

የሁሉም የአልኮል መጠጦች አመራረትን የተመለከቱ መዝገቦች መያዝ አለባቸው፤ ምክንያቱም የአልኮል መጠጦቹ በመጠጥነት ለሰው አገልግሎት የማይውሉ ሆነው ካልተዘጋጁ በስተቀር ለየትኛውም ጥቅም ቢውሉ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አለበት::

የኤክሳይዝ ታክስ ከፍተኛ ጥንካሬ ባለው ኤቲል አልኮል ላይ የሚጣል ሲሆን የአልኮል መጠጦች በመጠጥነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የታሰቡ በማይሆኑበትም ጊዜ እንኳን መዝገቦች ከምርት ሂደት ጀምሮ በመጠጥነት ለሰው አገልግሎት እንዳይውሉ እስከሚደረጉበት እና እስከመጨረሻ አጠቃቀማቸው ድረስ ግልፅ የአዲት መከታተያ መዝገብ ማሳየት አለባቸው:: አምራቹ አልኮሉ በመጠጥነት ለሰው አገልግሎት እንዳይውል መደረጉን ወይም ከታክስ ነፃ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ከልቻለ የኤክሳይዝ ታክሱን መክፈል አለበት::

በጅምላ የቀረበ ኤቲል አልኮል 10% የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ሲሆን ከአልኮል የተዘጋጁ መጠጦች ግን በፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ላይ 80% የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል::

የፈሳሹ ባህሪ የምርቱን አጠቃላይ ዋጋ የሚቀንሰው በመሆኑ የ10% ከፍያው ዝቅተኛ መሠረት (በሊትር) ይሆናል፡ :

8ሀ.2. የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ስለመጠቀም

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አንቀጽ 27 የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ አጠቃቀምን የሚዘረዝር ሲሆን የአልኮል ማጣሪያ ወይም ማሻሻያ ፋብሪካ ባለቤት በመሆን የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከተሰጠው ሰው ውጪ ማንም ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይም መጠቀም እንደማይችል ይገልፃል::

የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ ከግብርና ጥሬ ዕቃዎች መፍላት/መብላላት ወይም በሦስተኛ ወገን አቅራቢ የተዘጋጀውን ኤቲል አልኮል በማሻሻል (እንደገና በማጣራት) የአልኮል መጠጦችን ለማምረት ጥቅም ላይ ይውላል:: የኤቲል አልኮል ከተለያዩ ማጣፈጫዎች ጋር በማዋሃድ ከፍተኛውን አልኮል እንዲቀንስ ከሚያደርጉት በስተቀር ሌሎች የአልኮል መጠጥ አምራቾች ሁሉ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መጠቀም አለባቸው::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ የተጠበቀ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

8ሀ.3. የአልኮል መጠጦች አመራረት፡ የተለያዩ ዘዴዎች

8ሀ.3.1. ማጣራት

የአልኮል አምራች ማለት ጥሬ ዕቃዎችን በማፍላት የአልኮል መጠጦችን የሚያመርት እንዲሁም ከፍተኛ ጥንካሬ ያላቸውን የአልኮል መጠጦችን ለማምረት የማጣራት ሂደትን የሚያከናውን ሰው ነው::

ሁሉም የማጣራት ሥራዎች የሚጀምሩት በማፍላት/በማብላላት ሂደት (ከቢራ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ) ሲሆን በማስከተልም የፈላው አልኮል በአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲጣራ ይደረጋል::

8ሀ.3.2. ማሻሻል

ማሻሻያ የሚያከናውን ሰው ቀደም ሲል በማፍላት እና ማጣራት ደረጃ ላይ በነበረው የኤቲል አልኮል ላይ ማሻሻያ ("rectification") የሚባል ሂደት ያከናውናል:: ስለሆነም ማሻሻያ ለሚያደርገው ሰው በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግለው ከፍተኛ ጥንካሬ ያለው የኤቲል አልኮሆል ነው::

ማሻሻያ የሚያከናውን ሰው ፈሳሹ በድጋሚ ተጣርቶ እና ወደሚፈለገው የአልኮል ጥንካሬ ለመቀነስ ማሻሻያ ከመደረጉ በፊት ውህድ ወይም ጣዕም ወደ ኤቲል አልኮል ሊያስገባ ይችላል::

የመጨረሻው ምርት በውሃ እና በማጣፈጫዎች የአልኮል መጠኑ እንዲቀንስ (እንዲቀጥን) የተደረገ ከሆነ የማሻሻያ ሥራውን የሚያከናውነው ሰው የአልኮሉ ጥራት በጣም የተሻለ መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻለው ዘንድ አልኮሉን እንደገና የማጣራት (re-distil) ሥራዎችን ለማከናወን የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ይጠቀማል::

8ሀ.3.3. መደባለቅ/ማዋሃድ

የኤቲል አልኮልን የመደባለቅ ሥራ የሚያከናውን ሰው በተለምዶ ዝቅተኛ ጥራት፣ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው የአልኮል መጠጦችን የሚያመርት ነው:: በዚህም መሠረት በፈሳሹ ላይ የሚከናወን የማጣራት ወይም እንደገና የማጣራት ሥራ የለም:: አምራቹቹ ባህሪው ያልተለወጠ አልኮል (ማሻሻያ እንደሚያከናውነው ሰው) ተረክበው ነገር ግን በድጋሚ የማጣራት ሥራን ከመጠቀም ይልቅ የሚፈለገውን የአልኮል ጥንካሬ ለማምጣት ከፍተኛ ጥንካሬ ባለው አልኮል ላይ ሰው ሰራሽ ማጣፈጫዎችን በመጨመር በውሃ የማቅጠን ሥራን ያከናውናሉ::

8ሀ.5. ሕጉ እና ተግባራዊ አፈፃፀሙ

የሚከተለው ሠንጠረዥ በጽሑፍ የሠፈረውን የሕግ ድንጋጌ እና ተግባራዊ አፈፃፀሙን ያመለክታል:-

አንቀጽ	የሕግ ድንጋጌ	ተግባራዊ አፈፃፀም
27(1)	በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ከተሰጠው የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ/አምራች ውጭ ማናቸውም ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይም መጠቀም አይችልም::	የአልኮል መጠጦችን በግል ለመጠቀም በቤት ውስጥ ማምረት ሕገ-ወጥ ተግባር ነው:: የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን የሚጠቀም ማናቸውም ሰው ፈቃድ የተሰጠው መሆን እና ባመረታቸው የአልኮል መጠጦች ላይ የኤክሳይዝ ታክስን መክፈል አለበት::

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

27(2)	የገቢዎች ሚኒስቴር የሚጥላቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ከተፈቀደለት የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ ሌላ ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲይዝ ወይም እንዲጠቀምበት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊፈቅድ ይችላል፡-	የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ ፈቃድ ባልተሰጠው አምራች ሊያዝ የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡-
27(2)(ሀ)	የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ለሽያጭ የሚያመርት ወይም የሚይዝ ሲሆን፤	የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ብቻ የሚያመርት ሰው ሲሆን፣ ይህም ምንም ዓይነት የአልኮል ማጣራት ወይም ማሻሻል ሥራዎችን ሳይጨምር መሣሪያውን ብቻ የማምረት ተግባር ነው፡፡
27(2)(ለ)	መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ለመከራ፣ ለጥናት፣ ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ ሲሆን፤	ዩኒቨርሲቲዎች ወይም የላቦራቶሪ ማዕከላት የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ሊይዙ እና ሊጠቀሙ የሚችሉ ቢሆንም የአልኮል መጠጦችን ግን ማምረት የለባቸውም፡፡
27(2)(ሐ)	የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ከአልኮል መጠጦች ውጭ የሆነ ሌላ ምርት ለማምረት ሲሆን፡፡	በግልፅ የተቀመጠ

ማስታወሻ፡ የአልኮል አምራችነት ፈቃድ ሳይኖራቸው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው ሰዎች ምንም ዓይነት የአልኮል መጠጥ እየተመረተ እንዳልሆነ የሚያሳይ ማስረጃ ለማቅረብ የሚመረቱትን የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያዎች እና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ መዝገብ መያዝ አለባቸው፡፡

8ሀ.6. ማጠቃለያ

የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ አጠቃቀም እና የአልኮል መጠጦች አመራረት በከፍተኛ ሁኔታ ቁጥጥር ይደረግበታል፡ ፡

ይሁን እንጂ በዚህ ሁኔታም ቢሆን የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያው በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ መዝገቦች መያዝ አለባቸው፡፡

ለምሳሌ የታክስ ባለስልጣኑ በየጊዜው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ አምራቾችን መጎብኘት እና መሣሪያዎቹ ለማን እንደተሸጡ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል 8ለ፡ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያዎችን አጠቃቀም እና የአልኮል መጠጦችን የምርት ሂደት ቁጥጥር

8ለ.1. በአልኮል የአመራረት ሂደት ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

የአልኮል መጠጥ አምራቾችን በሚጎበኙበት ጊዜ የአመራረት ሂደቱን በተመለከተ መያዝ አለበት::

አምራቹ የአልኮል መያዣ ታንከሮች ተብለው በሚታወቁት የፈሳሽ መያዣዎች ከሦስተኛ ወገን የጅምላ ኤቲል አልኮል የሚረከብ ከሆነ የሚከተሉትን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡-

- ሙሉ የአቅርቦት ሰንሰለቱን ምንነት መገንዘብ፤
- የአቅራቢዎቻቸውን ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ መያዝ ፤
- የማስረከቢያ ሰነዶች እና ደረሰኞች ቅጂዎችን ማገናዘብና ማረጋገጥ፤
- የማስረከቢያ ሰነዶቹን ዕቃዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ አምራቾች ወጪ ከተደረጉባቸው ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡባቸው ሰነዶች ጋር ማመሳከር::

የጅምላ ኤቲል አልኮል ላይ 10% የኤክሳይዝ ታክስ እና የመጨረሻ ምርቶችን ወደ ገበያ በማቅረብ ላይ ደግሞ 80% የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል አለበት፤ ስለሆነም እነዚህ ሁሉ በትክክል ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

በጥሬ ዕቃነት ጥቅም ላይ በሚውል የጅምላ አልኮል ላይ ለኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ የተፈቀደ የሚቀናነስ ሂሳብ የለም::

ማስታረቅ የሚያስፈልጋቸው መካከል፡

- ገቢ የተደረገ የጅምላ አልኮል፤
- ገቢ የተደረጉ ማጣፈጫዎች/ዕጽዋት (በድጋሚ የማጣራት ሥራ ከመከናወኑ በፊት ጣዕም ለመጨመር የሚያገለግሉ ፍራፍሬ እና አትክልት) በሙሉ፤
- የጅምላ ፈሳሹን የአልኮል ጥንካሬ እና የመጨረሻ ምርቱን የአልኮል ጥንካሬ ማገናዘብ::

96% የአልኮል መጠን (Alcohol by Volume abv) ያለው (abv የተለመደው የአልኮል ጥንካሬ ማጣቀሻ ነው) 100 ሊትር አልኮል ላይ 100 ሊትር ውሃ ቢጨምሩ 48% የአልኮል መጠን ያለው 200 ሊትር ምርት ሊያገኙ ይገባል:: ስለዚህ ተመሳሳይ መጠን ያለው ውሃ ወደ አልኮል መጠጦች ሲያስገቡ የአልኮል ጥንካሬን በግማሽ ይቀንሳሉ:: በዚህም መሠረት የሚሸጡትን እያንዳንዱን የአልኮል ምርት ዓይነት እንዴት እንደሚያመርቱት ሂደቱን ማወቅ ያስፈልጋል::

እንዲሁም የጅምላ ኤቲል አልኮል በማንኛውም መንገድ ወደ ሌሎች ደንኞች ወጪ የተደረገበትን ሁኔታ በመተንተን ሁሉም ደንበኞች የተፈቀደላቸው ፋብሪካዎች መሆናቸውን ያረጋግጡ:: የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን የሚያመርት ሰው መሣሪያውን ለማን እንዳመረተ ለማጣራት እና ለተፈቀደው ከታክስ ነፃ የሆነ አገልግሎት ጥቅም ላይ መዋል አለመዋሉን ለማረጋገጥ በየጊዜው በጉብኝት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል::

8ለ.2. ማጠቃለያ

የአልኮል መጠጦች ምርት ቁጥጥር የሚያስፈልገው መስክ ነው:: ምክንያቱም በመጨረሻ ምርቶች ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ከፍተኛ በመሆኑ እንዲሁም የአልኮል መጠጦችን ለማምረት እንደ ጥሬ ዕቃ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

የሚያገለግለው የጅምላ ኤቲል አልኮል ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል ዘጠኝ፡ የምርት ሂደት እና የሂሳብ አያያዝ

ክፍል 9ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

9ሀ.1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚዘጋጁት ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን ሲሆን እነዚህም ከውጭ ሀገር የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያዊ አቅራቢ የሚገኙ ናቸው፡፡ አቅራቢውም ዕቃዎቹን አስመጥቶ ወይም በኢትዮጵያ ውስጥ ከተሠሩበት ቦታ ከሌላ አቅራቢ ገዝቶ ሊሆን ይችላል፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰሮች ማንኛውንም የምርት ደረጃ ልዩነት ጥሬ ዕቃዎችን ከመረከብ ጀምሮ ለመከታተል እንዲቻል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በማምረቻ ቦታው በአካል ተገኝቶ ለመፈተሽ እንዲቻል የምርት ሂደቱን ሙሉ የአዲት መከታተያ መዝገብ ለማዘጋጀት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳንድ የምርት ሂደቶች ከሌሎቹ ይልቅ ውስብስብ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የቢራ አመራረት ካርቦን ያላቸው ለስላሳ መጠጦችን ከማምረት የበለጠ ውስብስብ ነው፡፡

9ሀ.2. የአዲት መከታተያ መዝገብ

የአዲት መከታተያ መዝገብ ለጠንካራ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥርዓት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡-

ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጥሬ ዕቃዎችን መረዳት

↓

የምርት ሂደቱን መረዳት

↓

የPackaging የማሸግ ሂደቱን መረዳት

ከዚህ በመነሳት የዕቃዎችን ዋጋ፣ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ኪሳራዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠበቁባቸውን ቦታዎች ማግኘት እና እየተስተናገዱ ያሉትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ምንነት መረዳት አለብን ::

9ሀ.3. መዝገቦች

ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጣቸው አምራቾች በተለያዩ መንገዶች እና በተለያዩ ቅርፆች መዝገቦችን ይይዛሉ፡፡ ምንም እንኳን ወርሃዊ ቅጾችን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም የቀረበው መረጃ እንዴት እንደሚገኝ የሚያሳዩ መዝገቦችንም መያዝ አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቢ.ታ መዛግብትና ሰነዶች ማ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

መዝገቦች የሚከተሉትን መረጃዎች በሚያሳይ መልኩ መያዝ አለባቸው፡-

- የጥሬ ዕቃዎች አቀባበል እና አጠቃቀም (እና ማናቸውም ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎች በሀገር ውስጥ የሚመረቱ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ)፤ እና
- በአንድ የተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ የምርት ሂደቶችን በተመለከተ ለእያንዳንዱ የተከናወነ የምርት ሂደት ልዩ ቁጥሮች እና የሚመረቱ መጠኖች የተመደበላቸው መሆን አለባቸው፡፡

ለመጠጦች በጅምላ የቀረበው ፈሳሽ ለማሸጊያ ሥራዎች ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ የሚከተሉትን የሚያሳይ ተጨማሪ መዝገብ መያዝ አለበት፡-

- ከማሸጊያ ሥራው በፊት በጅምላ ኮንቴይነሩ ውስጥ ያለውን መጠን፤
- በማሸጉ ሥራ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ኮንቴይነሮች መጠን እና ቁጥር፤ እና
- ከማሸጊያው ሂደት በኋላ በኮንቴይነሩ ውስጥ የተረፈ ማንኛውም ፈሳሽ፡፡

9ሀ.4. የሕግ አግባብ

አንቀጽ 26 እና 35

አንቀጽ 26 ከላይ ባለው የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር በሚለው ክፍል ውስጥ በስፋት የተዳሰሰ ሲሆን ይህም በፋብሪካ ውስጥ ያሉ አንቅስቃሴዎችን በሙሉ የሚያሳዩ ጠንካራ መዝገቦችን በመያዝ ረገድ የአምራቹን ግዴታዎች ያብራራል፡፡

አንቀጽ 35 የተፈቀደላቸው አምራቾች በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ወይም የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ በተደነገገው መሠረት መዝገቦችን እንዲይዙ እና መዝገቦቹንም በታክስ አስተዳደር አዋጁ ለተገለፀው ጊዜ እና በተገለፀው አኳኋን መያዝ እንዳለባቸው ያስገድዳል፡፡

9ሀ.5. ለታክስ ባለስልጣኑ የሚቀርቡ የፀደቁ ቅጾች

የተፈቀደለት አምራች ጥሬ ዕቃዎችን ከመረከብ ጀምሮ በምርት እና በማሸግ ሂደቶች፣ በማከማቸት እና በስተመጨረሻም ዕቃዎች ከፋብሪካው ወጥተው የሚረከቡበትን ሁኔታ ቢታመለከተ ግልፅ የሆነ የአዲት መከታተያ የሚያቀርቡ መዝገቦችን/ሰነዶችን መያዝ አለበት፡፡

ይህም የአዲት መከታተያ (Audit Trail) ይባላል፤ ምክንያቱም እነዚህን ሁሉ ተግባራት የሚያሳይ ግልፅ የሆነ መዝገብ መኖር ያለበት ሲሆን ይህም በማስረከቢያ ሰነዶች፣ በደረሰኞች፣ እና የማምረቻ ቦታ ላይ በተያዙ መዝገቦች የተደገፈ መሆን አለበት፡፡

በዚህ የአዲት መከታተያ መንገድ ውስጥ ጥሰት ከተገኘ ቅጣቶች ተፈፃሚ መሆን ያለባቸው ሲሆን ሊቆጠሩ በማይችሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል አለበት፡፡

ለታክስ ባለስልጣኑ አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሁሉንም መዝገቦችን መያዝ እና ማቅረብ የአምራቹ ግዴታ ነው፡፡

የታክስ ባለስልጣኑ በተፈቀደለት አምራች ተሞልተው በየወሩ መቅረብ ያለባቸውን የፀደቁ ቅጾች ያዘጋጃል፡፡

እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ወርሃዊ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ (ከላይ በክፍል 5 ተዘርዝሯል)፤
- የተመላሽ ቅጽ (ከታች በክፍል 16 ተዘርዝሯል)፤

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቢሮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

- የዋጋ ዝርዝር ቅጽ::

ከተመላሽ ገንዘብ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ እና የዋጋ ዝርዝሮች ጋር የተያያዙ ቅጾች ከዚህ በታች ባሉት ተዛማጅ ክፍሎች ይሸፈናሉ:: የእቃ ቆጠራ ቅጽ እና የጥሬ ዕቃዎች ቅጽ በዚህ ክፍል ተዘርዝረዋል::

9ሀ.6. ወርሃዊ የዕቃ ቆጠራ ቅጽ

ወርሃዊ የዕቃ ቆጠራ ቅጹ የታክስ ባለስልጣኑ በመግለጫ የቀረበውን የመጨረሻ ምርት መጠን ከዕቃዎች ወደ ፋብሪካ መግባት ጀምሮ እስከ የምርት ሂደት እና ከፋብሪካ መውጣት ድረስ ያለውን ሂደት መሠረት አድርጎ ክትትል ለማድረግ ያስችላል::

በዚህ ቅጽ ላይ ያለውን ዝርዝር በወሩ መጨረሻ ከሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በሀገር ውስጥ በቀረቡ እና ከውጭ በገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ከጉምሩክ ኮሚሽን ከተሰበሰበው መረጃ ጋር ማስታረቅ ያስፈልጋል::

ወርሃዊ የቆጠራ ቅጹ በእያንዳንዱ ወር ውስጥ በእያንዳንዱ ፋብሪካ ያሉትን እንቅስቃሴዎች አጠቃሎ የሚይዝ ሲሆን በሚቀጥለው ወር መጨረሻ መቅረብ አለበት (ስለዚህ የሚያዚያ የቆጠራ ቅጽ እስከ ግንቦት 30 ቀን ድረስ መቅረብ አለበት)::

እንዲሁም ከፋብሪካ ዕቃዎችን የማውጣት ሁሉንም እንቅስቃሴዎች በተመለከተ ዕለታዊ ማስታወሻ የመመዝገብ ግዴታ የተቀመጠ ሲሆን እነዚህ ዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ መዝገቦች ከወርሃዊ ቅጹ ጋር የማስታረቅ ሥራ ሊከናወንባቸው ይገባል:: ይህ ዕለታዊ መዝገብ መቅረብ አያስፈልገውም፤ ነገር ግን ለማረጋገጫነት መቀመጥ አለበት::

9ሀ.7. ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር

እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በሥሩ ባሉ የተፈቀደላቸው ፋብሪካዎች የተመረቱትን ምርቶች ለእንዳንዱ የምርት ነጠላ መጠን እና የምርት ዓይነት የተመደበውን ዋጋ መሠረት በማድረግ በዋጋ ላይ የተመሠረተ የኤክሳይዝ ታክስን ማስላት አለበት::

እያንዳንዱ አምራች የኤክሳይዝ ታክሱን ለማስላት የሚጠቀምበትን ዋጋ የሚያሳይ የዋጋ ዝርዝር በየወሩ ማቅረብ አለበት::

ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ አምራች እየተመረቱ ያሉትን ሁሉንም የምርት ዓይነቶች ማሳወቂያም ይሆናል:: በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ዋጋ በቀጣዩ ወር እያንዳንዱ የምርት ዓይነት እና ነጠላ መጠን የሚሸጥበትን ዋጋ የሚገልጽ ወይም የሚያሳይ መሆን አለበት::

በዋጋ ዝርዝሩ ላይ ከቀረበው በላይ በሆነ ዋጋ ሽያጭ መከናወኑን የታክስ ባለስልጣኑ ከደረሰበት በኤክሳይዝ ታክሱ ላይ ለታየው ልዩነት የኤክሳይዝ ታክሱ እንዲከፈል ይጠይቃል::

ሽያጩ የተከናወነበት ዋጋ ዝቅ ያለ ከሆነ የስሌት መሠረቱ በዋጋ ዝርዝሩ ላይ የተጠቀሰው ዋጋ ይሆናል::

9ሀ.8. በአምራቹ መያዝ ያለባቸው ነገር ግን ለታክስ ባለስልጣኑ መቅረብ የማይገደዱ መዝገቦች/ሰነዶች

አብዛኞቹ መዝገቦች በአርግጥ በየወሩ መቅረብ አያስፈልጋቸውም፤ ነገር ግን የተወሰኑ ዝርዝር መረጃዎች የመዝገብ አያያዙ መስፈርቶች አንድ አካል ሆነው መያዝ አለባቸው::

እነዚህ መዝገቦች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ አይሰጡም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ አምራች የሚጠየቁ መረጃዎችን ያካተተ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

መዝገብ መያዝ አለበት::

የሚጠየቁ መረጃዎች እና መያዝ ያለባቸው መዝገቦች ለሁሉም አምራቾች በሚሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተሰጠው አምራች ማኑዋል ውስጥ በዝርዝር የሚቀመጡ ይሆናል::

9ሀ.9. የጥሬ ዕቃዎች መዝገብ

የጥሬ ዕቃዎች መዝገብ በእያንዳንዱ ፋብሪካ የሚገባውን እና ወደ ምርት የሚገባውን የእያንዳንዱን ጥሬ እቃ መጠን ያሳያል::

ይህም ከመጨረሻው ምርት መጠን አንፃር በጥሬ ዕቃው ላይ ትንተና በሚካሄድበት ጊዜ እገዛ የሚያደርግ ሲሆን ይህም በኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ውስጥ በስፋት ተዘርዝሮ ቀርቧል::

ለእያንዳንዱ ዋና ጥሬ ዕቃ ራሱን የቻለ መዝገብ ሊኖር የሚገባ ሲሆን መዝገቡም የሚከተሉትን ማሳየት አለበት፡
-

- ወደ ፋብሪካው የገባበትን ቀን፤
- የገባው ዕቃ መጠን፤
- ከውጭ ለገቡ ጥሬ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የገቡበት ሰነድ፣ ወይም በሀገር ውስጥ ለተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች የማስረከቢያ ሰነድ/ደረሰኝ ማመሳከሪያ፤
- ዕቃዎቹ የተከማቹበት ቦታ፤
- ተከማችተው ከነበረበት ቦታ ወደ ማምረቻው የወጡበት ቀን፤
- ለአንድ የተወሰነ የምርት ሂደት ማጣቀሻ መቀመጥ አለበት::

በተጨማሪም ማናቸውም የጠፉ ወይም የተበላሹ ጥሬ ዕቃዎች፣ የጠፉበትን ምክንያት እና መጠናቸውን እንዲሁም መጥፋታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ መመዝገብ አለበት::

9ሀ.10. በሀገር ውስጥ የተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች (ገብስ፣ ወይን) የሚመረት ቢራ እና ወይን ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ቅናሽ አለ::

9ሀ.11. ዕቃዎች የተመረቱበትን ቦታ የሚያሳይ ማስረጃ

ከተመረተበት ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎችን በተመለከተ ዕቃዎቹ ከተገለፀው ሀገር የመጡ ስለመሆናቸው ማስረጃ ሊቀርብበት የሚገባ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ የጉምሩክ ቀረጥ ሂደት አለ::

በተቻለ መጠን በሀገር ውስጥ ከሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች (Local Raw Materials LRM) የተሠራ የቢራ እና ወይን ላይ የቀነሰ የኤክሳይዝ ታክስ መጠን የሚከፍሉ የተፈቀደላቸው አምራቾችን በተመለከተ ያንን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት::

ለምሳሌ፡-

- ከአቅራቢው የተሰጡ ደረሰኞች፤
- ዕቃዎቹ ከተላኩበት ቦታ የተሰጡ የማስረከቢያ ሰነዶች::

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች እንደማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ሁሉ ጥብቅ

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፤ ምክንያቱም መገኛ ቦታቸው የሚከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ይወስነዋል፡
፡

ጥሬ ዕቃዎቹ በሀገር ውስጥ የተመረቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ በማይቻልበት ጊዜ ሙሉ የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል አለበት፡

9ሀ.12. የላቦራቶሪ ናሙናዎች

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ (3) የሚከተሉትን ይፈቅዳል፡-

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለላቦራቶሪ ምርመራ ናሙናዎችን ያለ ክፍያ ወይም ያለምንም የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መውሰድ ይችላል፤ እና

- የተፈቀደለት አምራች ጥራትን ለማረጋገጥ ዓላማዎች ለላቦራቶሪ ምርመራ ናሙናዎችን መውሰድ ይችላል::

ማስታወሻ፡ ለፍጆታ የማይውሉ የላቦራቶሪ ናሙናዎች ብቻ የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈል ሊፈቀዱ ይችላሉ::

ለደንበኞች የሚቀርቡ ማናቸውም የጣም ሙከራዎች ወይም ናሙናዎች ጥቅም ላይ በሚውሉ ወይም ከፋብሪካ በሚወጡ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸው መሆን አለባቸው::

ስለዚህ ለላቦራቶሪ ምርመራ የወጡ ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች መዝገብ ሚከተሉትን በሚያሳይ መልኩ መቀመጥ አለበት፡-

- ከፋብሪካ የወጡበትን ቀን፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት እና መጠን፤
- የምርመራውን ዓይነት፤
- ከፋብሪካው የሚወጡ ከሆነ የተላኩበትን የመዳረሻ ቦታ (እንዲሁም የማስረከቢያ ሰነድ መቀመጥ አለበት)::

9ሀ.13. በምርት ሂደት ላይ የሚደርስ የብክነት/ጉድለት/ብልሽት መዝገብ

በፋብሪካው ውስጥ በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ላይ ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የተከሰቱ ሁሉንም ብክነቶች/ጉድለቶች የሚያሳይ የብክነት/ብልሽት መዝገብ መቀመጥ አለበት:: ታክሳቸው ያልተከፈለ ማናቸውም ዓይነት ጉድለቶች/ብልሽቶች መካተት የለባቸውም፤ ምክንያቱም እነዚህ ተመላሽ አይደረጉም:: ታክሱ የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ያጋጠሙ ውድመቶች ማስረጃ ሲቀርብላቸው ብቻ ተመላሽ ሊደረጉ ይችላሉ::

የብክነት/ጉድለት መዝገቡ የሚከተሉትን ማሳየት አለበት፡-

- ውድመቱ ያጋጠመበትን ቀን፤
- የተበላሹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ዓይነት እና መጠን፤
- የውድመቱ ምክንያት፤
- የዚህ ዓይነቱ ውድመት ለወደፊቱ እንዲቀንስ ለማድረግ የሚወሰድ እርምጃዎች::

9ሀ.14. ዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ ሒሳብ መዝገብ



የታክስ ማስታወቂያው በሚቀጥለው ወር እስከሚቀርብ ድረስ ዕቃዎች ከፋብሪካ እየወጡ ባሉበት ወር የኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈል በመሆኑ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈለው "የክፍያ ስምምነት" ተብሎ በሚታወቀው መሠረት ነው - ክፍያውም እስከ ክፍያው ቀን ድረስ እንዲዘገይ የኤክሳይዝ ህጉ ይፈቅዳል::

ይህ ማለት ዕቃዎች በግንቦት 1 ከተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች ሊወጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን በዕቃዎቹ ላይ የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ እስከ ሰኔ 30 ድረስ ላይከፈል ይችላል:: ስለዚህ ዕቃዎቹ ለታክስ ባለስልጣኑክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ገበያ ላይ ይውላሉ፣ ብሎም ለሽያጭ እና ለፍጆታ ይውላሉ::

በአንድ ወር ውስጥ ከፋብሪካ የወጡ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ በአንድ የማስታወቂያ ቅጽ መቅረብ ያለበት በመሆኑ በዕቃ አወጣጡ ላይ ግልፅ የአዲት መከታተያ መንገድ መኖሩን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች ለእያንዳንዱ የተፈቀደለት የማምረቻ/የማከማቻ ቦታ ዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ ሒሳብ መዝገብ መያዝ አለበት::

በወሩ ውስጥ ለእያንዳንዱ የሥራ ቀን የሚከተለው መረጃ መቀመጥ አለበት:-

ቀን	የምርት ዓይነቱ ስም	ነጠላ መጠን	የመጠንብዛት	ለኤክሳይዝ ታክሱ የሚወሰደው ዋጋ	የደረሰኝ ቁጥር	የማስረከቢያ ሰነድ ማጣቀሻ ቁጥር	የኤክሳይዝ ታክስ መጠን

የተለየ ዋጋ ወይም የተለየ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ያለውን እንዳንዱ የምርት ዓይነት በተለየ መስመር ላይ መጻፍ አስፈላጊ ነው::

ይህ ትክክለኛ ክትትል እንዲኖር ለማስቻል የደረሰኝ ቁጥር እና የማስረከቢያ ሰነዱን በማጣቀስ ከፋብሪካው የወጡትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት ብዛት ያሳያል:: ይህም በእያንዳንዱ ዕቃ አወጣጥ፣ ለእንቅስቃሴው በተሰጠ የማስረከቢያ ሰነድ እና ለእያንዳንዱ ርክክብ በተቆረጠው ደረሰኝ መካከል ግንኙነትን ይፈጥራል:: በተጨማሪም የተፈቀደላቸው አምራቾች ያልሆኑ ነገር ግን የተፈቀደላቸው ፋብሪካዎች ደንበኞች የሆኑ የጅምላ ሻጮች እና የችርቻሮ ነጋዴዎች ላይ ፍተሻ እንዲያደርጉ ሌሎች ቡድኖችን መጠየቅ ስለምንችል ይህ ቢታክስ ባለስልጣን ከታክስ ባለዲረቦቻችን ጋር በቅርበት የመሥራት ዕድልን ይሰጣል:: ይህም ትክክለኛው ዋጋ መከፈሉን እና የተረከቡ ዕቃዎችን መጠን ለማረጋገጥ የማስረከቢያ ሰነዶችን እና ደረሰኞችን የማረጋገጥ ሥራ ማከናወን ያስችላል::

እነዚህም በአንድ ላይ በኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያው ላይ ከተገለፀው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ጋር መጣጣም ይኖርባቸዋል::

9ሀ.15. በተፈቀደለት አምራች እንዲያዙ የሚፈለጉ መዝገቦች ማጠቃለያ

በኤክሳይዝ ታክስ አፈሰሩ ሙሉ አዲት መከናወን እንዲችል በሀገር ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች የሚከተሉትን መዝገቦች መያዝ አለበት:-

የመዝገብ ዓይነት	**የአዲት ሠንሰለት**
የጥሬ ዕቃዎች መረከቢያ(GRN)	ደረሰኝ፣ የክፍያ ማረጋገጫ፣ ለሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱበት ቦታ ማረጋገጫ፣ የመቀበያ ማረጋገጫ (የዕቃዎቹ ማስረከቢያ ሰነድ)::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ከውጭ ሀገር ለሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች (የጅምላ ኤቲል አልኮል፣ ስኳር እና የትንባሆ ቅጠል)	ሕጋዊ የማስመጣት እና የጉምሩክ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማረጋገጫ፤ መጠኑን እና የተረከበውን ዕቃ የሚያሳይ የማስረከቢያ ሰነድ (ከጉምሩክ የገቢ ዕቃዎች ክሊራንስ መረጃ ጋር መጣጣም ያለበት)።
የጥሬ ዕቃዎች አጠቃቀም	በእያንዳንዱ የምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን ዓይነት እና መጠን የሚያሳዩ መዝገቦች።
በየአንዳንዱ ዙር የሚከናወኑ የምርት ሂደቶች	ከተመረቱ ምርቶች ብዛት እና ከምርት ዓይነት ዝርዝር መረጃዎች ጋር ተከታታይ የምርት ሂደት ቁጥሮች።
የጥሬ ዕቃ ንፅፅር መዝገብ	የጥሬ ዕቃዎች ዓይነት እና መጠን እንዲሁም ከመጨረሻው ምርት አንፃር የምርቱን ውጤት የሚያሳይ መዝገብ።
የማሽኒያ መዝገቦች	የኮንቴይነሮችን ብዛት፣ የኮንቴይሩን መጠን (የመያዝ አቅም)፣ ጥቅም ላይ የዋሉ የጅምላ ፈሳሾችን የሚያሳዩ መዝገቦች።
የአልኮል ጥንካሬ	የአልኮል ጥንካሬ ንባቦችን (የመለኪያ መሣሪያ ንባብ) የሚያሳይ መዝገብ (ከ7% በላይ የአልኮል መጠን ያላቸው የተወሰኑ ምርቶች ከፍ ያለ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን አላቸው)።

ያለቀለት ምርት(Stock) መዝገቦች	የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት በጠርሙሶች/ቆርቆሮዎች/ከረጢቶች ወዘተ. ከታሸገ በኋላ ክምችቱን እና በመጋዘኑ ውስጥ የተከማቸበትን ቦታ ይመዝግቡ።
የዕቃዎች ዋጋ	አምራቾች እያንዳንዱ የምርት ዓይነት ዋጋ እንዴት እንደሚሰላ መዝግበው መያዝ አለባቸው። የጥሬ ዕቃዎች ወጪ፣ የምርት ወዘተ.
ሽያጮች	አምራቾች የተቀበሏቸውን የግዢ መጠየቂያዎች፣ ደረሰኞች እና የማስረከቢያ ሰነዶችን መዝገብ መያዝ አለባቸው።
ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ጥቅም ላይ ሚውል ዋጋ	ይህ ለነጠላ ዋጋ እና ለምርት ዓይነት በየወሩ መስተካከል አለበት።
ደንበኞች እና አቅራቢዎች	አምራቾች የሁሉንም ደንበኞች እና አቅራቢዎች እንዲሁም የሽያጭ እና የማስረከቢያ መረጃዎችን መዝገቦች መያዝ አለባቸው።
ብክነት/ጉድለት/ብልሽት	በፋብሪካው ውስጥ ያጋጠሙ ሁሉም ውድመቶች እና ብልሽቶች ተመዝግበው መቀመጥ እና መብራራት አለባቸው።
ዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ ሒሳብ	ይህ በየዕለቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከፋብሪካው የማውጣት እንቅስቃሴዎችን በሙሉ የሚያሳይ እና ከማስረከቢያ ሰነዶች እና ደረሰኞች ጋር የተገናኘ ዕለታዊ መዝገብ ሲሆን ይህም የዕቃዎቹን መጠን፣ ዋጋ እና የመድረሻ ቦታ ለመመዝገብ እና ከቀረበው የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ጋር ለማስታረቅ ያስችላል።
ወርሃዊ የስቶክ ቅጽ	በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ሁሉም አምራቾች የክምችት መዝገብ ማቅረብ አለባቸው።
ወደ ውጭ የተላከበት ማረጋገጫ	ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ ውጭ ከተላኩ ወደ ውጭ የመላኪያ ሰነዶቹ እና ወደ ውጭ መላካቸውን የሚያሳዩ ማረጋገጫዎች መያዝ አለባቸው።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁጥር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል 9ለ፡ የምርት ሂደት ቁጥጥር እና የመዝገብ አያያዝ

9ለ.1. መግቢያ

ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራቾች ለራሳቸው የንግድ መስፈርቶች የሁሉንም ግዢዎች፣ የምርት ሂደቶች እና ሽያጮች መዝገቦችን መያዝ አለባቸው። ያለዚህ መሠረታዊ መስፈርት የትኛውም ንግድ ውጤታማ በሆነ መንገድ መሥራት አይችልም።

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ እነዚህ መዝገቦች በግልፅ መነበብ እና አዲት መደረግ በሚችሉበት አኳኋን እንዲያዙ ያስገድዳል።

9ለ.2. የመዝገብ አያያዝ ቁጥጥር

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደለትን ፋብሪካ ለመጎብኘት በሚገኙበት ጊዜ ሁሉም አስፈላጊ መዝገቦች ግልፅ በሆነ መንገድ መያዛቸውን እና ሁሉም በአንድ ላይ ሲቀመጡ ጥሬ ዕቃዎቹን ከመቀበል ጀምሮ በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ ያለው የዕቃዎች ፍሰት መተንተን ተገቢ ነው።

አንዳንድ መዝገቦች እንዴት እንደሚገኙ ካልተረዱ አምራቹን *በመጠየቅ* እና በግልፅ መረዳት እንዲቻል ማስታወሻ በመያዝ ሁሉንም የመዝገቦቹን መግለጫዎች በማስታወሻዎች ፋይል ውስጥ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡
፡

መዝገቦቹን እና የሚያዙበትን መንገድ እና አሰራር በበቂ ሁኔታ መረዳት ያስፈልጋል ካልሆነ ግን ማንኛውም በመዝገቦቹ ላይ የሚደረግ ማረጋገጫ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ስለሆነም በመዝገቦቹ ውስጥ የተያዙትን መረጃዎች መተንተን ከመጀመርዎ በፊት ጥሬ ዕቃዎችን ከመቀበል ጀምሮ የመጨረሻ ምርቶችን እስከ ማስረከብ ድረስ ያለው አጠቃላይ ሂደት/የአዲት መከታተያ መንገድ ላይ ቅኝት ማካሄድ ተገቢ ነው።

ጥሬ ዕቃዎችን መቀበል ⟹ በተገቢው የማከማቻ ቦታ ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን ማከማቸት/ማስቀመጥ ⟹ ለምርት የሚውሉትን ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ምርት ሂደት ማስገባት ⟹ በምርት ሂደት ውስጥ የሚቆዩበት ጊዜ ⟹ የተመረተው የምርት ዓይነት ⟹ የምርት ሂደት ወደ ማሸግ ሂደት ⟹ ማሸጊያዎች ወደ መያዣዎች ⟹ በሂደቱ ያጋጠሙ ጉድለቶች (ዝቅተኛ መሆን አለባቸው) ⟹ መያዣዎች/ማሸጊያዎች ወደ መጨረሻ የማከማቻ ቦታዎች ⟹ ማዘዣዎችን (መጠየቂያዎችን) መቀበል ⟹ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ማውጣት እና የማስረከቢያ ሰነዶች ⟹ ደረሰኞችን ለደንበኞች መስጠት ⟹ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት ⟹ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ⟹ ያለኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ አለመውጣታቸውን የሚያሳይ ማረጋገጫ።

ተገቢውን ዕቃ መረከባቸውን ከደንበኞቻቸው ለማረጋገጥ እንዲቻል ማስታወሻዎችን ይያዙ፤ የማስረከቢያ ሰነዶችን/ደረሰኞችን ኮፒ ይውሰዱ። ሁሉም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች እና ዕቃዎችን ከፋብሪካ የማውጣት ተግባራት በዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ ሒሳብ ውስጥ ተመዝግበው መገኘት አለባቸው፤ ስለዚህም ይህንን ከቀናት ተግባራት ከሚወሰድ ናሙና ጋር ያስታርቁ።

9ለ.3. መዝገቦች እንዴት መያዝ አለባቸው?

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ቢሮ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

አምራቾች እነዚህን ሁሉ መዝገቦች ቀድሞውኑ ይዘው የቆዩ ሊሆኑ ይገባል፤ አለበለዚያ ዘላቂነት ያለው ንግድ ማከናወን አይችሉም:: ይሁን እንጂ እያንዳንዱ አምራች መዝገቦቹን የሚይዝበት ቅርፅ መጠነኛ ልዩነት ይኖረዋል፡ : መልቲናሽናል ኮርፖሬሽኖች ረቀቅ ያሉ የሶፍትዌር ሥርዓቶች የሚኖራቸው ሲሆን አነስተኛ አምራቾች ግን አሁንም ድረስ የወረቀት መዝገብ ሊኖራቸው ይችላል:: የአዲት መከታተያ መንገዱ እስከተጠበቀ እና ሊታረቅ የሚችል እስከሆነ ድረስ ሁለቱም መንገድ ተቀባይነት ይኖረዋል::

9ለ.4. ማጠቃለያ

በአቅርቦት ሠንሰለት እና የአሠራር ሂደቶች ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን እርምጃ የተመለከቱ መዝገቦች መያዝ አለባቸው::

እያንዳንዱ አምራች የራሱን አሠራር የሚከተል በመሆኑ መዝገቦቹ ለአምራቹ በሚስማማ መልኩ በማንኛውም መልክ ሊያዙ ይችላሉ፤ ነገር ግን በአግባቡ መያዝ፣ በግልፅ ሊነበቡ የሚችሉ መሆን እንዲሁም የተሟላ እና ግልፅ የሆነ የአዲት መከታተያ መንገድ መፍጠር አለባቸው::

ከማረጋገጫ ጉብኝቶች እና አጠቃላይ የታክስ አዲቶች የተሰበሰበ መረጃ ወደ ዳታ ዌርሃውስ ውስጥ መግባት እና በራስ ታክስ ስሌት የቀረቡ የታክስ ማስታወቂያዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ መተንተን አለበት::

የትንታኔ ውጤቶች ላይ በአስተዳደር ደረጃ ውይይት መደረግ እና በተገቢው ጊዜም የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ስምምነት ላይ መደረስ አለበት::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ሰነድ አያያዝና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ዓሥር፡ ብክነት/ጉድለት/በልሽቶች

ክፍል 10ሀ፡ መግቢያ፣ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

10ሀ.1. መግቢያ

የሀገር ውስጥ ኤክሳይስ ታክስ በኢትዮጵያ የተመረቱ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለፍጆታ የሚውሉ ምርቶች ላይ የተጣለ ታክስ ነው። በፋብሪካ የሥራ ከባቢ ላይ ብክነት/ጉድለት የሚያጋጥም ክስተት ነው። ስለሆነም ከማምረት ሥራ ተፈጥሮ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የሚከሰቱ ብክነት እና ጉድለቶች በአጥጋቢ ሁኔታ መብራራት እስከቻሉ ድረስ ኤክሳይስ ታክስ አይከፈልባቸውም። ለምሳሌ የቢራ ምርት ሂደት ላይ ቢራ ጠርሙሶች ቢሰበሩና ምርቱ ቢባክን አጥጋቢ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስ ከኤክሳይስ ታክስ ክፍያ ማካካስ ይቻላል።

10ሀ.2. ሕጉ፡ አንቀጽ 28

የኤክስሳይስ ታክስ አዋጅ በአንቀፅ 28 ላይ እንዳስቀመጠው፣ የተፈቀደለት አምራች የታክስ ባለስልጣኑን በሚያረካ አኳኋን በፋብሪካው የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ተመርቷል በተባለው እና ሊመረት ይችላል ተብሎ በሚታመነው መካከል ያለውን ዕቃ ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ እንዳደረገ ይቆጠራል:: ይህም ማለት ብክነቱን/ጉድለቱን በተመለከተ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት።

የተፈቀደለት አምራች በትክክል ባመረተው እና የተመረተ ዕቃ በሚመዘገብበት ሰነድ ላይ በተመዘገበው መካከል ልዩነት መኖሩን ያወቀ እንደሆነ፣ ይህንኑ ወዲያውኑ ለገቢዎች ሚኒስቴር ማስታወቅ አለበት። ይህም የሚከናወነው በወርሃዊ የክምችት/ስቶክ ቅፅ ላይ መሆን ይኖርበታል። አምራቹ ይህን ለታክስ ባለስልጣኑ ሳያሳውቅ ከቀረ ወይም የብክነት መዝገብ ሳይዝ ከቀረ፣ በምርመራ ወቅት ለተገኙ የክምችት ጉድለቶች የኤክሳይስ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት።

10ሀ.3. ሕጉ፡ ቅጣቶች

የኤክሳይስ ታክስ አዋጁ አንቀፅ 38 ንዑስ አንቀፅ (3) እንዳስቀመጠው፣ ማናቸውም ዕቃዎች ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ እንደተደረጉ በሚቆጠርበት ሁኔታ የተፈቀደለት አምራች ይህንን የኤክሳይስ ታክስ ካላስታወቀ በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል።

እንደ ወንጀል ጥፋቶቹ መጠን ታይቶ በእነዚህ ጥፋቶች ላይ ተጨማሪ ቅጣቶችም ሊጣሉ ይችላሉ። ይህም እንደሚከተለው ነው:-

- ከ3 እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስራት፤ ወይም
- ከብር 50,000 እስከ 100,000 የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት::

10ሀ.4. የሚፈቀድ የብክነት መጠን አለ?

ብክነቶች/ጉድለቶች መጠናቸው እንዳይጨምር ተደርገው መጠበቅ አለባቸው:: ማናቸውም የማምረት እና የማሸግ ሂደቶች በተቻለ መጠን በብቃት እንዲከናወኑ ብክነቶችን በዝቅተኛው መጠን ማቆየት እና ሂደቱን መከታተል የአምራቹም ዋነኛ ጥቅም ነው:: በእርግጥ የብክነት እና የጉድለት መጠን እስከምን ድረስ እንደሚፈቀድ ሕጉ በግልፅ አያስቀምጥም። ምክንያቱም እያንዳንዱ የምርት ሂደት እና ጥቅም ላይ የሚውሉ የማምረቻ ቁሳቁስ እንደየአምራቹ አመራረት ስለሚለያዩ ለሁሉም አምራቾች የሚሠራ አንድ የጉድለት ጣሪያ መጠን ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው።

ስለሆነም የገቢዎች ሚኒስቴር ፖሊሲ አያንዳንዱ አምራች ያቀረበውን የጉድለትና ብክነት መጠን በማየትና

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በመርመር "አማካይ" ሊባል በሚችለው መጠን ላይ ከእያንዳንዱ አምራች ጋር ስምምነት ላይ መድረስን የሚፈልግ/የሚጠይቅ ነው።

በዚህም መሠረት አምራቾች እያንዳንዱን በምርት ዓመቱ የነበረውን ጉድለት በአግባቡ ተከታትለው ማወቅ አለባቸው። በእርግጥ አምራቾች ምርቶች ተሰርቀው እንደሆነ ወይም ከማምረት ብቃት ጋር ተያይዞ የማምረቻ መሣሪያዎች እድሳትና መሻሻል ያስፈልጋቸው እንደሆነ ለመረዳት ሲሉ የየጊዜውን ጉድለት መመዝገባቸው አይቀርም። የአንዱ ወር ጉድለት ከሌላው ጊዜ በተለየ ከፍተኛ የሆነበት የተለየ ምክንያት ሊኖር ይችላል። ነገር ግን አማካይ ተብሎ የተቀመጠው የጉድለት መጠን ቋሚ የመለኪያ ማመሳከሪያ ሊሆን ይገባል። ማብራሪያ ሊቀርብባቸው የማይችሉ ማናቸውም ጉድለቶች የኤክሳይስ ታክስ ይከፈልባቸዋል።

10ሀ.5. ሊከሰቱ የሚችሉ የብክነት/ጉድለት አይነቶች

የኤክሳይስ ታክሱ ሊነሳ የሚችለው ጉድለቶቹ በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ ሲከሰቱ እና በዕቃዎቹ ላይ ምንም ዓይነት የኤክሳይስ ታክስ ያልተከፈለባቸው ሲሆን ነው።

የጉለቶቹ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከሥራው ተፈጥሮአዊ ባህሪ አንፃር የሚከሰት ጉድለት ወይም ብክነት (ለምሳሌ ያህል ትነት) ነገር ግን መጠኑ አነስተኛ መሆን ይኖርበታል።
- የምርትና ማሸግ ጉድለቶች፡- እነዚህ ጉድለቶች በማሸግ ሂደት ላይ የሚከሰቱ የፈሳሽ ምርቶችን መደፋፋት ወይም የትንባሆ ምርቶችን መፋሰስ ያካትታሉ። የጉድለቱን መጠንም ምርቱ ከመታሸጉ በፊት የተመዘገበውን የጅምላ ምርት መጠን መረጃ እና በኋላ ላይ ወደ ምርት መያዣው ውስጥ የገባውን መጠን በማመሳከር መለካት እና ማወቅ ይቻላል። ይህም ማለት 100 ሊትር የጅምላ ፈሳሽ ምርት ኖሮ 300 x 30cl ጠርሙሶች (90 ሊትር) ከተሞሉ የ10cl ጉድለት ያሳያል ማለት ነው። ስለዚህ የዚህ ፈሳሽ ጉድለት ተመዝግቦ መያዝ ያለበት ሲሆን ጉድለቱ መብራራት ካልቻለ የኤክሳይስ ታክሱ በጎደለው 10 ሊትር ላይ መከፈል አለበት።
- በድንገተኛ አደጋ የሚከሰት ጉድለት፡- ለምሳሌ በፋብሪካ ውስጥ የሚከሰቱ ውድመቶች:: እነዚህ ተመዝገበው መያዝ እና ቀንና ሰዓቱ የተጠቀሰባቸው ፎቶዎችን የመሳሰሉ ማስረጃዎች ሊኖራቸው ይገባል።

10ሀ.6. የስቶክ ጉድለቶች

ሁሉም አምራቾች ወርሃዊ የክምችት ቆጠራ መዝገብ መያዝ አለባቸው:: ይህም የሚከተሉትን የሚያሳይ ሊሆን ይገባል፡-

- ምንም ዓይነት የምርት እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት በወሩ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ክምችት፣
- በወሩ ውስጥ የተመረቱና የታሸጉ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ በፍጆታነት ጥቅም ላይ ለመዋል ከፋብሪካ ወጪ የተደረገ ምርት ብዛት፤
- ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ ከፋብሪካ ወጪ የተደረገ ምርት ብዛት፤
- ለኤክሳይስ ታክስ ነፃ ተጠቃሚዎች ከፋብሪካ ወጪ የተደረገ ምርት ብዛት::

በዚህም መሠረት በክምችት ውስጥ ያለውና የተመረተው ብዛት ወጪ ከተደረገው ምርት ጋር ሲቀናነስ፣ በተጨባጭ ካለው ክምችት ጋር የሚጣጣም ቁጥር መሆን አለበት። ነገር ግን ማናቸውም ጉድለቶች/ልዩነቶች የሚታዩ ከሆነ በጎደሉት ዕቃዎች ላይ የኤክሳይስ ታክስ መከፈል አለበት። እንዲሁም ዕቃዎች ተሰርቀውም ከሆነ በእነዚያ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይስ ታክስ መከፈል አለበት። ስለሆነም ቋሚ የሆነ የክምችት ክትትል እና ቁጥጥር መከናወን አለበት። በዚህም መሠረት ሁሉም ክምችቶች ለዚሁ ዓላማ ተለይተው በተወሰኑ ቦታዎች ላይ መቀመጥ እና ቦታዎቹም በክምችት መዝገቦች ውስጥ በአግባቡ ተመዝግበው መቀመጥ አለባቸው።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

10ሀ.7. የእቃ ቆጠራ የመመሪያ ቁጥር 1071/2017 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 1 -6

የተፈቀደለት አምራች በዓመት በእያዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካው ውስጥ አጠቃላይ የእቃ ቆጠራ ማድረግ አለበት። የክምችት ቆጠራው የሚደረግበት ቀን ለገቢዎች ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች መገለፅ ያለበት ሲሆን የሚመለከታቸው የኤክሳይስ ታክስ ባለሙያዎችም በቆጠራው ሂደት ላይ በአካል ለመገኘት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የዕቃ ቆጠራው ማናቸውም ሊከሰቱ የሚችሉ ጉድለቶችን ወይም የታክስ ማስታወቅ ስህተቶችን ለይቶ ለማወቅ ወሳኝ ነው። ቆጠራው በሚደረግበት ጊዜም የማምረት ሥራው ወይም ዕቃዎችን ከፋብሪካው ወጪ የማድረግ ሥራው ተቋርጦ ፋብሪካው ዝግ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህም ቆጠራውን ፍፁም ትክክል እንዲሆን ያደርገዋል።

በቆጠራው ላይ የተገኘው ቁጥር በወርሃዊ የዕቃ ቅጾች ሲቀርብ ከነበረው የጥቅል ክምችት ቁጥር ጋር የሚስማማ መሆን አለበት። በቁጥሩ ላይ ልዩነት ከታየ በገቢዎች ሚኒስቴር ተመርምሮ በጎደሉት ክምችቶች ላይ የኤክሳይስ ታክስ ውሳኔዎች ይሰጣሉ።

ነ) እያንዳንዱ የተፈቀደለት ሰው በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ጥሬዕቃዎችን ጨምሮ በፋብሪካው ውስጥ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ በየዓመቱ የተሟላ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡፡

2) ከዚህም በተጨማሪ የተፈቀደለት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ ተከታታይነት ያለው ወርሀዊ ቆጠራ ማካሄድ አለበት፡-

ሀ) በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኘውን ጥሬዕቃና የመጨረሻ ምርት፣

ለ) አዲስ ወደፋብሪካው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን፣

ሐ) በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬዕቃዎችን፣

መ) በፋብሪካው የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶችን፣

ሠ) በፋብሪካው ተመርተው ወደፋብሪካው መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን

ረ) የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሰ) የኤክሳይዝ ታክሰ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

ሸ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎችን፣

3) የተፈቀደለት ሰው ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት።

4) የዕቃ መጥፋት ተቀባይነት የሚኖረው የዕቃው መጥፋት በታወቀበት ጊዜ ሪፖርት የተደረገና አግባብ ባለው የፀጥታ አካል ምርመራ ተካሂዶ የዕቃው መጥፋት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን መጥፋቱ ባልተረጋገጠ ዕቃ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል።

5) በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ቆጠራ ከመካሄዱ ከ14 ቀን በፊት የታክሱ ባለሥልጣን ይህንኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት።

6) ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ በፋብሪካው ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ መቆም አለበት።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል10ለ: ጉድለቶችን/ብክነቶችን መቆጣጠር

10ለ.1. መግቢያ

የደረሱት ብክነቶች ወይም ጉድለቶች በአምራቹ መብራት ሳይችሉ ሲቀሩ በነደሉት ዕቃዎች ላይ ያለው የኤክሳይስ ታክስ መከፈል አለበት:: ይህም የሆነበት ምክንያት ማብራሪያው ካልቀረበ ዕቃዎቹ የኤክሳይስ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው እንደወጡ ተደረገው መቆጠር ስላለባቸው ነው።

ቀደም ሲል በዚህ ማኑዋል ላይ እንደተጠቀሰው፣ አምራቹም ግዴታውን መወጣቱን ለማሳየት የገቢዎች ሚኒስቴርም አምራቹን ኦዲት ለማድረግ እንዲችል ዋናው አስፈላጊ ጉዳይ የኦዲት መከታተያ መዝገቡ ነው። ይህም ወደ ፋብሪካው የገቡ ዕቃዎችን ርክክብ፣ በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወኑ የምርት ሂደቶችና እንቅስቃሴዎችን፣ የመጨረሻ ምርቶችን አስተሻሸግ እና አቀማመጥ እንዲሁም ዕቃዎቹ ከፋብሪካው ወጪ ሲደረጉ የኤክሳይስ ታክስ ስለመከፈሉ ወይም ያለኤክሳይስ ታክስ ክፍያ ወጪ መደረጋቸውን የሚያሳይ ግልፅ መዝገብ ነው።

ዕቃዎቹ ከፋብሪካ ወጪ ሲደረጉ፣ ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ ለሆኑ ወይም ታክሱ ዘግይቶ መከፈል ለሚችልባቸው ጉዳዮች ወጪ መደረጋቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ካልተቻለ የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት። በማናቸውም የምርት ሂደት እና በማናቸውም የፋብሪካ የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉድለቶች በየቀኑ ያጋጥማሉ። በጠርሙሶች የማሸግ ሂደት ውስጥ የመደፋፋት/መፍሰስ፤ በአልባሳት ማምረቻ ውስጥ የጨርቆች አቆራረጥ ብክነት፤ በሲጋራ ማምረቻ ውስጥ የትምባሆ ቅጠል በብናኝ መልክ ሊባክን ይችላል:: ነገር ግን አምራቾች እነዚህን ብክነቶች መጠናቸው ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ አለባቸው። (ይህን ማድረግ ጥቅሙ ለራሳቸው ነው)።

ከዕቃ ቆጠራው ጋር ተያይዞ አስፈላጊው ጉዳይ በቆጠራው ቀን ፋብሪካው መዘጋት አለበት:: የማምረት ሥራውም የሚቋረጥ ሲሆን ከፋብሪካው የሚወጣም ሆነ ወደ ፋብሪካው የሚገባ ምንም ዓይነት ዕቃ አይኖርም። ይህም ቆጠራው ያለምንም መደነቃቀፍ እንዲደረግ ያግዛል። በመሆኑም የቆጠራው ውጤት በጊዜው ፋብሪካው ውስጥ ያለውን ትክክለኛ ክምችት የሚያሳይ ይሆናል። ስለዚህ ቆጠራው በትክክል መካሄዱን ለማወቅ በቦታው መገኘት ይኖርብናል። ስለሆነም የትልልቅ ድርጅቶች ቆጠራ በሚደረግበት ጊዜእንደፋብሪካው ስፋትና ጥበት መሰረት አፈሰሮች በቦታው ሊገኙ እና ቆጠራው በሚደርግበት እያንዳንዱ ቦታ ሊመደቡ ይገባል።

ቆጠራው ሲጠናቀቅ በፋብሪካው ውስጥ ምን እንዳለ የሚያሳይ ውጤት በእጃችን ይኖራል:: ይህንንም ቁጥር ወደ ፋብሪካው የገቡ የገቢ ዕቃዎችን፣ ሌሎች ገቢ የተደረጉ ዕቃዎችን፣ የምርት ደረጃዎችን፣ ሽያጮችን፣ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን እንዲሁም የኤክሳይስ ክፍያዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ለመተንተን እንደ ዋነኛ ማመሳከሪያ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

እንጠቀምበታለን።

ይህ ቆጠራ በወረቀት መልክ እያንዳንዱን አምራች እንዲያቀርብ በምንጠይቀው የእያንዳንዱን ወር እንቅስቃሴና ክምችት ከሚያሳዩ ሰነዶች ላይ በየወሩ መከናወን ይችላል። ይህን መረጃ በቅርበት መከታተል በቀረበው ቁጥርና መከፈል ባለበት የኤክሳይስ ታክስ መካከል ማንኛውም ልዩነት ካለ በማሳየት ሊከሰት ለሚችል ጥፋት አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል።

ቆጠራው በሚካሄድበት ጊዜ ድርጅቱ የት ቦታ ምን እንደሚገኝ የተመዘገበ መረጃ ሊኖረው ይገባል። የትኛውም ዓይነት ጉድለት ሲገኝ መመርመር ያለበት ሲሆን ማብራሪያ ሊቀርብበት ካልቻለ የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት። ለምሳሌ መብራራት የሚችል ጉድለት ስንል፣ አምስት ሳጥን የዋሊያ ቢራ ጎድሎ ግን ሌላ ተመሳሳይ ብራንድ ተጨማሪ ትርፍ አምስት ሳጥኖች ከተገኙበት በመረጣ ላይ የተከሰተ ስህተት ነው ብለን እንወስደዋለን ማለት ነው። ይሁንና ጎደለ የተባለው ብራንድ የሚከፈልበት የኤክሳይስ ታክስ፣ ትርፍ ቁጥር ከተገኘበት ብራንድ የሚበልጥ ከሆነ የኤክሳይስ ታክሱ በልዩነቱ ላይ መከፈል አለበት።

ኩባንያው ለዋነኛ የመዝገብ አያያዙ የሶፍትዌር ሲስተም የሚጠቀም እንኳ ቢሆን ወደ ፋብሪካው የሚገቡትንና የሚወጡትን ዕቃዎች አመዘጋገብ ሊያግዙ የሚገቡ የወረቀት ሰነዶች ይኖራሉ።

ለምሳሌ የማስረከቢያ ሰነዶች ወደ ፋብሪካ የገቡትንና ከፋብሪካ የወጡትን ምርቶች ዓይነት እና መጠን ሊያካትቱ ይገባል። እንዲሁም ዕቃዎቹ ከፋብሪካው የወጡበትን ወይም ወደ ፋብሪካው የገቡበት ቀን እና ያጓዝው ሰው / የአቅራቢው / የደንበኛው ስም በቅጹ ላይ መስፈር ይኖርበታል። ከእነዚህ መረጃዎች አንዱ ቢጎድል ለቅጣት ወይም ኤክሳይስ ታክስ ውሳኔ ልናቀርብ እንችላለን። ትክክለኛውን ምዝገባ በትክክለኛው ቅጽ ላይ ማከናወን የተፈቀደለት አምራች ግዴታ ነው።

10ለ.3. ማጠቃለያ

በምርት ሂደት ላይ ጉድለት ምንጊዜም የሚያጋጥም ክስተት ነው። ነገር ግን ያ ጉድለት በእያንዳንዱ ሂደት ላይ ተለክቶ እና ክትትል ተደርጎበት የጉድለቱ መጠንም ተመዝግቦ መያዝ አለበት። ስለዚህም ተጠባቂ የሚሆነውን የጉድለት መጠን በአማካይ ለማስቀመጥ ይቻላል።

ማናቸውም ማብራሪያ ሊቀርብባቸው የሚችሉ ጉድለቶች ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ ይደረጋሉ። ይሁንና በፋብሪካው ላይ አማካይ ተብሎ ከተያዘው ተጠባቂ የጉድለት መጠን በላይ የሆነ ጉድለት እንዲሁም በቂ ማብራሪያ ሊቀርብበት ያልቻለ ማናቸውም ጉድለት፣ ለምሳሌ የክምችት ቆጠራ ላይ የታየ ጉድለት የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

የገቢዎች ሚኒስቴር ማናቸውም የተፈቀደላቸው አምራቾች የአመራረት ሂደታቸውን በብቃት እና በውጤታማነት እንዲመሩ ሊጠብቅ ይገባል። እንዲሁም የኪሳራዎችን መጠን ዝቅተኛ እንዲያደርጉ በሕግ የተቀመጠ ግዴታ ነው። በአምራቹ ላይ የተጣሉት የመዝገብ አያያዝ የሕግ ግዴታዎች ጥብቅ እና መከበር ያለባቸው ናቸው።

ያጋጠመን ጉድለት ለማስታረቅ ከጥሬ ዕቃ መቀበል ጀምሮ የመጨረሻ ምርቱ እስከወጣበት ድረስ ባለው ሂደት ማመሳከር ይቻላል፤ ወይም ለእያንዳንዱ ብራንድ የተከፈለውን የኤክሳይስ ታክስ እንደማመሳከሪያ ይዞ ጥሬ ዕቃ ወደገባበት ወደኋላ ተመልሶ በማመሳከር ጉድለቱን መፈለግና ማግኘት ይቻላል።

አምራቹ መዝገቦችን የሚይዘው በወረቀት ላይም ይሁን በሲስተም መዝገቦቹ የሚጠበቀውን እንቅስቃሴ የሚያሳዩ መሆናቸውን ያረጋግጡ፤ ማብራሪያ ሊቀርብበት ላልቻለ ማንኛውም ጉዳይ ጥያቄያችሁን አቅርቡ።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቁ.1 መዛግብትና ሥነ-ሰነዳሰነድ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል አስራ አንድ፡ የሀገር ውስጥ ኤክሳይስ ታክስ አከፋፈል ስርዓትና ተጠያቂነት

11.1. መግቢያ

የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ለፍጆታ ዝግጁ ሲሆኑ በጅምላ ባሉበት ሁኔታም ቢሆን ለሀገር ውስጥ የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ ግዴታ ያለባቸው ይሆናሉ። በዚህም መሠረት የአልኮል መጠጥ ምርት ልክ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ሲወጣ የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት። የኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያ እና የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ ከሂሳብ ጊዜው ቀጥሎ ባለው በወር የመጨረሻው የሥራ ቀን መቅረብ እና መከፈል አለበት።

11.2. የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይስ ታክስ የክፍያጊዜ እና ግዴታ

11.2.1. ሕጉ

የኤክሳይስ ታክስ አዋጁ በአንቀፅ 7 ላይ እንደተደነገገው ማንኛውም በኢትዮጵያ የተመረተ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ተመርቶ ከፋብሪካው እንደወጣ የኤክሳይስ ታክስ የመክፈል ግዴታው ይቋቋማል።

ይሁን እንጂ ዕቃው እዚያው በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋለ ልክ ጥቅም ላይ በዋለበት ሰዓት ከፋብሪካው እንደወጣ ተደርጎ የሚወሰድ እንደሆነም አዋጁ ይደነግጋል።

በአንቀፅ 28 ላይ እንደተቀመጠው፣ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ብዛት በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ተመርቷል በተባለው እና ሊመረት ይችላል ተብሎ በሚታመነው መካከል ያለውን ዕቃ ከኤክሳይስ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ከፋብሪካው ወጪ እንዳደረገ ይቆጠራል።

የተፈቀደለት አምራች በተጨባጩ እና ምዝገባ ባደረገባቸው ቆጠራዎች መካከል ልዩነት መኖሩን እንዳወቀ ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት። በመሆኑም አምራቹ ከምችቱ ላይ ያገኛቸውን የቁጥር ልዩነቶች በሙሉ በማስታወሻ መዝግቦ ማስቀመጥ አለበት።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረቱ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ጥቅም ላይ ለመዋል ብቁ ሲሆኑ የኤክሳይስ ታክስ ግዴታቸው ይቋቋማል:: ይህም የገቢዎች ሚኒስቴርን ማብራሪያ ባልቀረበባቸው ጉድለቶች ላይ የኤክሳይስ ታክሱን እንዲጠይቅ ያስችለዋል። ምንም እንኳን በአዋጁ መሠረት ግዴታው ከፋብሪካው ወጪ በተደረጉ ወይም በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች የተገደበ ቢሆንም፣ በአንቀፅ 28 እንደተገለፀው በቂ ማብራሪያ ያልቀረበባቸው ማናቸውም ጉድለቶችም የኤክሳይስ ታክስ ይከፈልባቸዋል።

ማስታወሻ፡- ሁሉም ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይስ ታክስ ይከፈልባቸዋል። ይህም ማለት ምርቶቹ በሽያጭ ባይወጡም እንኳ (በነፃ ስጦታነት ወይም በናሙናነት

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ወጪ ቢደረጉም) ኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት። እንዲሁም ወጪ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ የኤክሳይስ ታክስ ደረሰኝ መኖር አለበት።

11.3. የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ

የሀገር ውስጥ የኤክሳይስ ታክስ መከፈል ያለበት የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ ሲደረጉ ነው። ሌሎች የኤክሳይስ ታክስ መክፈያ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ማብራሪያ ሊቀርብባቸው ያልቻሉ ጉድለቶች፤
- ምርቱ በፋብሪካው ውስጥ ለፍጆታ ሲውል፤
- በዕቃ ቆጠራ ወቅት የተገኘ የዕቃ ጉድለት፤
- ምርቶች ያለ ምንም ክፍያ ከፋብሪካው ወጪ ሲደደረጉ፤
- ምርቶች የተሰረቁ እንደሆነ፡፡

በአጠቃላይ የሒሳብ መዝገብ ላይ የተመዘገቡ ቁጥሮችን እንዴት ማስታረቅ እንዳለብን እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሥራ እንቅስቃሴው አንፃር የቀረቡትን የኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያዎች እንዴት መከታተል እንደሚችል የኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ያብራራል።

114. ሕጉ፡ የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ

የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ እንደሚያስቀምጠው፡-

አንቀፅ 6፡ ... በተፈቀደላቸው አምራቾች በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረቱ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተጣለው የኤክሳይስ ታክስ ይከፈልባቸዋል (ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎችም የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ሲሆን ይህም በጉምሩክ ዲፓርትመንት በኩል የሚስተናገድ ነው)። የኤክሳይስ ታክስ ማስከፈያ መጠኑም በሠንጠረዥ 1 ላይ በተቀመጠው አግባብ ይሆናል፡፡

አንቀፅ 7፡ ... የተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ ለተመረቱ የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ኤክሳይስ ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት። (አስመጪም ከሆነ፣ ከውጭ ሀገራት ላስመጣቸው ምርቶች የመክፈል ግዴታ አለበት)።

ያልተፈቀደለት አምራች ሲገኝ በሁሉም ዕቃዎች ላይ የኤክሳይስ ታክስ መክፈል አለበት፤ እንዲሁም ሕግ በመተላለፉ ቅጣት ይጣልበታል።

11.5. የኤክሳይስ ታክስ ማሳወቂያ ቅጽ

በኤክሳይስ አዋጁ አንቀፅ 36 በተደነገገው መሠረት የተፈቀደለት አምራች የእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የወሩን ሒሳብ መዝጊያ ተከትሎ 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት የኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያ በታክስ ባለስልጣኑ በኩል በጸደቀው ቅጽ መሰረት ማቅረብ አለበት። የታክስ ማሳወቂያው በወረቀትም፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴም መቅረብ ይችላል። ያሳወቁት ታክስ ክፍያው የሚፈፀመው በተከታዩ ወር ሰላሳኛ ቀን ላይ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ቅጅ አገልግሎት ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በታክስ ማስታወቂያ ቅጹ ላይ የቀረቡት መረጃዎች በጠቅላላ በገቢዎች ዳታ ቄርሃውስ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ እና የእያንዳንዱ አምራች መረጃም እንዲተነተን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም የኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያው ሰንጠረዦች እያንዳንዳቸው በትክክል መሞላት አለባቸው። እያንዳንዱ ዝርዝር ከአምራቹ የየቀን የኤክሳይስ ምዝገባ ጋር የሚታረቅ መሆን አለበት። ቅጹ የኤክሳይስ ታክሱን ለማስላት ጥቅም ላይ የዋሉት ደረሰኞች እንዲዘረዘሩ ይጠይቃል፤ ነገር ግን ዋናዎቹ ደረሰኞች መቅረብ አያስፈልጋቸውም።

11.6. የኤክሳይስ ታክስ እንዴት ይከፈላል?

በባንክ ወይም በኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴ ወደ ገቢዎች ሚኒስቴር የባንክ ሒሳብ በማስተላለፍ የኤክሳይስ ታክስ ክፍያው ይፈፀማል። በተቻለ መጠን ከፋዮች በጥሬ ገንዘብ ከመክፈል ይልቅ በኤሌክትሮኒክ የክፍያ መንገድ እንዲከፍሉ ይበረታታሉ።

በቀላሉ ከትክክለኛው ቅጽ ጋር ለማዛመድ እንዲቻል ክፍያው የግብር ማስታወቂያ ቅጹ ላይ ያለውን የማመሳከሪያ ቁጥር ማካተት አለበት።

11A.7. ማጠቃለያ

የኤክሳይስ ታክስ መክፈል ግዴታ የሚሆነው ምርቶቹ ለአገልግሎትና ፍጆታ ዝግጁ ሲሆኑ ነው። ነገር ግን እቃዎቹ በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚመረቱ እና የሚከማቹ በመሆኑ የኤክሳይስ ታክስ እግድ ስር መቆየት ይችላሉ።

የኤክሳይስ ታክስ መክፈል ያለበት ምርቶቹ ከፋብሪካው ሲወጡ ነው። ምርቶቹ ከፋብሪካ ወጪ በተደረጉ በቀጣዩ ወር መጨረሻ ላይ የኤክሳይስ ታክሱ መክፈል ይኖርበታል።

ማስታወሻ፦ የታክስ ማሳወቂያ ቅጹ እንዴት እንደሚመረመርእና የፍተሻ ሥራ እንዴት እንደሚከናወን የሚያስረዳው መረጃ በኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ላይ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ደህንነት ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ዓሥራ ሁለት፡- ከተፈቀደለት ፋብሪካ የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ወጪ ስለማድረግ

12ሀ: የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

12ሀ.1. መግቢያ

የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ምርቶች በሚከተሉት አግባቦች ከተፈቀደላቸው ፋብሪካዎች ወጪ ሊደረጉ ይችላሉ፡-

- የተወሰኑ ሽያጮች ሲከናወኑ የኤክሳይስ ታክሱ ተከፍሎ ከሆነ።
- ምንም ዓይነት ሽያጭ በማይኖርበት ሁኔታ ከፋብሪካው ወጪ ሲደረጉ የኤክሳይስ ታክሱ ተከፍሎ ከሆነ።
- ምርቶቹ ለሽያጭ ናሙና ወጪ የሚደረጉ ከሆነ።
- ወደ ውጭ ሀገራት ለሚላኩ ዕቃዎች ሲሆን፤
- የኤክሳይስ ታክስ ነፃ ለተደረገላቸው ተጠቃሚዎች ከሆነ።

ይህ ክፍል የተፈቀደለት አምራች ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ሲያደርግ መከተል ያለበትን የአሠራር ሂደት የሚያስረዳ ነው።

12ሀ.2. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከተፈቀደለት ፋብሪካ ስለማውጣት

መመሪያ ቁጥር 1071/2017/2013 አንቀጽ 42 እና 43 ዕቃዎች በኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ ለመቅረብ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ ስለሚደረጉበት ሁኔታ ይገልፃል::

አንቀጽ 42 ሽያጭ ከተከናወነ በኋላ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ስለማውጣት የሚከተለውን ይዘረዝራል፡-

(1) የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከፋብሪካው ወጪ እንዳደደረገ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል።

(2) በታወቀ ሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ የወጡ ዕቃዎች የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የማስረከቢያ ሰነድ እና የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥባቸው ይገባል።

(3) ወደፊት ሽያጫቸው የሚከናወን ዕቃዎች ካልሆኑ በስተቀር ከፋብሪካ በሽያጭ በሚወጡ ዕቃዎች ላይ ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት የሽያጭ ደረሰኝ መቆረጥ አለበት።

(4) ከተፈቀደለት ፋብሪካ ከወጡ በኋላ የሚሸጡ ዕቃዎች ከፋብሪካው ከወጡበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለደንበኛው ተሸጠው የሽያጭ ደረሰኝ ሊቆረጥላቸው እና ሽያጩ ከማስረከቢያ ሰነድ ጋር እንዲጣጣም መደረግ ይኖርበታል።

አንቀጽ 43 ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ ስለሚወጡ ዕቃዎች የሚከተለውን ይዘረዝራል፡-

(1) የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ሽያጭ የሚከናወነው ከፋብሪካው ውጪ የሚሆንበት አጋጣሚ ሲኖር ዕቃዎቹ ለሽያጭ ከፋብሪካው በሚወጡበት ጊዜ የምርቱን ልዩ መጠሪያ፣ ዓይነት እና ብዛት የሚገልፅ የማስረከቢያ ሰነድ መዘጋጀት አለበት።

(2) የማስረከቢያው ሰነድ በታክሱ ባለስልጣን በሚወጣ መመሪያ የሚወሰኑ ዝርዝር መረጃዎችን

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ሰነድ ማስተዳደሪያ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ሊይዝ ይገባል።

(3) በሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ የተሸጠውን ዕቃ ብዛት፣ ዓይነት፣ ልዩ መጠሪያ፣ ታክሱ ባለስልጣን አስቀድሞ የተገለፀውን ለኤክሳይስ ታክስ መሠረት የሆነውን ዋጋ፣ የሚከፈለውን የኤክሳይስ ታክስ ልክ እንዲሁም የገዢውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና አድራሻ የሚያሳይ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ገዢ መሰጠት አለበት።

(4) የሽያጩ ደረሰኝ ዕቃው ከፋብሪካ በወጣበት ጊዜ የተመዘገበውን የማስረከቢያውን ሰነድ ቁጥር መያዝ ይኖርበታል።

(5) የሽያጭ ደረሰኙ ቅጂዎች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን፣ ዋናው ለደንበኛው ይሰጣል፤ ቀሪው ከማስረከቢያው ሰነድ ጋር ይያያዛል።

(6) ከፋብሪካ የወጣውን፣ የተሸጠውን እና ተመላሽ የተደረገውን ዕቃ በትክክል ለማስታረቅ እንዲቻል በሽያጭ ደረሰኙ ላይ የማስረከቢያው ሰነድ ቁጥር እንዲሁም በማስረከቢያው ሰነድ ላይ የሽያጭ ደረሰኙ ቁጥር መጻፍ አለበት።

ወጪ የሚደረጉ ዕቃዎችን በሚመለከት የፍተሻ ሥራዎች እንዴት እንደሚታቀዱ እና እንደሚካሄዱ በኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ላይ በዝርዝር ተቀምጧል። ይሁን እንጂ በዚህ ክፍል ቀጣይ ንዑስ ክፍሎች አጠቃላይ ቅኝቶች ተጠቃለው ቀርበዋል።

12ሀ.3. ከሽያጭ ሰነዶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ

አብዛኛውን ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከደንበኞች ከቀረበ የሽያጭ መጠየቂያ ሰነድ ጋር በተጣጣመ መልኩ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ ይደረጋሉ።

እነዚህ ርክክቦች በሚከናወኑበት ጊዜ አምራቹ ዕቃዎቹ ወደየት እንደሚሄዱ እና ግዢውን የፈፀመው ደንበኛ ማን እንደሆነ ያውቃል። ደንበኛም እንዲሁ ምን ያህል ዕቃዎችን እንዳዘዘ ያውቃል። ስለዚህ ለኤክሳይዝ ታክስ ዓላማዎች ሲባል የሽያጭ ደረሰኙ የዕቃውን ብዛትና ዓይነት እንዲሁም የኤክሳይስ ታክሱ መሠረት የሆነውን ዋጋ የሚያንፀባርቅ ይሆናል።

እነዚህ እንቅስቃሴዎች ከመከናወናቸው አስቀድሞ ዕቃዎቹ ወጪ በሚደጉበት ፋብሪካ ውስጥ የሚከተሉት ተግባራት መከናወን አለባቸው፡-

- በሽያጭ ውሉ መሠረት ዕቃዎቹን በተሸከርካሪው ላይ መጫን::
- የዕቃውን ዓይነትና ብዛት፣ እንዲሁም የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት/ብራንድ ዋጋ የሚያሳይ የማስረከቢያ ሰነድ ሞልቶ ማጠናቀቅ። የተለያየ ዋጋ ወይም የኤክሳይስ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ያላቸው እያንዳንዳቸው ዕቃዎች በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ ተለይተው መቀመጣቸውን ያረጋግጡ::
- በተሸከርካሪው ላይ የተጫነው ዕቃ ብዛት በሚመለከተው አካል በፊርማ መረጋገጥ አለበት።
- የማስረከቢያ ሰነዱ አንድ ቅጂ ለአሽከርካሪው መሰጠት እና ቅጂው ከዕቃዎቹ ጋር አብሮ መሄድ አለበት። የሰነዱ ዋና ቅጂ ተፈርሞበት በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ የተገለፁት ዕቃዎች የተላከለትን ደንበኛ ማንነት ከሚያሳዩት ሁሉም ተዛማጅ ደረሰኞች ጋር ተያይዞ መቀመጥ አለበት።
- ለዕቃዎቹ የተቆረጠው ደረሰኝ በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ ካሉት ዝርዝሮች ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት።

ማናቸውም ወጪ የተደረጉ ዕቃዎች ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ በዕለታዊ የኤክሳይስ ታክስ መመዝገቢያ ላይ

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

መመዝገብ አለበት። በተጨማሪም ለደንበኛው የተሰጠው የማስረከቢያ ሰነድ መለያ ቁጥር እና የሽያጭ ደረሰኙ መለያ ቁጥር መመዝገብ አለባቸው።

ዕቃዎቹን በመረከብ ሂደት ተረካቢው ዕቃዎቹ በትክክል መድረሳቸውን ማረጋገጥ፣ ዕቃዎቹን ስለመረከቡ ማረጋገጫነትም የማስረከቢያ ሰነዱ ላይ መፈረም እና የማስረከቢያ ሰነዱን በመዝገብ መያዝ አለበት። በጭነቱ ላይ ማናቸውም ልዩነቶች ካሉ ይህ የታየው ልዩነት በመቀበያ ቅጹ ቅጂ ላይ መጻፍ አለበት።

12ሀ.4. የተረጋገጠ ሽያጭ ሳይኖር ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ

አብዛኞቹ የተፈቀደላቸው አምራቾች የተረጋገጠ ሽያጭ በሌለበት ሁኔታ ዕቃዎችን ከፋብሪካቸው ወጪ ያደርጋሉ። ነገር ግን ዕቃዎቹን ወደ ገቢያ በማቅረብ በዕለቱ ሽያጭ ይፈፅማሉ። እንደዚህ ላሉት የዕቃ አወጣጦች ዕቃው ወጪ ከመደረጉ በፊት ተገቢው ***የማስረከቢያ ሰነድ*** መሞላት እና መረጋገጥ አለበት። በገቢያ ቦታው ሽያጩን የሚያከናውነው የሽያጭ ባለሙያም የሽያጭ ደረሰኝ ጥራዝ ይዞ መንቀሳቀስ ያለበት ሲሆን ለእያንዳንዱ ሽያጭም የሚከተሉትን ማከናወን አለበት፡-

- ደረሰኝ መቁረጥ፤ እና
- የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት/ብራንድ ዓይነት እና ብዛት እንዲሁም የእያንዳንዱን ምርት/ብራንድ ዋጋ የሚያሳይ ማስረከቢያ ሰነድ በአግባቡ መሙላት አለበት። የተለያየ ዋጋ ወይም የኤክሳይስ ታክስ ማስከፈያ መጠን ያላቸው እያንዳንዳቸው ዕቃዎች በማስረከቢያ ሰነዱ ላይ በተለያዩ መስመሮች ተለይተው መቀመጣቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

ከፋብሪካ ወጪ የሚደረጉ ማናቸውንም ዕቃዎች በተመለከተ በሁሉም ዕቃዎች ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ በዕለታዊ የኤክሳይስ ታክስ መመዝገቢያ ላይ መመዝገብ አለበት። ዕቃዎቹን ጭኖ የወጣው ተሽከርካሪ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ሳይሸጡ የተመለሱ ዕቃዎች በሙሉ ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች መዝገብ ላይ ተመዝግበው በፋብሪካው ውስጥ ታክስ የተከፈለባቸው ዕቃዎች የሚከማቹበት ቦታ ላይ መቀመጥ አለባቸው። እነዚህ ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ለቀጣይ ሽያጭ ከፋብሪካው ተመልሰው ሲወጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸው ዕቃዎች የሚመዘገቡበት የማስረከቢያ ሰነድ ጥቅም ላይ መዋል አለበት:: ይህም መደበኛ የማስረከቢያ ሰነድ መሆን ይችላል፤ ነገር ግን የኤክሳይስ ታክስ መከፈሉን የሚገልፅ ማስታወሻ በሰነዱ ላይ መጻፍ አለበት።

12ሀ.5. የኤክሳይስ ታክስ ሳይከፈል ዕቃዎችን ከፋብሪካ ወጪ ስለማድረግ

የኤክሳይስ ታክስ አዋጁ አንቀፅ 8 የኤክሳይስ ታክስ ላይከፈል የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ዝርዝር ያስቀምጣል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

- ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ (ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ የተደረጉ) ዕቃዎች፤
- የተፈቀደለት የዕቃ መጋዘንን ጨምሮ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች፤
- ከገቢዎች ሚኒስቴር አስቀድሞ በተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች በተገኙበት ከተመረቱበት ፋብሪካ ከመውጣታቸው በፊት ከጥቅም ውጭ እንዲሆኑ የተደረጉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤
- ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤
- ለኢኮኖሚ፣ ለማኅበራዊ እና ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች በሚኒስትሩ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች፤
- ለሰው ልጅ በመጠጥነት አገልግሎት ሊሰጥ በማይችልበት አኳኋን የተመረተ አልኮል፤

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- በሚከተለው ሁኔታ በአደጋ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጠፉ ወይም የተበላሹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፡-
  (a) ዕቃዎች የመጫን ወይም የማውረድ ተግባርን ጨምሮ ዕቃዎቹ ከአምራቹ ፋብሪካ በመውጣት ላይ ባሉበት ጊዜ፤
  (b) ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት ዕቃዎቹ በተመረቱበት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ ባሉበት ጊዜ፤ ወይም
  (c) ዕቃዎቹ ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት በአውሮፕላን ወይም በመርከብ በመጓጓዝ ላይ ባሉበት ጊዜ::

12ሀ.6. ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ ለመሆን መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች

ምንም እንኳ በአንቀጽ 8 ላይ የተገለፁት የዕቃ አወጣጦች የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ ባያስፈልጋቸውም የሚከተሉትን የዕቃ አወጣጦች በተመለከተ ዕቃዎቹ በአግባቡ ጥቅም ስለመዋላቸው የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡-

- በተፈቀደ መጋዘን ውስጥ የተከማቹትን ጨምሮ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ወደ ውጭ ሀገር የተላኩ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፡- እነዚህን በተመለከተ ዕቃዎቹ ወደ ውጭ ሀገር መላካቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች መኖር አለባቸው:: ማስረጃዎች ከሌሉ ዕቃዎቹ የኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ እንደተሸጡ መቆጠር ስላለበት የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት።
- ከገቢዎች ሚኒስቴር አስቀድሞ በተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ መሠረት የታክስ ባለስልጣኑ ሠራተኞች በተገኙበት ከተመረቱበት ፋብሪካ ከመውጣታቸው በፊት በአምራቹ ከጥቅም ውጭ እንዲሆኑ የተደረጉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፡- ለእነዚህም አምራቹ ትክክለኛውን የአወጋገድ ሂደት መከተል አለበት:: የአወጋገዱ ቅድመ-ማስታወቂያ ካልተፈፀመ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከአወጋገዱ በፊት በዕቃዎቹ ላይ ምርመራው ማድረግ ስለማይችል የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት።
- ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይስ ታክስ አይከፈልባቸውም። ነገር ግን አምራቹ ዕቃዎቹ የተሸጡለት ሰው ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ የተደረጉ ድርጅቶችን የሚወክል ወይም የተፈቀደለት ሰው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ሊኖረው ይገባል:: እንዲሁም ዕቃው የሚደርስበት አድራሻ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት። እነዚህ ማስረጃዎች ካልተሟሉ ግን አምራቹ የኤክሳይስ ታክሱ መከፈል አለበት።
- ለሰው ልጅ በመጠጥነት አገልግሎት ሊሰጥ በማይችልበት አኳኋን የተመረተ አልኮል፡- ነገር ግን አልኮሉ በተገቢው ኬሚካል ለሰው ልጅ በመጠጥነት አገልግሎት ላይ እንዳይውል ተደርጎ መመረቱን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት። ከዚህ ጋር ተያይዞ አልኮል ለሰው ልጅ በመጠጥነት አገልግሎት ላይ እንዳይውል የሚደረግበትን ሁኔታ ለማብራራት መመሪያ የሚወጣ ይሆናል።

12ሀ.7. ማጠቃለያ

የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይስ ታክስ የተከፈለባቸውንም ሆነ ምንም ዓይነት የኤክሳይስ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከፋብሪካው ወጪ የሚደረጉ ማናቸውንም ዕቃዎች በተመለከተ ማስረጃ መያዝ አለበት።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዘርፉ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

እንዲሁም አምራቾች ወደ ውጭ ሀገር የተላኩ ወይም በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን በተመለከተ ማስረጃ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን፣ ቀረጥ ለተከፈለባቸው ዕቃዎች ደግሞ ሁሉም የማስረከቢያ ሰነዶች የደንበኛውን ማንነት፣ የምርት ዓይነቶችን፣ ብዛት እና ዋጋ ከሚያሳዩ ደረሰኞች የተያያዙ መሆን አለባቸው።

እነዚህን መረጃዎች አሟልተው ካልተገኙ ቅጣት የሚጣል ሲሆን ወደ ውጭ ሀገር በተላኩ ዕቃዎች ላይ በማስረጃ መረጋገጥ ያልቻለ የኤክሳይስ ታክስ መከፈል አለበት።

ክፍል 12ለ፡ የዕቃ አወጣጥ ሂደቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ

12ለ.1. መግቢያ

የዕቃዎች ከፋብሪካው ወጪ መደረግ የአዲት መከታተያ ሥራውን እንዲጠናቀቅ ያደርገዋል። ከአንድ ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን ዓይነትና መጠን ለማረጋገጥ በአምራቹ የተያዙ መዝገቦችን መጠቀም የተሻለው አማራጭ ነው።

አምራቹ እንዲያሟላቸው የሚጠበቁ ግዴታዎች ያሉበት ሲሆን፣ ይህም ታክስ የተከፈለባቸውን ርክክቦች የሚያሳዩ የማስረከቢያ ሰነዶችን እና ደረሰኞችን፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክን የሚያረጋግጡ የጉምሩክ ሰነዶችን፣ እንዲሁም ከታክስ ነፃ ለሆኑ ተጠቃሚዎች የኤክሳይዝ ታክሱ ሳይከፈልባቸው ወጪ የተደረጉ ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ኣግባብነት ላላቸው ደንበኞች በትክክል መድረሳቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን መያዝን ያጠቃልላል።

12ለ.2. የዕቃ አወጣጥ ሂደቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ

ማናቸውንም የተፈቀደለት ፋብሪካ በሚጎበኙበት ጊዜ ሥራው እንዴት እንደሚከናወን ለማወቅ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የዕቃ አወጣጡን ወይም የማስረከብ ሂደቶችን ይመልከቱ። የማስረከቢያ ሰነዱ ቁጥር እና የደረሰኙ ቁጥር ለእያንዳንዱ ደረሰኝ ከሚመደበው ራሱን የቻለ የማስረከቢያ ሰነድ ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል። (ስለዚህ ለምሳሌ አንድ የጭነት ተሽከርካሪ ሦስት ዙር ጭነት ይዞ ቢወጣ ሦስት የተለያዩ የማስረከቢያ ሰነዶች እና ሦስት የተለያዩ ደረሰኞች ሊኖሩ ይገባል ማለት ነው)።

እንዲሁም ዕቃዎቹ ወደታሰበው ቦታ ለመድረሳቸው ማረጋገጫ ሊኖር ይገባል። ስለዚህ ከዚህ ቀደም ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን በተመለከተ ምርመራ በሚያካሂዱበት ጊዜ እያንዳንዱ የማስረከቢያ ሰነድ ተቀባዩ መረከቡን በፊርማ ያረጋገጠበት ቅጂ ያለው መሆኑን ያረጋግጡ።

ምንም እንኳን ተረካቢው ደንበኛ የኤክሳይስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የተፈቀደለት አምራች ባይሆንም፣ የኤክሳይስ ታክስ አጣሪ ባለሙያዎች በተፈቀደለት አምራች የተያዙትን የማስረከቢያ ሰነዶች የአዲት ሂደት መከታተል፣ እንዲሁም ወደ ደንበኞቹ በአካል በመሄድ የማስረከቢያ ሰነዶቹ ቅጂ እንዳላቸው እና የዕቃዎቹ መጠንም በደረሰኞቹ እና በማስረከቢያ ሰነዶቹ ላይ ከተጠቀሰው መጠን ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

ሥራው በሚከናወንበት ቦታ በሚገኙበት ጊዜ የማስረከቢያ ሰነዶቹን እና ደረሰኞቹን በአካል ያረጋግጡ። ከዚህ ቀደም የተደረጉ ግብይቶችን በተመለከት ዕለታዊ የኤክሳይስ ታክስ መዝገቡን በመመልከት የማስረከቢያ ሰነዶቹን እና በእያንዳንዱ የማስረከቢያ ሰነድ ላይ የተጠቀሰውን የእያንዳንዱን የዕቃ ዓይነት ብዛት ከደረሰኞቹ እና ዕቃዎቹ ከተሸጡበት ዋጋ ጋር ያስታርቁ። የእነዚህ ሽያጮች ዋጋ ለሌሎቹ ጥቅም ላይ ከዋለው ዋጋ ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።

እነዚህ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎቹ በሙሉ ዕቃዎቹን የገዛውን አካል ማንነት፣ ዕቃዎቹ የተላኩበትን አድራሻ (እንዲሁም የዕቃዎቹን ዓይነት እና መጠን) የሚያሳይ ደረሰኝ እና የማስረከቢያ ሰነድ ሊኖራቸው ይገባል።

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation Center

ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ዕቃዎችን በተመለከተ አምራቹ ዕቃዎቹ ወደ ውጭ ሀገር እንደተላኩ የሚያሳይ ማስረጃ መቀበል አለበት። በዚህም መሠረት ዕቃዎቹ ወደ ውጭ ሀገር መላካቸውን የሚያረጋግጥ ተገቢው የጉምሩክ ሰነድ መኖር አለበት።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት መረጃ የማይገኝ ከሆነ በዕቃዎቹ ላይ የተጣለው የኤክሳይስ ታክስ መከፈል አለበት።

የኤክሳይስ ታክስ አዋጁ አንቀፅ 33 እንደሚደነግገው አንድ ሰው ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ገዝቶ ነገር ግን ዕቃዎቹን ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ ባልሆነ አግባብ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ ተገቢውን የኤክሳይስ ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት።

በመሆኑም በየጊዜው የኤክሳይስ ታክስ ማረጋገጫ ጉብኝቶች በሚካሄዱበት ወቅት የዕቃዎቹ ሁሉም የአቅርቦት ሰንሰለቶች እና የአዲት መከታተያ መዝገብ እንዲሁም ሰነዶች ክትትል ሊደረግባቸው እና ሊረጋገጡ ይገባል።

ይህም ማለት የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ከኤክሳይስ ታክስ ነፃ መብት ወዳለው ሰው መድረሳቸውን የሚያሳየው ደረሰኝ/የማስረከቢያ ሰነድ ተጣርቷል፤ እንዲሁም ዕቃዎቹንም ትክክለኛው ሰው መረከቡን ለማረጋገጥ ደረሰኙ/የማስረከቢያ ሰነዱ ተረጋግጧል እንደ ማለት ነው።

በአንቀፅ 33 መሠረት ማንኛውም ጥፋት የፈፀመ ሰው ማለትም የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ ለሆነ ዓላማ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ እቃዎቹ በተሸጡበት ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ በዋሉበት ቀን ፀንቶ በሚሰራበት የማስከፈያ ልክ መሰረት የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል አለበት።

12ለ.3. ማጠቃለያ

ከተፈቀደለት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በጠቅላላ ክትትል ሊደረግባቸው እና ሊረጋገጡ ይገባል። ይህም የገቢዎች ሚኒስቴርን፣ ወደ ገበያ ለመቅረብ ወጪ ለተደረጉ ዕቃዎች ትክክለኛው የኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያ እንደቀረበ እና እንደተከፈለ፣ የኤክሳይስ ታክሱ ሳይከፈል ወጪ ለተደረጉ ዕቃዎች ደግሞ ዕቃዎቹ በትክክል ወደ ተገቢው ስፍራ መድረሳቸውን በቀላሉ ለማረጋገጥ ያስችላል።

ይህም ከፋብሪካው ወጪ ተደርገው ወደ ደንበኛው የሚደርሱ ዕቃዎችን መከታተልን እንዲሁም በተፈቀደለት አምራች እና በደንበኛው መካከል ያሉትን የማስረከቢያ ሰነዶች ማመሳከርን ይጠይቃል።

የማስረከቢያ ሰነዱ የማይገኝበት ማናቸውም ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ በዕቃዎቹ ወይም ግብይቶቹ ላይ ሊከፈል የሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዕቃ መጣቢትና ደህመንቱቨን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል ዓሥራ ሦስት፡ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች

ክፍል 13ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

13ሀ.1. መግቢያ

በሀገር ውስጥ ከሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች በሚመረቱ የቢራና የወይን ምርቶች ላይ የተጣለው የሀገር ውስጥ የኤክሳይስ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ቅናሽ የተደረገበት ነው።

13ሀ.2. የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች

13ሀ.2.1. ቢራ

በመመሪያ 1007/2015 ሰንጠረዥ መሰረት በቢራ ላይ ሁለት ዓይነት ኤክሳይስ ታክስ ማስከፈያ መጣኔዎች አሉ፡-

- በኢትዮጵያ ውስጥ በተመረተ/በበቀለ ገብስ ብቻ የተመረተ ቢራ፡፡
- ውሃን ሳይጨምር ከክብደቱ ቢያንስ 75% የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን የያዘ ቢራ፡፡

ቢራው በአብዛኛው ከውጭ ሀገር በመጡ ግብዓቶች የተመረተ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ የቢራውን የፋብሪካ ዋጋ 40% ወይም በአንድ ሊትር 28 ብር በንፅፅር የሚበልጠው መጠን ተፈፃሚ ይሆናል።

በሀገር በቀል ጥሬ ዕቃዎች ለሚመረት ቢራ ዝቅ የተደረጉት ሁለቱ የማስከፈያ መጠኖች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡-

- በኢትዮጵያ ውስጥ በተመረተ/በበቀለ ገብስና ብቻ የተመረተ ቢራ የፋብሪካ ዋጋውን 35% ወይም በአንድ ሊትር 23 ብር።
- ውሃን ሳይጨምር ከክብደቱ ቢያንስ 75% የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን የያዘ ቢራ የፋብሪካ ዋጋውን 30% ወይም በሊትር 21 ብር ይከፈልበታል።

13ሀ.2.2. ወይን

ውሃን ሳይጨምር ከክብደቱ ቢያንስ 75% የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን የያዘ ወይን፡፡

የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎችን በግብአትነት በመጠቀም የተመረተ ወይን ከመደበኛው 40% የፋብሪካ ዋጋ ባነሰ መልኩ 30% የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል።

13ሀ.3. የስሪት ሀገር ማረጋገጫ

አምራቾች ቅናሽ የተደረገበትን የኤክሳይስ ታክስ ስሌት የሚያከናውኑባቸውን የምርት ዓይነቶች/ብራንዶች ለይተን ማወቅ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም አምራቾቹ ለእያንዳንዱ የምርት ዓይነት በጥሬ ዕቃነት የተጠቀሟቸው ግብዓቶች በእርግጥም በሀገር ውስጥ የተመረቱ መሆናቸውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል። በተጨማሪም ገብሱ በብቅል መልክ እንዲዘጋጅ የተደረገው በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

13ሀ.4. የማስረጃ ግምገማ (Evidence of Review)

ሁሉም የቢራና የወይን አምራቾች በምርት ሂደቱ ውስጥ የሚጠቀሟቸውን ጥሬ ዕቃዎች በአግባቡ እንዲመዘግቡ ሕጉ ያስገድዳቸዋል።

የተጠቀሙት የጥሬ ዕቃ መጠን እና መጨረሻ ላይ ከጥሬ ዕቃዎቹ ይገኛል ተብሎ የሚገመተው የምርት መጠን ተመጣጣኝ መሆን ይኖርበታል።

የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች ተጠቅመው በማምረታቸው ዝቅተኛ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፍሉ የተፈቀደላቸው አምራቾች የሚከተሉትን መረጃዎች መዝግበው መያዝ አለባቸው፡-

- ያስገቧቸውና የተጠቀሟቸውን የጥሬ ዕቃዎች ዝርዝር፤
- ወደ ሀገር ውስጥ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ዝርዝር፤
- ከአቅራቢው የተረከቧቸውን ጥሬ ዕቃዎች የሚያሳዩ የማስረከቢያ ሰነዶች ቅጂዎች፤
- ጥሬ ዕቃዎቹ ከየት እንደመጡ የሚጠቁሙ ከአቅራቢዎቹ የተቀበሏቸውን የግዢ የደረሰኞች ቅጂዎች::

አምራቾች እነዚህን መረጃዎች መዝግበው ያላስቀመጡ ከሆነ ዝቅተኛውን የኤክሳይስ ታክስ መጠን እንዲከፍሉ አይፈቀድላቸውም። ይልቁንም ቢራው ወይም ወይኑ ከውጭ ሀገር እንደመጣ ታሳቢ ተደርጎ መደበኛውን የኤክሳይስ ታክስ መጠን እንዲከፍሉ ይገደዳሉ።

የኢትዮጵያ መንግስት ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ይሕመንቴሽን ቁ.1 ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል 13ለ፡ ቅናሽ የተደረገበትን የማስከፈያ መጠን መቆጣጠር

13ለ.1. ወይን እና ቢራ

የወይን ወይም የቢራ ፋብሪካዎችን ሲጎበኙ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውኑ፦

- የጥሬ ዕቃ አቅራቢዎችን ዝርዝር ያዘጋጁ፤
- የጥሬ ዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶችን የተወሰነ ናሙና ይገምግሙ (ካለፉት ሦስት ወራት ጀምሮ የነበሩትን የጥሬ ዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶችን)፤
- የአቅራቢዎቹን ስም፣ የጥሬ ዕቃውን ዓይነት እና ብዛት ማስታወሻ ይያዙ፤
- የጥሬ ዕቃው በተጨባጭ በኢትዮጵያ ውስጥ መመረቱን የሚያሳይ ማስረጃ መኖሩን ያረጋግጡ፤
- ጥሬ ዕቃው ገቢ የተደረገበት መዝገብ ላይ የተቀመጠውን ቀን እና ዝርዝር መረጃ በእያንዳንዱ ማስረከቢያ ሰነድ ላይ ካለውን የዕቃ ብዛት ጋር ያመሳክሩ።

ለምርመራ በመረጣችሁት የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ፋብሪካው የገቡትን ጥሬ ዕቃዎችን ምረጃ በሙሉ ከያዛችሁ በኋላ እነዚያን ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም ምን ዓይነት ምርቶች እንደተመረቱ መጣራት ያስፈልገዋል። ከዚያም በአመራረት ሥራው ላይ ተገቢውን ያህል መጠን የጥሬ ዕቃ ለግብዓትነት መዋሉን ማረጋገጥ።

ምዝገባዎቹ ላይ ስህተቶችና የጎደሉ መረጃዎች ሲያጋጥሙ ይህንኑ በሪፖርት ላይ በመግለጽ የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድ ለክፍል ኃላፊው ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

13ለ.2. ማጠቃለያ

የቢራ እና የወይን ምርቶች ላይ የተደረገው የኤክሳይስ ታክስ ቅነሳ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሀገር ውስጥ የማምረት ልምምድ በማሳደግ፣ እንዲሁም በፋብሪካዎች የሥራ እድልን በመፍጠር እና አርሶ አደሮችም ምርታቸውን እንዲሸጡ የገበያ እድልን በማመቻቸት ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው።

ይሁንና እነዚህ ጥሬ ዕቃዎች በእርግጥም የተመረቱት ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል። ካልሆነ ግን በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ላይ የሚደረግ የታክስ መጣኔ ቅነሳ ሥርዓት ጽንሰ-ሐሳብ የተጣሰ ይሆናል።

ስለዚህ ደረሰኞችና የማስረከቢያ ሰነዶች በአግባቡ መያዝ አለባቸው። ጥሬ ዕቃዎቹ በቀጥታ ከአርሶ አደሮች ሳይሆን፣ ከአቅራቢዎች የተገዙ ከሆነ፣ ይህንን የሚያስረዳ ሰነድ ሊኖር ይገባል።

ማስታወሻ፦ በጥሬ ዕቃ ላይ ስለሚደረግ ምርመራ ተጨማሪ መረጃ በኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ላይ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መገልገያና ያስመንጪሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል ዓሥራ አራት፡ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች

ክፍል 14ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

14ሀ.1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ የኤካሳይስ ታክስ ሊከፈልባቸው የሚገባ በርካታ ምርቶች ይኖራሉ። ነገር ግን አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ጥሬ እቃዎች የኤክሳይስ ታክስ ሳይከፍሉ ከቦታ፣ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት ምቹ ስርዓት የለም። ይህ ባለመሆኑም አንዳንድ ጥሬ ዕቃዎች ወደ ፋብሪካ ገብተው ለግብዓትነት ከመዋላቸው በፊት የኤክሳይስ ታክስ ይከፈልባቸዋል። በእዚህም ጥሬ ዕቃዎች ግብዓትነት የተመረቱት ምርቶች ደግሞ እንደገና የኤክሳይስ ታክስ እንዲከፍሉ ሆኗል።

ለእነዚህ ምሳሌ የሚሆኑት ጥሬ ዕቃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የአልኮል መጠጦችን ለማምረት የሚውል ምንም ያልተቀላቀለበት ንፁህ አልኮል፤
- ስኳር፤ እና
- የትንባሆ ቅጠል።

14ሀ.2. ሕጉ፡ አንቀጽ 14

የኤክሳይስ ታክስ አዋጁ አንቀፅ 14 የኤክሳይስ ታክስ የተጣለባቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ ታክሱ እንዴት እንደሚተገበር ያስረዳል።

ይህም እንደሚከተለው ተደንግጓል፡-

1/ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይስ ታክስ በሚከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ ወይም በሀገር ውስጥ በተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች ላይ የኤክሳይስ ታክስ የከፈለ እንደሆነ እና እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች የመጨረሻውን ምርት (ከዚህ በኋላ "የመጨረሻ ምርት") ለማምረት በግብዓትነት የተጠቀመባቸው ከሆነ፣ በጥሬ ዕቃዎቹ/ግብዓቶቹ ላይ የተከፈለው ታክስ በመጨረሻ ምርቶቹ ላይ ከሚከፈለው የኤክሳይስ ታክስ ጋር እንዲቀናነስ ይደረጋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው አልኮልን፣ ትንባሆ እና ስኳርን አይጨምርም።

14ሀ.2.1. አንቀጽ 14፡ የአምራች ግዴታዎች

የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀጽ (1) የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበትን ምርት ለማምረት የዋለ ጥሬ ዕቃ በቅድሚያ የኤክሳይስ ታክስ ከተከፈለበት፣ የመጨረሻው ያለቀለት ምርት በሚወጣበት ጊዜ በጥሬ ዕቃው ላይ የተከፈለውን ታክስ ታሳቢ በማድረግ ያለቀለት ምርቱ ላይ ይከፈል የነበረው የኤክሳይስ ታክስ ይቀናነሳል።

ይሁን እንጂ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) ከታች በተዘረዘሩት ዕቃዎች ላይ የተከፈለ የኤክሳይስ ታክስ ግን ተቀናናሽ እንደማይሆን ይገልጻል፡-

- አልኮል
- የትንባሆ ቅጠል፤ እና

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 ★ የሰነድ መረጃዎችና ዶክመንቴሽን ★ Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- ስኳር::

ስለዚህ በጥሬ ዕቃዎቹ ላይ ከመነሻው የተከፈለው የኤክሳይስ ታክስ፣ በመጨረሻው ያለቀለት ምርት የሚወጣው ዋጋ ላይ ተጨምሮ ስለመሰላቱ ማስረጃ መቅረብ አለበት።

14ሀ.3. የአምራች ግዴታዎች፡ ተቀናናሽ/ተመላሽ ግብር አንዴት ይከናወናል?

የኤክሳይስ ታክስ ለሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች **ከአልኮል፣ ከትንባሆና ከስኳር ውጪ** የተከፈለው የኤክሳይስ ታክስ፣ ገንዘቡ ተመላሽ ሊሆን ይችላል። ነግር ግን አምራቹ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለበት፡-

- በጥሬ እቃዎቹ ላይ የኤክሳይስ ታክስ መከፈሉን በማስረጃ ማረጋገጥ፤ እና
- የታክስ ተመላሽ ወይም ማካካሻ የተጠየቀባቸው ጥሬ ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ፣ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ለማምረት እንደዋሉ በማስረጃ ማረጋገጥ አለበት።

እንዲሁም የኤክሳይስ ታክሱን ለማስላት የተጠቀመው የዋጋ መጠን ትክክለኛ እና መረጋገጥ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

ተመላሽ የሚደረገው የኤክሳይስ ታክስ ክፍያ፣ ተመላሽ የሚሆነው በኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያ ቅጹ በተቀናናሽነት በተቀመጠው ላይ ነው።

14ሀ.4. ማጠቃለያ

ይህ ከተመላሽ ሂደት ጋር ተመሳሳይ ሂደት እና ከአዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ ስትራቴጂ እና የቁጥጥር ዘዴ ጋር የሚጣጣም ሲሆን ይህም በገቢዎች ሚኒስቴር እና በተፈቀደላቸው አምራቾች መካከል ትስስር እና ግልፅ የሆነ የግንኙነት መስመር ይገነባልናል።

ይሁንና ግዴታቸውን የሚወጡ አምራቾች (ግዴታውን የሚወጣ አምራች ማለት ሕጎችን የሚከተል እና በማረጋገጫ ጉብኝት ወይም በመደበኛ አዲት ወቅት ምንም ዓይነት ጉድለት ያልተገኘበት ነው) ከኤክሳይስ ታክስ ማስታወቂያው ጋር በሚጣጣም መልኩ የተቀናናሹ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ።

ሆኖም ይህን መንገድ የሚከተሉ ሁሉም አምራቾች በየጊዜው ጉብኝት ሊደረግባቸው እና የተቀናናሽ ቁጥሩም ሊረጋገጥ ይገባል::

የሒሳብ ምርመራዎቹ ግልፅነት የሆነ የአዲት መከታተያ የማሳዩ ከሆነ ቅጣቶች መጣል ያለባቸው ሲሆን ለአምራቹም የተቀናናሽ መብት ተጠቃሚ እንደማይሆን ሊገለፅለት ይገባል። ይሁን እንጂ ቀጥሎ በሚገኘው በክፍል 15 የተገለፀውን የተመላሽ ሂደቶችን እንዲከተል መደረግ አለበት።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዳታ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል 14ለ፡ ተቀናናሹን መቆጣጠር

14ለ.1. መግቢያ

ቢያንስ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ጥሩ የታክስ ሕግ ተገዢነት ሬከርድ ያላቸው ግዴታቸውን የተወጡ አምራቾች ብቻ በታክስ ማሳወቂያ ቅጹ ላይ ያለውን የተቀናናሽ መስመር ሊጠቀሙ ይችላሉ።

አምራቹ በታክስ ማሳወቂያ ሰነዱ የተቀናናሽ መስመር ላይ ያሰፈራቸው የኤክሳይስ ታክስ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ብዛት ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ አለበት።

ይህ የማይረጋገጥ ከሆነ አምራቾች ይህን መብት አላግባብ እንዲጠቀሙበት ሊያደርግ ይችላል።

14ለ.2. ተቀናናሹን ማረጋገጥ

ተቀናናሹን ለማረጋገጥ አምራቹ ላይ ማጣራት በሚያደርጉበት ጊዜ የሚከተሉትን ማከናወን አለብዎት፡-

- የማካካሻ ጥያቄው ከየትኛው የኤክሳይስ ክፍያ ጋር እንድተያያዘ መረዳት አለባችሁ። ለምሳሌ አምራቹ የማካካሻ ጥያቄ ያቀረበው ወደ ውጭ ሀገር ለተላኩ ወይም ለተወገዱ የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች ከሆነ ጥያቄው ተገቢነት አይኖረውም። ጥያቄው መቅረብ ያለበት በማካካሻ ሳይሆን በተመላሽ መሆን ይኖርበታል።
- በተፈቀደለት አምራች ጥቅም ላይ የዋሉትን የኤክሳይስ ታክስ የሚከፈልባቸውን ጥሬ ዕቃዎች መለየት።
- የአቅራቢዎችን ዝርዝር መቀበል።
- ጥሬ ዕቃዎቹ ወደ ፋብሪካው መግባታቸውን የሚያሳዩ የስረከቢያ ሰነዶችን መገምገም አለባችሁ።
- ወደ ፋብሪካው የገባውን የጥሬ ዕቃ ብዛትና ዓይነት፣ ከተመዘገበው የጥሬ ዕቃ ብዛትና ዕይነት ጋር ማመሳከር።
- የገባውን ጥሬ እቃ በመጠቀም የተመረቱት ምርቶች የትኞቹ እንደሆኑ ማጣራት አለባችሁ።
- የኤክሳይስ ታክሱ የተከፈለበትን የዋጋ መጠን ማጣራት።
- የማካካሻውን መጠን መመርመር።
- አምራቹ የታክስ ማካካሻውን ከፍ ለማድረግ ሲል ደረሰኙ ላይ ያለውን የዋጋ መጠን ከፍ ሊያደርግ ይችላል። ይህ እንዳይሆን ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይኖርባችኋል።
- ለማካካሻው ብቁ ያልሆኑትን ብቁ እንደሆኑ አድርገው በተሳሳተ መንገድ ሊመድቡ ስለሚችሉ ያንን ማጣራት ያስፈልጋል።
- በአልኮል፣ በትንባሆ ቅጠል እና በስኳር ጥሬ ዕቃዎች ላይ የታክስ ማካካሻ ወይም ተመላሽ እንዳልተጠየቀባቸው ማጣራት።
- በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ግብዓትነት የተሠራው ያለቀለት ምርት ላይ ያለው ዋጋ፣ በጥሬ ዕቃው ላይ የሚከፈለውን የኤክሳይስ ታክስ የሚጨምር መሆኑን አረጋግጡ።

ዝርዝር ማስታወሻ ይያዙ። ሁሉም የተመዘገቡት መረጃዎች ግልፅ እና በቀላሉ የሚነበቡ መሆናቸውን አረጋግጡ። ጥሬ ዕቃዎቹ መቼ እንደገቡና ከፍያ መቼ እንደተፈፀመባቸው የሚያሳዩ መረጃዎችን ያረጋግጡ።

14ለ.3. ልዩነቶች

የኤክሳይስ ታክስ ማካካሻ መደረግ በማይገባበት ሁኔታ፣ ማካካሻ ተደርጎ ከሆነ፣ ወይም ጥሬ ዕቃው ላይ ያለው ዋጋ የኤክሳይስ ታክሱን ዋጋ ያላካተተ ከሆነ፣ ቅጣት መጣል እና ዝቅ ተደርጎ ለቀረበው የኤክሳይስ የታክስ ውሳኔ መሰጠት አለበት::

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ክፍል ዓሥራ አምስት፡ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ (የአዋጁ አንቀፅ 30 እና 31 ንዑስ አንቀፅ 1-7)

ክፍል 15ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

15ሀ.1. መግቢያ

የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ የሚችልባቸው በጣም ውስን ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- ዋናው የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎ ከሆነ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከጥቅም ውጪ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ፤
- ገዢው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በተፈቀደለት አምራች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ፤
- ማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው አመልካቹ የሚከተሉትን ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ ነው፡-
  - የኤክሳይዝ ታክሱ የተከፈለ መሆኑን፤ እና
  - የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የተመላሽ ጥያቄን ለማቅረብ ብቁ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ያጋጠመ መሆኑን፡፡

ማስታወሻ፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት ጥቅም ላይ በሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ (ከኤቲል አልኮል፣ የትንባሆ ቅጠል እና ስኳር በስተቀር) የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ የሂሳብ ማስታረቂያው ግዴታን ያለመወጣትን ካላሳየ በስተቀር በኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያው ላይ መቀናነስ አለበት፡፡ በማስታወቂያ ቅጹ ውስጥ ያለውን የማካካሻ/ማቀናነሻ መስመር መጠቀም የተፈቀደ መብት ሲሆን አላግባብ ጥቅም ላይ ከዋለ ግን በዚህ ክፍል ውስጥ የተገለፀው የተመላሽ ሂደት ብቻ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

15ሀ.2. የሕጉ አግባብ እና የአምራች ግዴታዎች

አንቀጽ 30 የኤክሳይዝ ታክስ መቼ ተመላሽ መደረግ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ አመልካቹ የሚከተሉትን ማረጋገጥ ካልቻለ በስተቀር ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊከፈለው አይገባም፡-

- የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈሉን፤ እና
- ዕቃዎቹ ተመላሽ በሚደረግበት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ መዋላቸውን፡፡

በአንቀጽ 30 እንደተገለፀው በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ ሀገር የመጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለባቸው በኋላ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ያጋጠመ መሆኑን የታክስ ባለስልጣኑ **ያረጋገጠ እንደሆነ**፣ በአምራቹ ወይም በአስመጪው በሚቀርብ የጽሑፍ ማመልከቻ መሠረት የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል፡-

- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ)፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት፣ ወደ ኢትዮጵያ በመጓጓዝ ላይ እያሉ ዕቃዎቹ ከጥቅም ውጭ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ ወይም በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች ከጥቅም ውጭ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ ወይም በሽያጭ ውሉ መሠረት ገዢው ዕቃውን ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፡፡
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (1)(ለ)፡ የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለ በኋላ ፈቃድ በተሰጠው ወይም

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በተመዘገበ አምራች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት የዋሉ እንደሆነ::

- ነገር ግን ይህ ለተፈቀደለት አምራች ብቻ እንዲኖር የተደረገ ስለሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ጥቅም ላይ ውለው ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ በመጀመሪያ ሊመረመር የሚገባው ነገር የሚመረቱትን ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑትን ዕቃዎች የማምረቱ ሥራ በተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የተካሄደ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ የተከፈለ መሆኑን እና ተከፍሎ ከሆነ ለምን እንደተከፈለ ማረጋገጥ ነው::
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (2)፡ የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች/አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክሱን የከፈለ እና ለእነዚህ ዕቃዎች/አገልግሎቶች ከገዢው ምንም ዓይነት ክፍያ ያልተቀበለ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ የቻለ እንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክስ ባለስልጣኑ በጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል:: የታክስ ባለስልጣኑም የተፈቀደለት ሰው በእነዚህ ዕቃዎች/አገልግሎቶች ላይ ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ያልተቀበለ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል::
- ይህ "ሊሰበሰብ የማይችል ዕዳ"ን የሚመለከት አንቀጽ ነው:: የኤክሳይዝ ታክስ ጽንሰ-ሃሳብ አምራቹ የኤክሳይዝ ታክሱን ለታክስ ባለስልጣኑ ከፍሎ ያንን የታክስ ወጪ በዕቃው ዋጋ ላይ ለተጠቃሚው ማስተላለፍ ነው:: ደንበኛው ለአምራቹ ያልከፈለበት ሁኔታ ሲኖር ከሽያጮች ጋር በተያያዘ አምራቹ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ደንበኛው ተመላሽ እንዲያደርግ ግዴታ ይጣልበታል::
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (3)፡ የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ከእነዚህ በቀደመው ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡- (ሀ) ዕቃዎቹ ከተሸጡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፤ ወይም (ለ) ገዢው የከሠረ መሆኑ በሕግ በተረጋገጠበት ጊዜ::
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (4)፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርበው ማመልከቻ በፀደቀው ቅጽ መሠረት፤ እና የኤክሳይዝ ታክሱ በተከፈለ በዓሥራ ሁለት ወራት ውስጥ መቅረብ አለበት::
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (5)፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተመላሽ የሚደረገው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን የሚወሰነው በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ይሆናል::
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (6)፡ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ተመልሰው ወደ ውጭ ሀገር በተላኩ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ ከሆነ ወደ ውጭ ሀገር በተላኩት ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ታክስ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተመላሽ ይሆናል::"
- አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (7)፡ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከገዢው ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተቀበለ ከሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ በተቀበለው መጠን ተመላሽ የተደረገለትን የኤክሳይዝ ታክስ ለታክስ ባለስልጣኑ መመለስ አለበት::

15ሀ.3. ለተመላሽ የይገባኛል ጥያቄ ብቁ ስለመሆን

15ሀ.3.1. ተመላሽ የሚደረግባቸው ዕቃዎች

15ሀ.3.2. ተመላሽ የማግኘት መብት ያለው ሰው

የኤክሳይዝ ታክሱን በቀጥታ ለታክስ ባለስልጣኑ የከፈለው አምራች ብቻ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ ሊደረግለት ይችላል:: በሌላ በኩል የኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ጋር በተያያዘ የኤክሳይዝ ታክሱ በአስመጪው ከተከፈለ ለአምራቹ የሚሰጠው ደረሰኝ የኤክሳይዝ ታክስ መጠኑን ይጨምራል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክሱ ለአስመጪው የተከፈለው በተፈቀደለት አምራች ከሆነ እና ደረሰኙ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈሉን በግልፅ የሚያሳይ ከሆነ (እና አስመጪው ዕቃውን ከውጭ ሀገር ሲያስገባ ለታክስ ባለስልጣኑየኤክሳይዝ ታክስ መክፈሉን የሚያሳይ ማስረጃ ካለ) አምራቹ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግለት ሊጠይቅ ይችላል::

ይሁን እንጂ ከላይ ያሉት ሁሉም ካልተረጋገጡ በስተቀር ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መከፈል የለበትም:: በዚህም መሠረት ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ የገቡበት ሰነዶች፣ የጉምሩክ እና የኤክሳይዝ ቀረጥ ክፍያዎች፣ ከዕቃዎቹ ጋር ተዛማጅነት ያለው ደረሰኝ እና የማስረከቢያ ሰነድ መቅረብ አለባቸው::

15ሀ.3.3 ተመላሽ የሚደረግባቸው ዕቃዎች

ሕጉ ተመላሽ እንዲደረግ የሚፈቅደው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የየኤክሳይዝ ታክሳቸው ከተከፈለ በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው:-

- ወደ ውጭ ሀገር ሲላኩ (በጉምሩክ አዋጁ ውስጥ የተቀመጡትን ደንቦች ይከተሉ)፤
- ከጥቅም ውጪ ሲሆኑ፣ ሲሠረቁ ወይም ጥሩው ዕቃዎቹን ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፤
- ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት ጥቅም ላይ ሲውሉ::

15ሀ.4. የተመላሽ ሂደት

15ሀ.4.1. ቅድመ-ማስታወቂያ

በተፈቀደለት አምራች እና በታክስ ባለስልጣኑ መካከል የሚኖር ግንኙነት ግልፅ እና ወቅቱን የጠበቀ እንዲሆን ያስፈልጋል:: በዚሁ መሠረት የተፈቀደለት አምራች የተመላሽ ጥያቄን የሚያስከትል ማንኛውም ሂደት ከመከናወኑ በፊት ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት::

ይህ የታክስ ባለስልጣን (ያሉት ሀብቶች ይህን ለማድረግ የሚፈቅዱ ከሆነ) ሂደቱ ከመከናወኑ በፊት ዕቃዎቹ የተቀመጡበትን ፋብሪካ እንዲጎበኝ ያስችለዋል::

15ሀ.4.2. በተመላሽ ቅጹ ላይ የሚኖሩ መረጃዎች

የቅድመ-ማስታወቂያ ቅጹ የሚከተሉትን ያካትታል:-

- የተመላሽ ጥያቄ አቅራቢው ስም እና አድራሻ፤
- የተመላሽ ጥያቄ አቅራቢው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- የተመላሽ ጥያቄው ምክንያት (ወደ ውጭ ሀገር መላክ ወይም የታቀደ ውድመት)፤
- የተመላሽ ጥያቄው የቀረበባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ብዛት እና ዓይነት፤
- በዕቃዎቹ ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን፤
- ተመላሽ የሚደረግበት ቀን እና ሰዓት::

ጥያቄው ከአገልግሎት ውጪ ከተደረጉ ወይም ከተወገዱ የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለባቸው ዕቃዎች ጋር ለተገናኙ ጉዳዮች ከሆነ ጥያቄ አቅራቢው የአወጋገዱን ዘዴ ማብራራት አለበት::

ለቀረበው ጥያቄ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት አምራቹ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል:: ነገር ግን እዚህ ደረጃ ላይ ተሞልቶ የቀረበው የቅድመ-ማስታወቂያ ቅጽ ብቻ ነው

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation

የሚያስፈልገን::

15ሀ.4.3. የማስታወቂያ ጊዜ

ቅጹ ፈቃድ በተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች መቅረብ ያለበት ሲሆን ገቢ ለመደረጉ ማረጋገጫነትም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ማህተም መደረግ ይኖርበታል::

15ሀ.4.4. የተመላሽ ጥያቄ

ቅድመ-ማስታወቂያው ከቀረበ እና የማስታወቂያ ጊዜው ካበቃ በኋላ አምራቹ ከተመላሹ ጋር የተገናኙ ሂደቶችን ሊያከናውን የሚችል ሲሆን ሂደቱ ከተጠናቀቀም በኋላ ዋናውን የተመላሽ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል::

የተመላሽ ጥያቄው የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማረጋገጫ እና ዕቃዎቹ የተመላሽ ጥያቄን ለማቅረብ በተፈቀደ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ከሚያሳይ ማስረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት:: እንዲሁም ጥያቄው በቅድመ-ማስታወቂያ ቅጹ ላይ ላለው የዕቃዎቹ ትክክለኛ ዓይነት እና መጠን መሆን አለበት::

15ሀ.4.5. ደጋፊ ሰነዶች

አምራቹ የመጨረሻውን የተመላሽ ጥያቄ ሲያቀርብ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት:-

- በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን፤
- የኤክሳይዝ ታክሱ ቀደም ሲል የተመላሽ ጥያቄ ያልቀረበበት ስለመሆኑ፤ እና
- ዕቃዎቹ ተመላሽ በሚያስገኝ የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው::

15ሀ.4.6. የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማረጋገጫ

የሚከተሉት ሰነዶች መቅረብ አለባቸው:-

- የኤክሳይዝ ታክሱ የተከፈለበት የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ፤
- የዕቃዎቹን አወጣጥ የሚያሳይ ዕለታዊ የኤክሳይዝ ታክስ ሂሳብ መዝገብ፤
- ከእያንዳንዱ የዕቃ አወጣጥ ጋር የተያያዘ የማስረከቢያ ሰነድ እና ደረሰኝ::

እነዚህ ሰነዶች ሊቀርቡ ካልቻሉ ምንም ዓይነት ተመላሽ ሊደረግ አይችልም::

ዕቃዎቹ የተሸጡበት ትክክለኛ ዋጋ እንዲረጋገጥ የኤክሳይዝ ታክሱ ከፋብሪካ በሚወጡ ዕቃዎች ላይ መቼ እንደተከፈለ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው:: የኤክሳይዝ ታክሱ የተሰላበትን ዋጋ በትክክል መገምገም ካልቻልን ማንኛውንም የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መመለስ አንችልም::

የተመላሽ ጥያቄ የሚያቀርቡ ማናቸውም አምራቾች እነዚህ ዝርዝር መረጃዎች እና ተመላሹ የተጠየቀባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈሉን የሚያረጋግጥ የመከታተያ እና መቆጠጠሪያ ዘዴ ሊኖራቸው ይገባል: : ይህ ማስረጃ በማይኖርበት ሁኔታ ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ተመላሽ ሊደረግ አይችልም::

በዚህም መሠረት ማስረጃ የማቅረቡ ጫና በአምራቹ ላይ የተጣለ ግዴታ ይሆናል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ይክሙንቲሽን ዋ/ሥ
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation

15ሀ.4.7. ዕቃዎቹ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋላቸው ማረጋገጫ

ዕቃዎች ከአገልግሎት ውጪ የሚደረጉበትን ወይም የሚወገዱበትን ሁኔታ በተመለከተ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ለአካቢቢ ደህንነት ተስማሚ በሆነ መንገድ መወገድ አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የአልኮል መጠጦችን በቀጥታ ወደ ፍሳሽ ማስወገጃዎች ማፍሰስ አይቻልም፡፡

የማስወገዱ ሥራ የተከናወነው በሦስተኛ ወገን ከሆነ የማስወገጃው የምስክር ወረቀት መቅረብ አለበት፡፡

የማስወገዱ ሥራ ወይም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን የማምረት ሥራው የተከናወነው በፋብሪካው ውስጥ ከሆነ የማስወገጃ ጊዜውን እና ዘዴውን የተመለከቱ መዝገቦች ተይዘው ከተመላሽ ጥያቄው ጋር መቅረብ አለባቸው፡፡

በጽንሰ-ሃሳብ ደረጃ አወጋገዱ እማኝ ሊኖረው ይገባል፡፡ አምራቹም ሁሉንም የአወጋገድ/አጠቃቀም መዝገቦችን መያዝ ያለበት ሲሆን ሁሉም ማስረጃዎች እስካልቀረቡ ድረስ ምንም ዓይነት ተመላሽ አይደረግም፡፡

ሁሉም ለነዶች ከዕቃዎቹ እና ከተመላሽ ጥያቄው ጋር መገናኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ የአምራቹ ኃላፊነት ነው፡፡

ክፍል 15ለ፡ የተመላሽ ጥያቄዎችን ማረጋገጥ

15ለ.1. መግቢያ

ማንኛውም የታክስ ተመላሽ ለአንዳንድ አምራቾች ሥርዓቱን አላግባብ ለመጠቀም እንዲሞክሩ እድል ይሰጣል፡፡

አንድ አምራች የታክስ ሕግ ተገዢነትን በሚያሳይ ጊዜ ቀለል ያሉ ሂደቶች ሊፈቀዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሂደቶች የተመላሽ ክፍያው ከተፈፀመም በኋላ አዲት ሊደረግባቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም ማስረጃው የማይኖር ከሆነ ተመላሽ የተደረገው የኤክሳይዝ ታክስ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

15ለ.2. ማረጋገጫ

በቀደሙት ክፍሎች እንደተገለፀው ቀጣዮቹን ሂደቶች መከተል አለብን፡-

አንደኛ፡ አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ የሚደረግበት እንቅስቃሴ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህም እንቅስቃሴው ከመከናወኑ (ይህ የማስታወቂያ ጊዜ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ለታክስ ባለስልጣኑ ዕቃዎቹ ከመወገዳቸው ወይም ወደ ውጭ ሀገር ከመላካቸው በፊት የተከማቹበትን የማምረቻ/ማከማቻ ቦታ በአካል ለመጎብኘት እድል ይሰጣል)፡፡ አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት መጠየቅ የሚችለው አስቀድሞ ባሳወቀው ዕቃ ላይ ብቻ በመሆኑ የሚወገዱ ወይም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ወይም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ዓይነት እና መጠን ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

ሁለተኛ፡ አምራቹ የማስታወቂያው ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ መጠበቅ አለበት፡፡

ሶስተኛደረጃ ሥስት፡ የታክስ ባለስልጣኑየሚወገዱትን ዕቃዎች ለማረጋገጥ በተቻለ መጠን ብዙ አምራቾች ዘንድ ለመገኘት ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

አራተኛደረጃ አራት፡ አምራቹ ተመላሽ የሚደረግበትን ተግባር ማከናወን የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡-

- የታክስ ባለስልጣኑ የማምረቻ ቦታውን ከጎበኘ እና ዕቃዎቹን ከፈቀደ፤ ወይም

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ በማስታወቂያው ጊዜ ውስጥ ካልተገኘ::

አምስተኛ ፡ የታክስ ባለስልጣኑ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አፈሰሮች ካልተገኙ በስተቀር ተግባሩ እንዳይከናወን ሊጠይቅ ይችላል::

ስድተኛ፡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

- ቅድመ-ማስታወቂያው ከቀረበ በኋላ፤
- የማስታወቂያው ጊዜ ካለፈ በኋላ፤
- ዕቃዎቹ ከተረጋገጡ እና የተመላሽ ተግባሩ ከተከናወነ በኋላ::

በቅድመ-ማስታወቂያው ላይ የቀረቡትን ዝርዝሮች የያዘ የተመላሽ ቅጽ መላክ አለበት:: በዚህም መሠረት አስቀድሞ በተገለፀው ዕቃ ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ ብቻ ነው ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው::

ሰባተኛ፡ አምራቹ ከኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማስረጃ እና ዕቃዎቹ በተገቢው የተመላሽ ተግባር ጥቅም ላይ መዋላቸውን ከሚያሳይ ማረጋገጫ ጋር የተመላሽ ቅጹን ይመልሳል::

ስምንተኛ፡ ሁሉም ሰነዶች ተተንትነው የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ መደረግ የሚችል መሆን አለመሆኑ ውሳኔ ይሰጥበታል::

15ለ.3. ትንታኔውን ማካሄድ

የተመላሽ ሂደቱ መሟላቱን ለማረጋገጥ በሚያስፈልጉት በርካታ ሰነዶች ምክንያት የማረጋገጫ አፈሰሩ በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ የማረጋገጫ ሥራውን እንዲያደርግ ይመከራል:: ለዚሁ ተግባርም ቢያንስ ሁለት አፈሰሮች መገኘት አለባቸው::

በአምራቹ በኩል አሉታዊ ድርጊቶች ካሉ አፈሰሩ የማምረቻ ቦታውን ለቆ መውጣት እና የተመላሽ ጥያቄውን በከፍተኛ ደረጃ ውድቅ ማድረግ አለበት:: ወይም ሁሉም ተያያዥ ሰነዶች በተወሰነ ቀን ውስጥ ለሚመለከተው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍል እንዲተላለፉ ጥያቄ መቅረብ አለበት::

ለሕግ ተገዢ አለመሆን ጥያቄው ትክክል እንዳልሆነ እና ውድቅ መሆን እንዳለበት የሚያሳይ ማስረጃ ነው ተብሎ እንዲታሰብ ያደርጋል::

በርካታ የተመላሽ ጥያቄዎች ያሉ እንደሆነ ሁሉም ተያያዥ ሰነዶች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ክፍል እንዲቀርቡ ጥያቄ ማቅረብ የተሻለ ሲሆን የተመላሽ ጥያቄዎቹ በቢሮ ውስጥ ሊተነተኑ እና ሊከናወኑ ይችላሉ::

15ለ.4. የቀረቡ ሰነዶች

አምራቹ ሂደቱን መከተል ይኖርበታል፤ ስለዚህም የተመላሽ ሂደቱ ለማረጋገጫ ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ የሚከተሉት ሰነዶች የሚኖሩ ይሆናል፡-

1. የመጀመሪያው/ዋናው የቅድመ-ማስታወቂያ ሰነድ፤
2. የተመላሽ መጠየቂያ ቅጹ፤
3. የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማስረጃ፤
4. ዕቃዎቹ ተመላሽ ለመጠየቅ ብቁ በሚያደርግ መንገድ ጥቅም ላይ መዋላቸውን የሚያሳይ ማስረጃ::

- የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ በተጠየቀባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክሱ የተከፈለበትን ቀን የሚያሳዩ የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች፤
- ተመላሽ የሚያሰጡ ተግባራት ማስረጃ (ቀረጥ ተከፍሎባቸው ወደ ውጭ ሀገር ለተላኩ ዕቃዎች የኤክስፖርት ማስረጃ፤ ዕቃዎች ከአገልግሎት ውጪ የተደረጉበት ወይም የተወገዱበት ማስረጃ፤ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆነ ዕቃ ምርት ማስረጃ)::

ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ በሚይኖሩበት ሁኔታ የተመላሽ ጥያቄው ሊስተናገድ አይችልም::

15ለ.5. የቀረቡ·ት ሰነዶች ላይ የሚደረግ ማረጋገጫ

የሚከተለው ዝርዝር ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸውን አንዳንድ የማመሳከሪያ እና የማረጋገጫ ጉዳዮችን ያብራራል፡-

1. የቅድመ-ማስታወቂያው መረጃ የተመላሽ ጥያቄ ከቀረበባቸው ምርቶች ዓይነት እና መጠን ጋር ይጣጣማል?
2. መልሱ "አዎ" ከሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማስረጃ ወደሚረጋገጥበት ቀጣዩ ደረጃ መሸጋገር ይኖርበታል::
3. መልሱ "አይ" ከሆነ እና በቀረበው የተመላሽ ጥያቄ እና በቅድመ-ማስታወቂያው ላይ በተገለፀው መካከል ልዩነቶች ካሉ ሪፖርት ያድርጉ እና ስለቀጣይ እርምጃዎች ከክፍል ኃላፊዎ ጋር ይነጋገሩ:: ይህ የተመላሽ ጥያቄ ሂደቱን ያልተከተለ በመሆኑ ምክንያት ውድቅ ሊደረግ ይገባል::
4. የኤክሳይዝ ታክሱ የተከፈለ መሆኑን የሚያሳዩትን የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያዎች መመልከት ተገቢ ነው:: የኤክሳይዝ ታክሱ የተሰላበት ዋጋ እና በእያንዳንዱ ዕቃ ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ከሚወገዱ፣ ወደ ውጭ ሀገር ከሚላኩ ወይም በተፈቀደ የምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ ዕቃዎች ጋር ይጣጣማል?
5. የታክስ ባለስልጣኑ የማምረቻ/ማከማቻ ቦታው ተገኝቶ ዕቃዎቹ መወገዳቸውን ወይም ተመላሽ ለማግኘት ብቁ በሚያደርግ ተግባር ውስጥ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማየት ካልቻለ አወጋገዱን የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ·አለበት:: ይህም አወጋገዱን የሚያሳይ ቀን እና ሰዓት የታተመበት ቪዲዮ፣ ወይም ለኤክስፖርት ከሆነ በመውጫ ድንበር ላይ ማረጋገጫ የተሰጠበት አግባብነት ያለው የጉምሩክ ሰነድ፣ ወይም የተመረቱትን ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ዓይነት እና መጠን የሚያሳይ የኦዲት መከታተያ መዝገብ ሊሆን ይችላል::
6. አምራቹ የኤክሳይዝ ታክሱን የከፈለው በቅርቡ ከሆነ ከላይ ያሉትን ማረጋገጥ በጣም ቀላል ይሆናል:: ነገር ግን አንድ አምራች ከተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ የሚበልጥ የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ተመላሽ እንዲደረግለት ከመጠየቅ እንዲቆጠብ ማድረግ አለብን::

ለምሳሌ:- አንድ የቢራ አምራች በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም አንድን የቢራ ብራንድ ሊያመርት ይችላል፣ ወይም ይህ በማይገኝበት ጊዜ ከውጭ ሀገር የመጡ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ተመሳሳይ የምርት ዓይነት ሊያመርት ይችላል:: እነዚህ ሁለቱም ብራንዶች አንድ ዓይነት መለያ/ሌብል ሊኖራቸው ይችላል ነገር ግን አንደኛው ዝቅ ያለ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን ሲጣልበት ለአንደኛው ግን ሙሉው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን መከፈል አለበት::

30% ብቻ የተከፈለ በሚሆንበት ጊዜ በ40% ተመላሽ ማድረግ አንችልም::

የዕቃዎቹ ብዛት ተረጋግጦ ነገር ግን ለእያንዳንዱ ጠርሙስ የአመራረት ዘዴ ሊቀርብ የሚችል ከሆነ ዝቅተኛውን መጠን ብቻ ተመላሽ ማድረግ አለብን::

15ለ.6. ስህተቶች

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ኦዲዮመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ አንቀጽ 31 እንደተገለፀው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ የተደረገባቸው ዕቃዎች በቀጣይ የኤክሳይዝ ታክስ ለሚከፈልበት አገልግሎት ጥቅም ላይ ሲውሉ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አለበት::

ስለዚህ ቅጾቹ ከተመላሽ መስፈርቶቹ ጋር የማይጣጣሙ ከሆነ ማስረጃ እስኪቀርብ ድረስ ተመላሽ አናደርግም:: እንዲሁም ተመላሹ ከተደረገ በኋላ የማረጋገጫ ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ ዕቃዎቹ ታክስ ሊከፈልበት በሚገባ አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ካረጋገጥን ተመላሽ የተደረገው የኤክሳይዝ ታክስ ሊገመገም ይችላል::

15ለ.7. ማጠቃለያ

ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራቾች አስቀድመው ማቀድ እና ሥራቸውንም በተደራጀ እና ቁጥጥር በሚደረግበት መንገድ ማስተዳደር መቻል አለባቸው::

የምርት ሥራ የሚካሄድበትን ፋብሪካ ዝርዝር መረጃዎች የሚያካትቱት አዲሶቹ ፈቃዶች ዋነኛው ምክንያት በተፈቀደላቸው አምራቾች እና በታክስ ባለስልጣኑ መካከል ግንኙነት መፍጠር መቻሉ ነው::

ተመላሽ ሊያስደርጉ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን ለታክስ ባለስልጣኑ ማሳወቅ በአምራቹ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው:: የተመላሽ ጥያቄ የሚያቀርቡ አምራቾች ተገቢውን ሂደት መከተል አለባቸው:: በመሆኑም ቅድመ-ማስታወቂያ ካልቀረበ፣ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማረጋገጫ ከሌለ፣ ወይም ተመላሽ ሊደረግበት የሚችል ሥራ በትክክል መከናወኑን የሚያሳይ ማስረጃ ከሌለ ተመላሽ መደረግ የለበትም:: ግዴታቸውን የሚወጡ አምራቾችን ለመጥቀም እና ለተጭበረበሩ የተመላሽ ገጥያቄዎች ክፍያ እንዳይፈፀም ለማድረግ አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ ህግ ተዘጋጅቷል::

አዲሶቹን ሂደቶች እና አሠራሮች ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የተወሰነ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፤ ስለዚህ ሥራ ላይ ከሚውሉበት ጊዜ ጀምሮ የሦስት ወራት የሽሽግር ጊዜ ሊኖር ይገባል:: ይህም አምራቾች ግዴታን ባለመወጣት ቅጣት ሳይከተልባቸው በትክክለኛ ሂደቶች ላይ መማር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቁ.1 መዛግብትና ዶክመንቴሽን ዳ.ተ
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል ዓሥራ ስድስት፡ ለመጠጥ አገልግሎት የማይውል አልኮል

ክፍል 16ሀ፡ የሕግ ትንተና እና የአምራች ግዴታዎች

16ሀ.1. መግቢያ

ኤቲል አልኮል (Ethyl Alcohol) የአልኮል መጠጦችን ለማምረት ጥቅም ላይ ከመዋል በተጨማሪ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት::

አልኮል አሟሚ (solvent) በመሆኑ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት ሊውል እንዲሁም ሽቶዎችን፣ መዋቢያዎችን፣ የስክሪን ማፅጃዎችን፣ የቤት ውስጥ ንፅህና መጠበቂያዎችን እና መድሃኒቶችን ለማምረት ሊያገለግል ይችላል::

አልኮል ለመጠጥ አገልግሎት በማይውልበት ጊዜ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ለሆነ አገልግሎት መዋሉን የሚያሳይ ማረጋገጫ እስከሚቀርብ ድረስ አልኮሉ የኤክሳይዝ ታክስ እንደተጣለበት መቆየት አለበት::

በተጨማሪም አልኮሉ በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል (denatured) መደረግ ያለበት ሲሆን ይህም ማለት አልኮሉ እንዳይጠጣ ለማድረግ ኬሚካሎች መጨመር አለባቸው::

16ሀ.2. አልኮልን በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ የሚችለው ማነው?

16ሀ.2.1. የአልኮል አምራቾች

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉም የአልኮል መጠጥ አምራቾች የንግድ ሥራ ለማከናወን የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል:: የአልኮል መጠጥ አምራቾች ጥሬ ዕቃዎችን ከማፍላት ጀምሮ በፋብሪካው ውስጥ የሚመረቱት የአልኮል መጠጦች ከተመረቱ በኋላ ምርቶቹ ወደ ገበያ ለመቅረብ ፋብሪካውን ለቀው እስኪወጡ ድረስ በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር እንዳሉ ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈል በፋብሪካው ቅጥር ግቢ ውስጥ ሊያቆዩ ይችላሉ::

በእነዚህ ኩባንያዎች የሚመረቱት የአልኮል መጠጦች የኤክሳይዝ ታክሱ ሳይከፈል በመጠጥነት ለሰዎች እንዳይውሉ ሊደረጉ ይችላሉ:: ነገር ግን ይህ ከመፈፀሙ በፊት የሂደቱ ቅድመ-ማስታወቂያ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መቅረብ አለበት:: ስለሆነም አንድ አፈሰር ትክክለኛው ሂደት ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ እና በመጨረሻው የታሸገ ለመጠጥነት የማይውል ምርት ላይ ሊከፈል የሚገባው ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ እንደሌለ ለማረጋገጥ አልኮሉ ለመጠጥነት እንዳይውል በሚደረግበት ሂደት (denaturing process) ላይ መገኘት ይችላል::

16ሀ.2.2. የኤቲል አልኮል አስመጪዎች

የኤቲል አልኮል አስመጪዎች ዕቃዎቹ ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ በጅምላ ላስመጡት ፈሳሽ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለባቸው::

ከኤቲል አልኮሉ የአልኮል መጠጦች በሚዘጋጁበት ጊዜ በመጨረሻዎቹ ምርቶች ላይ ሁለተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መክፈል እንዳለበት ግዴታ ተቀምጧል::

ነገር ግን የኤቲል አልኮሉ ለመጠጥነት ለማይውል አልኮል ከወጡ ደንቦች ጋር በተጣጣመ መልኩ በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል ሊደረግ ከሆነ ይህ ሂደት በተከናወነበት (ዲኔቸር በተደረገው) አልኮል ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ የተመላሽ ሂደትን የተከተለ ጥያቄ እስከቀረበ ድረስ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህንነቱ የተጠበቀ ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

16ሀ.3. መዝገቦች

ለመጠጥነት እንዳይውል በሚደረግበት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካሎችን፣ ጥቅም ላይ የዋለውን የኤቲል አልኮል መጠን፣ በጅምላ አልኮሉ ላይ የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ማረጋገጫን የተመለከቱ መዝገቦች መያዝ አለባቸው፤ እንዲሁም ለመጠጥነት የማይወለው አልኮል የተሸጠላቸውን ደንበኞች የሚያሳዩ ደረሰኞች መያዝ አለባቸው::

16ሀ.4. የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ

በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውል ሁሉም አልኮል ላይ ያለው የኤክሳይዝ ታክስ ለኤክሳይዝ ታክስ ግዴታ እንደተጣለበት ይቆያል፤ እናም አልኮሉ ከታክስ ነፃ ለሆነ ዓላማ ጥቅም ላይ መዋሉን የሚያሳዩ ምንም ዓይነት መዝገቦች መገኘት ካልቻሉ መከፈል አለበት::

ክፍል 16ለ፡ ሂደቱን መቆጣጠር

16ለ.1. መግቢያ

ይህ ለሕግ ጥሰት ክፍተትን የሚፈጥር ሌላ መስክ ነው:: በመሆኑም የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል እንደሌለበት ወይም የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባው ነው በሚል በሚንኛውም አምራች የቀረበውን መረጃ እውነት ነው ብለን ልንቀበለው አንችልም:: የሰነድ ማስረጃውን ማቅረብ የአምራቹ ግዴታ ነው::

16ለ.2. በማረጋገጫው ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች

አልኮል ለመጠጥነት አገልግሎት እንዳይውል የሚደረግበትን ቦታ በሚጎበኙበት ጊዜ የሚከተሉት ጉዳዮች መስተዋላቸውን እና መመርመራቸውን ያረጋግጡ፡-

- የንፁህ አልኮሉ አቅራቢዎች::
- ተይዞ ሊቀመጥ ከሚገባው የጥሬ ዕቃዎች መዝገብ አንፃር የማስረከቢያ ሰነዶችን ያረጋግጡ::
- አልኮሉን ለመጠትነት አገልግሎት እንዳይውል ለማድረግ ትክክለኛዎቹ ኬሚካሎች በትክክለኛው መጠን ጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸውን ያረጋግጡ::
- ለመጠትነት አገልግሎት እንዳይውል የተደረገውን አልኮል በትክክል ለሚጠቀሙ አምራቾች ብቻ እየቀረበ መሆኑን ያረጋግጡ::
- ሁሉም ደንበኞች ላይ የማጣራት ሥራዎችን በማካሄድ ምንም የመጠጥ አምራቾች አለመካተታቸውን ያረጋግጡ::
- የመጠጥ አምራቾች ሆነው ከተገኙ የትኛውም አልኮል መጠጦችን ለማምረት ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ለማረጋገጥ ቦታው ድረስ በመሄድ ይጎብኙዋቸው::
- የተወሰኑ የማስረከቢያ ሰነድ ቁጥሮችን ቅጂ/ማስታወሻ በመውሰድ ምርቶቹ መረከባቸውን እና በተፈቀደ አግባብ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ወደ ደንበኞቹ በመሄድ ጉብኝት ያድርጉ::

የትኛውም አልኮል በትክክል ለመጠትነት አገልግሎት እንዳይውል ካልተደረገ በምርቱ ላይ ሊከፈል የሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ መከፈል አለበት::

16ለ.3. ማጠቃለያ

ማስታወሻ፡ በአሁኑ ጊዜ ያለው የቁጥጥር ሥራ በማንኛውም አልኮል የመጨረሻ አጠቃቀም ላይ ያተኮረ መሆን

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

አለበት፡፡ ለመጠትነት አገልግሎት እንዳይውል የተደረገ አልኮልን የተመለከቱ ደንቦች ከግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ላይ የወጡ ደንቦች ታሳቢ ይደረጋሉ፡፡

ክፍል ዓሥራ ሰባት፡ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች

17.1. መግቢያ

በኢትዮጵያ ውስጥ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ይጣላል፡፡

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እንደ ስልክ እና የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎቶች ያሉ በአገልግሎት አቅራቢው የሚሸጡትን ሁሉንም የቴሌኮሙኒኬሽን ዓይነቶች ያጠቃልላሉ፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የ"አገልግሎቶች" ቁጥጥር እና የኤክሳይዝ ታክስ ግዴታን በተመለከተ ተያያዥ ዝርዝር ነጥቦችን ያካትታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት መመሪያዎች ያልተቀመጡ ቢሆንም የኤክሳይዝ ቀረጥ ክፍያው ጽንሰ-ሐሳብ በዕቃዎች ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

17.2. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ፡ ስለአገልግሎቶች

አንቀጽ	በጽሑፍ የሠፈረው ድንጋጌ
4(2)	የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለበት የአገልግሎት አቅርቦት ተከናወነ የሚባለው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ነው፡- ሀ) አገልግሎቱ በተሰጠበት ቀን፤ ለ) ለአገልግሎቱ የከፍያ መጠየቂያ ኢንቮይስ በተዘጋጀበት ቀን፤ ወይም ሐ) የአገልግሎቱ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል በተከፈለበት ቀን፡፡
5(1)(ሐ)	በተፈቀደለት አገልግሎት ሰጪ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች (የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል)፡፡
7(3)	የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው አገልግሎቶች ላይ የተፈቀደለት ሰው የሚኖርበት የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ አገልግሎቱ በተፈጠበት ጊዜ ይቋቋማል፡፡
8	1/ ረ) ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊና ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች በሚኒስትሩ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች፤ 2/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰጡ ናቸው የሚባለው አገልግሎቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የንግድ ሥራ ቦታ የተሰጡ ሆነው ጥቅም ላይ የሚውሉት ግን ከኢትዮጵያ ውጪ ሲሆኑ ነው፡፡ 3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ተፈፃሚ የሚሆነው የታክሱ ባለስልጣን አገልግሎቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን ሲያምንበት ነው፡፡
9	4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ዋጋ የሚከተለው ይሆናል፡- ሀ) የተመዘገበው ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተደረገ ግብይት ከሆነ ተከፋይ የሆነው የአገልግሎቱ ዋጋ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፤ ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የአገልግሎቱ ትከከለኛ የገበያ ዋጋ፡፡ 5/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ዋጋ በአገልግሎቱ ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አይጨምርም፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

13	የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች የተሰጡት አገልግሎት ሰጪው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የንግድ ሥራ ቦታ ከሆነ አገልግሎቱ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡
15	1/ ማንኛውም ሰው ከታክስ ባለስልጣኑ ፈቃድ ካላገኘ ወይም በታክስ ባለስልጣኑ ዘንድ ካልተመዘገበ በስተቀር በሚከተሉት ሥራዎች ላይ መሠማራት አይችልም፡- ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች ማቅረብ፤ ወይም 2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን በመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎቶችን በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡
18(5)	የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን አገልግሎቶች በማቅረብ ሥራ ላይ ለተሠማራ ሰው የሚሰጠው ፈቃድ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚገልገፅ መሆን አለበት፡፡
19	1/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን የመፈፀም ግዴታ አለበት፡- ሀ) የተሰጠውን ፈቃድ ዋና ቅጂ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ዋና መሥሪያ ቤት በግልፅ በሚታይ ቦታ መለጠፍ፤ ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች በሚመለከት የፈቃዱን የተረጋገጠ ኮፒ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ቦታ ሁሉ የመለጠፍ፡፡
22	2/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች ለማቅረብ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሠረዘ እንደሆነ ባለፈቃዱ፡- ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን አገልግሎት ማቅረቡን ማቆም፤ እና ለ) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ላይ ያልተከፈለውን ታክስ መክፈል፡፡
30	2/ የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክሱን የከፈለ እና ለእነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከገዢው ምንም ዓይነት ክፍያ ያልተቀበለ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ የቻለ እንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግለት ለባለስልጣኑ በጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የታክሱ ባለስልጣንም የተፈቀደለት ሰው በእነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ ምንም ዓይነት ክፍያ ያልተቀበለ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡ 3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በቀደመው ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡- ሀ) ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ከተሸጡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፤ ወይም ለ) ገዢው በሕግ የከሠረ መሆኑ በተረጋገጠበት ጊዜ፡፡ 7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከገዢው ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተቀበለ ከሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ በተቀበለው መጠን ተመላሽ የተደረገለትን የኤክሳይዝ ታክስ ለታክሱ ባለስልጣን መመለስ አለበት፡ ፡
36	በማናቸውም አንድ ወር የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም የተፈቀደለት አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ የእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት በፀደቀው ቅጽ እና በታዘዘው አኳኋን ለታክሱ ባለስልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡
37	2/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የሚያቀርብ ሰው በአንድ ወር ባቀረባቸው አገልግሎቶች ላይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ የሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

17.3. ማጠቃለያ

የአገልግሎቶች የኤክሳይዝ ታክስ ጽንሰ-ሐሳብ ከዕቃዎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም በጥቅሉ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል፡-

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

- ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች አቅራቢዎች ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል፤
- ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ የሚሸጡበትን ዋጋ በመጠቀም የኤክሳይዝ ታክሱን ማስላት አለባቸው፤
- የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያውን በማስታወቂያ ቅጽ ላይ ማስታወቅ አለባቸው፤
- በማስታወቂያው የቀረበው የኤክሳይዝ ታክስ እንዴት እንደተሰላ የሚያሳዩ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው፤
- ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው በተወሰኑ ሁኔታዎች ብቻ ነው፤
- ማናቸውም የነፃ ስጦታዎች (ለምሳሌ"ነፃ" የዓየር ሰዓት) የተመደበላቸው ዋጋ ሊኖር የሚገባ ሲሆን እንደተሸጡ ተቆጥረው የኤክሳይዝ ታክሱ በነፃው የዓየር ሰዓት ላይ መሰላት አለበት::

ክፍል ዓሥራ ስምንት፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልባቸውን ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፡ ምደባ/ዋጋ

18.1. መግቢያ

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ ከሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በተጨማሪ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ላይም ተመሳሳይ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል::

ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ በኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት (ECMS) በቀረበው ትክክለኛ የጉምሩክ መግቢያ ቅጽ መግባት አለባቸው::

የዕቃዎቹ የጉምሩክ ቀረጥ የክሊራንስ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈል ይሆናል:: የኤክሳይዝ ታክሱ የሚሰላውም በንግድ ደረሰኙ የማስመጫ ዋጋ ሲሆን ይህም ጉምሩክን፣ ኢንሹራንስን እና ጭነትን (cif) ማካተት አለበት::

በሀገር ውስጥ አምራቾች ላይ የሚታይ የኤክሳይዝ ታክስን ዝቅ አድርጎ የማሳወቅ ስጋት እንዳለ ሁሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባትም ላይ ተመሳሳይ ስጋት አለ::

ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት እና ወደ ውጭ ሀገር የመላክ ትንተና በኤክሳይዝ ታክስ የኢንስፔክሽን ማኑዋል ውስጥ ይበልጥ በዝርዝር ተካቷል::

18.2. ምደባ

ምድባ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: ሁሉም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች የተለየ የምርት ኮድ የተሰጣቸው ሲሆን ይህም በአነዚህ የምርት ኮዶች ላይ ተፈፃሚ ከሚሆኑ አግባብነት ያላቸው የጉምሩክ ቀረጥ እና የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ጋር የተሳሰረ ነው::

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ሁሉም የምርት ኮዶች ዝርዝር ከዚህ በታች ባለው አባሪ ውስጥ ይገኛል::

ዋነኛ ስጋቶች የሚባሉት አንድ አስመጪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትን ዕቃዎች ዓይነት (በስህተትም ሆነ ሆን ብሎ) ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሲከፋፍል/ሲመድብ ነው::

አንዳንድ የምርት ኮዶች ከውጭ ለሚገቡ ምርቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ ከተገኙ ጥሬ ዕቃዎች የተሠራን ቢራ እና ወይን የሚያጠቃልሉ የምርት ኮዶች ፈፅሞ ወደ ሀገር ውስጥ አይገቡም::

በመሆኑም ከፍተኛው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን ከውጭ በሚገባ ቢራ ላይ ሁልጊዜ መጣል አለበት::

በተመሳሳይ ሁኔታ አንዱ የተለመደው ጉዳይ አልኮል ያለውን ቢራ እንደ አልኮል አልባ ቢራ አድርጎ (በ2203 ፈንታ በ2202) አለአግባብ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ደህመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

መመደብ ነው::

18.3. ለምሳሌ:- ከፍራፍሬ የሚሠሩ መጠጦች እና የፍራፍሬ ጭማቂዎች

በኢትዮጵያ ውስጥ አልኮል አልባ መጠጦች የኤክሳይዝ ታክስ ተጥሎባቸዋል:: በምርት ኮድ 2202 መሠረት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሁሉም ምርቶች የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል:: ይህ ርዕስ:- "የፍራፍሬ ወይም የአትክልት ጭማቂዎችን እና የሰዎችን ጤንነት ለማሻሻል የተዘጋጁ መጠጦችን ሳይጨምር ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ያላቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉ ሁሉንም ዓይነት የማዕድን ውሃዎች እና ጋዝ ያላቸው ውሃዎችን እንዲሁም ሌሎች አልኮል አልባ መጠጦች"ን ያጠቃልላል::

ነገር ግን በኮድ 2009 መሠረት በትክክል ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የፍራፍሬ ጭማቂዎች የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልባቸውም::

ታማኝነት የሌላቸው አስመጪዎች የፍራፍሬ መጠጦችን ከታክስ ነፃ በሆነው በምድብ 2009 ውስጥ ለማካተት ሊሞክሩ ይችላሉ::

ይሁን እንጂ ከ30% በላይ እውነተኛ የፍራፍሬ ጭማቂ ወይም የተጣራ/ድፍድፍ የያዙ ምርቶች ብቻ ከታክስ ነፃ ለመሆን የተፈቀዱ ናቸው::

ከ30% ያነሰ እውነተኛ የፍራፍሬ ጭማቂ/የተጣራ/ድፍድፍ የያዙ ማናቸውም ምርቶች "የፍራፍሬ መጠጦች" እንጂ "የፍራፍሬ ጭማቂዎች" አይደሉም፤ ስለዚህም በአልኮል አልባ መጠጦች ላይ የሚጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸዋል::

የዚህን ልኬት መሟላት ለማረጋገጥ፣ በኮድ 2009 መሠረት የፍራፍሬ ጭማቂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎችን ለማወቅ ከኤሌክትሮኒክ የጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓት (ECMS) ሪፖርት ያጠናቅሩ እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ምርቶች እውነተኛ የፍራፍሬ ጭማቂዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ የፍተሻ መርሃ-ግብር ያዘጋጁ::

18.4. ዋጋ

ሌላው ሊታወቅ የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ዕቃዎች የዋጋ ግምት ነው:: ምንም እንኳን ከሀገር ውስጥ አምራቾች በተቃራኒው አስመጪዎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላበትን ወርሃዊ የዋጋ ዝርዝር ማቅረብ ባያስፈልጋቸውም ዋጋው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል ከሚደረግ የግብይት መርህ ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት:: እንዲሁም ዋጋው የጉምሩክ ቀረጥ በሚሰላበት እና በሚከፈልበት የማስመጫ ዋጋ ላይ ተመስርቶ መሰላት አለበት::

ለምሳሌ ሄኒከን ከውጭ ቢራ የሚያስመጣ ከሆነ ዋጋው "ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ግብይት" ዋጋ መሆኑን እና የቢራው ሽያጭ የሄኒከን በሆኑ ድርጅቶች መካከል በመከናወኑ ምክንያት እንዲቀንስ የተደረገ ዋጋ አለመሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት::

የሀገር ውስጥ አምራቾች ከውጭ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ሲከፍሉ ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባት ሂደትን የማረጋገጥ ሥራ በኢንስፔክሽን ማኑዋሉ ውስጥ ተካቷል::

ይሁን እንጂ የመጨረሻ ምርቶችም ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ተመሳሳይ የማረጋገጥ ሥራዎች መከናወን አለባቸው::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዝገብና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenue
Records & Documentation No.1

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አስመጪዎች ፈቃድ ሲኖራቸው ፈቃዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በነጋዴው መካከል የስምምነት ውል እንዲኖር ስለሚያደርግ ሂደቱን በእጅጉ ያቀለዋል::

እንደ መሠረታዊ የማረጋገጫ ሥራ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው የመጨረሻ ምርቶች ላይ የሚከተሉትን ያከናውኑ:-

- የኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልባቸው ዕቃዎች ጋር የተያያዙ የጉምሩክ መግቢያ ሰነዶችን ናሙና ይውሰዱ::
- አንድ ዓይነት ምርት የሚያስመጡ አስመጪዎችን ወካይ ናሙና በመውሰድ ያረጋግጡ::
- ተመሳሳይ ዓይነት ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥቅም ላይ የሚውለውን ወደ ሀገር ውስጥ የማስገቢያ ዋጋ ይተንትኑ: :
- ጥቅም ላይ በሚውለው ዋጋ ላይ ልዩነት ካለ ያረጋግጡ::
- አስመጪው ከላኪው ጋር ግንኙነት እንዳለው ያረጋግጡ::
- በተጨማሪም የሀገር ውስጥ አምራቾች በተመሳሳይ ዕቃዎች ላይ ያለውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚያሰሉበትን ዋጋ ያረጋግጡ::
- ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ምርቶች የማምረቻ ወጪ፣ እንዲሁም የትራንስፖርት እና የጉምሩክ ቀረጥ ወጪን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሀገር ውስጥ ምርቶች ዋጋ ከውጭ ከሚገቡ ተመሳሳይ ዕቃዎች ያነሰ ሊሆን ይገባል::

ክፍል ዓሥራ ዘጠኝ፡ የኦፊሰሮች ስልጣን እና ማረጋገጫ

19.1. መግቢያ

በማንኛውም የኤክሳይዝ ታክስ ሥርዓት ግብር ከፋዮች በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የወጡትን ሕጎች እና ደንቦች ያከበሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቁጥጥር ሥራዎች ያስፈልጋሉ::

ከማስታወቂያ እና ከክምችት ቅጾች የተገኙ መረጃዎችን መተንተን አዝማሚያዎችን ለመለየት እና በተወሰኑ የአዲት እና የስጋት አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ትኩረት ለማድረግ ሊጠቅም ይችላል::

19.1. የማረጋገጫ ዓላማ

የኤክሳይዝ ታክስን በብቃት ለመቆጣጠር የገቢዎች ሚ/ር የሥራ ኃላፊዎች እያንዳንዱ ግብር ከፋይ የሚጠቀምበትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች አጠቃላይ የአመራረት ሂደት፣ ቁልፍ የመረጃ ነጥቦችን፣ ሊከሰቱ የሚችሉ የስጋት አካባቢዎችን በተመለከተ ጥሩ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል::

በተጨማሪም የሥራ ኃላፊዎች በሥራ ባልደረቦች እና በሌሎች ኤጀንሲዎች እገዛ እያንዳንዱ ግብር ከፋይ የሚሠራበትን የአቅርቦት ሠንሰለት የመቆጣጠር ችሎታ ያስፈልጋቸዋል::

19.2. የማረጋገጫ ሥራ ጥቅሞች

የኤክሳይዝ ታክስ የሥራ ኃላፊዎች በሚያከናውኗቸው ተግባራት እና በአካል በሚደረጉ ፍተሻዎች፣ በማምረቻ ቦታ ውስጥ ቁሳቁስን እና የምርት ሂደቶችን መከታተልን ጨምሮ፣ በቦታው የሚገኙ የማስተላለፊያ መስመሮች ሥራን መከተታተልን የመሳሰሉ ቀላል የሚመስሉ ሂደቶች ላይ ሳይቀር በትጋት መሥራት መቀጠል አለባቸው::

የማጭበርበር ዓላማ ያላቸው ተመዝጋቢዎች መደበኛ ጊዜ በተያዘላቸው ምርመራዎች ወይም በአካል በሚደረጉ

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ፍተሻዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሥራ ኃላፊዎችን መገኘት መጠቀሚያ ስለሚያደርጉት የመደበኛ እና የድንገተኛ ጉብኝት ሂደት ወሳኝ ተግባር ነው::

19.3. የማረጋገጫ አፈሰር ስልጣን እና አሠራሮች ምሳሌ

አዲስ በተሰየሙ የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰሮች የሚካሄደው የመጀመሪያው ተግባር አፈሰሩ የተመደበበትን ተመዝጋቢ በተመለከተ ታሪካዊ የንግድ ግምገማ ማካሄድ ነው:: በዚህም መሠረት አፈሰሩ ሚከተሉትን መገምገም ይፈልጋል

- ጥሬ ዕቃዎቹ ከተወሰነ ጊዜ የምርት ውጤቶች ጋር ሲነፃፀሩ፤
- የተመዘገቡ ኪሳራዎች፤
- ወደ ውጭ ከተላኩ ምርቶች ጋር የተገናኘ መረጃ፤
- የተመዝጋቢው ግዴታን የመወጣት (የታክስ ሕግ ተገዢነት) አጠቃላይ ታሪክ፤
- ማናቸውም የተመዘገቡ ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ የአደጋ ምክንያቶች ወይም በፋይል ላይ ያሉ የተለዩ መገለጫዎች፤
- በምርት እድገት ውስጥ ያሉ አዝማሚያዎች፤
- የዕቃዎች ዋጋ እና የኤክሳይዝ ታክስን ለማስላት ጥቅም ላይ የሚውል ዋጋ፤
- ከቀደሙ የአዲት ሪፖርቶች የሚገኙ ማናቸውም የተመዘገቡ መረጃዎች፤
- በመዝገብ አያያዝ ሥርዓቱ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም መረጃዎች::

በተጨማሪም አምራቹ ወደ ሀገር ውስጥ ውስጥ የሚያስገባቸውን ምርቶች በተመለከተ ከጉምሩክ አስተዳደር ሥርዓቱ ለመረዳት ማንኛውንም የኩባንያውን የማስመጣት መረጃ መተንተን እና ዕቃዎቹን እና ጥሬ ዕቃዎቹን መቀበሉን በማጣራት የመዝገብ አያያዙን ማረጋገጥ ይችላሉ::

19.4. ስህተቶች

ስህተቶች ሲገኙ የኤክሳይዝ ታክስ አፈሰሩ ሪፖርት ማድረግ እና የገንዘብ ቅጣት የሚያስከትል የሕግ ስህተት መሆን አለመሆኑን (ለምሳሌ የኤክሳይዝ ታክሱ ተከፍሎ ነገር ግን መዝገቦቹ አጥጋቢ አልነበሩም)፤ ወይም ስህተቱ የኤክሳይዝ ታክሱ እንዳይከፈል ምክንያት መሆን አለመሆኑን (ለምሳሌ ዕቃዎቹ ወደ ውጭ ተልከዋል ነገር ግን ወደ ውጭ የተላኩበት ወይም የክምችቱ መጥፋት/ከአገልግሎት ውጪ መሆን ማስረጃ የለም) መወሰን አለበት: :

ከዚህ ጋር ተያይዞ ከኤክሳይዝ ታክስ ግምገማው በተጨማሪ ሊጣሉ የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት ቅጣቶች ይኖራሉ: :

19.5. ማጠቃለያ

ለአዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ የቁጥጥር ሥርዓት ጤናማ እና ቀልጣፋ ቁጥጥር እንዲኖር ግንኙነት ዋነኛው ቁልፍ ጉዳይ ነው::

የአሠራር ሂደቶችን ተከትሎ በአምራቾች የቀረቡ መረጃዎችን መተንተን እና አምራቾች በሕግ የተቀመጡ ግዴታዎቻቸውን መወጣታቸውን ማረጋገጥ በአምራቹ እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ መካከል የግንዛቤ ሁኔታን ይፈጥራል:: ይህም ግዴታቸውን የሚወጡ አምራቾችን የሚጠቁም ሲሆን በሌላ በኩል ግዴታቸውን የማይጡትን ለመለየት ያስችላል::

በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት በተፈቀደለት አምራች ያልተመረቱ በገበያ ላይ ያሉ የምርት ዓይነቶችን/ብራንዶችን እና ምርቶችን ለመለየት ያስችለዋል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ያሕመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ክፍል ሃያ፡ የወንጀል ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

20.1. መግቢያ

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ የተጣሉበትን ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም ሰው የሚከተሉት ቅጣቶች ይከተሉበታል፡-

- የእስር ጊዜ፤
- ቋሚ የገንዘብ ቅጣት፤ ወይም
- ከተሰወረው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር የተያያዘ የገንዘብ ቅጣት::

20.2. ቅጣቶች

የሚጣሉት ቅጣቶች ከቅጣቱ ጋር ተያያዥ በሆነው ከላይ ባለው ክፍል ውስጥ ተጠቅሰዋል:: ይሁን እንጂ ይህ ክፍል አንቀጽ 38 እና 39ን በኤክሳይዝ ታክስ አዋጁ ላይ በተቀመጡበት አግባብ ይዘረዝራል፡-

አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ (1)፡ ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ሰው የሚከተለውን ቅጣት ይቀጣል፡- ሀ) የአዋጁ አንቀጽ 15 (1) (ሀ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሰው በሚመለከት ፈቃድ ቢሰጠው ኖሮ ሊከፍል ይገባ የነበረውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ፤ ወይም ለ) የአዋጁ አንቀጽ 15 (1) (ለ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሰው በሚመለከት የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው በሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ በትጣለባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ::

አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ (2)፡ በበፈቃዱ ላይ ከተመለከተው ቦታ ውጪ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ የተሠማራ የተፈቀደለት አምራች በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል::

አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ (3)፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 (1) የተደነገገው ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ከፋብሪካ ወጪ እንዳደረገ የሚቆጠር የተፈቀደለት አምራች በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል::

አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ (4)፡ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጣሉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለኤክሳይዝ ታክስም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (1)፡ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 15(3)፣ 18(4)፣ 26(1)፣ 27(1)፣ 30(7)፣ 31(2) እና 32 ድንጋጌዎችን ተላልፎ መገኘቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ 100,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::

አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (2)፡ የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ከተመለከተው ሥፍራ ውጭ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ መሠማራቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ5 እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::

አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (3)፡ የተፈቀደለት አምራች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 (1) ወይም 19 (2) የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ1 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 ባልበለጠ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::

አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (4)፡ ማንኛውም ሰው፡- ሀ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ 25 (3) (ለ) በመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ከማምረቻ ፋብሪካው ወጪ ያደረገ እንደሆነ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቤተ መዛግብትና ያልተማከለ ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ለ) ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች ተከማችተው በሚገኙበት ቦታ የገባ እንደሆነ፤ ወይም ሐ) የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ባልተፈቀደ መንገድ ከተከማቹበት ቦታ ወጪ በማድረግ፣ ባህሪያቸውን በመለወጥ ወይም የቁጥጥሩን ሥራ በማወክ ረገድ የተባበረ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ5 እስከ 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::

አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (5)፡ በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከተመረቱበት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን የገዛ ወይም ሳይፈቀድለት እነዚህን ዕቃዎች የተቀበለ ወይም በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ለሽያጭ በማዋል ተግባር የተሠማራ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::

አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ (6)፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ስለኤክሳይዝ ቴምብር የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ 100,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::

20.3. አጠቃላይ ቅጣት

አብዛኞቹ ቅጣቶች በሕግ የተቀመጡ ግዴታዎቻቸውን የማይወጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ የተሠማሩ የተፈቀደላቸው አምራቾች ላይ ብቻ ያነጣጠሩ ናቸው::

ይሁን እንጂ በማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አጠቃላይ የቅጣት ግዴታም አለ:- "በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከተመረቱበት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን የገዛ ወይም ሳይፈቀድለት እነዚህን ዕቃዎች የተቀበለ ወይም በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ለሽያጭ በማዋል ተግባር የተሠማራ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ3 እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 100,000 እስከ 200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል::"

ይህም ሁሉንም በቸርቻሮ ንግድ ላይ የተሠማሩ ሰዎችን እና የጅምላ አከፋፋዮችን እንዲሁም ማናቸውንም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች በይዞታቸው ሥር ያደረጉ ግለሰቦችን ያጠቃልላል::

20.4. ማጠቃለያ

ፈቃድ በተሰጣቸው እና ፈቃድ ባልተሰጣቸው አምራቾች ላይ ሊጣሉ የሚችሉ የተለያዩ ዓይነት ቅጣቶች አሉ:: እነዚህም በወንጀል ጥፋቱ ልክ ተፈፃሚ መደረግ ያለባቸው ሲሆን መታየታቸውን ለቀጠሉ ስህተቶች ወይም በተወሰኑ ጊዜያት ምንም ዓይነት ግዴታን የመወጣት ሁኔታ በማይታይበት ጊዜ መጨመር አለባቸው::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሀገር መዛግብትና ሶስመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

አባሪ አንድ፡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ትርጓሜ

ሀ1. መግቢያ

ለሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ ለአምራቾቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን የተወሰኑ ዕቃዎች ዓይነት እና ምድብ መረዳት አስፈላጊ ነው::

አንዳንድ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠሪያዎች/ስያሜዎች አሻሚ ናቸው::

የሚከተለው ሰነድ በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ስያሜ ያቀርባል::

የዕቃውን ምንነት ለመወሰን የጉምሩክ የሸቀጦች ኮድ ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ አጠራጣሪ ነገሮች ካሉ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ እንደገቡ አድርጎ (በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ቢሆንም) ለመወሰን እና ለማስተናገድ የጉምሩክ ታሪፍ የተዋሃደ ሥርዓት ማብራሪያ ማስታወሻዎችን ይመልከቱ:: ምደባው ከማናቸውም ከውጭ ከሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶች ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት:: በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች የተመረተ ቢራ ወይም ወይን ብቻ (እነዚህ ምርቶች የሚመረቱት በኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነ) አይካተትም::

---

1. የስብ እና ዘይት የሸቀጦች ምድብ፡

ከ15.01 እስከ 15.15: ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከተለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የማይቻል የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብ እና ዘይት፤ እና የእነዚህ ተዋጽኦ ውጤቶች::

የዕቃው ዓይነት፡ ከ100 ግራም ምርት ውስጥ 40 ግራም ሳቹሬትድ የስብ መጠን ያላቸው ለማብሰያነት የሚያገለግሉ የአሳማ ስብን ጨምሮ ሁሉም የአትክልት ወይም የእንስሳት ስብ እና ዘይቶች:: ይህ መጠን በመለያው/ሌብሉ ላይ መገለፅ አለበት:: መለያው ይህንን የማያሳይ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ መከፈል አለበት::

የስብ ይዘቱን ለመለካት የፍተሻ ሥራዎች መከናወን አለባቸው:: ከ100 ግራም ምርት ውስጥ ከ40 ግራም በታች ሳቹሬትድ የስብ መጠን ያላቸው ማናቸውም ምርቶች የኤክሳይዝ ታክስ አይጣልባቸውም::

15.16: ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም 0.5 ግራም ወይም የበለጠ ኒሔና ጎጂ የሆነ ቅባት የያዘ፤ ወይም የሳቹሬትድ ቅባት መጠኑን ከተለጠፈበት መግለጫ ላይ ለማወቅ የማይቻል በከፊል ወይም በሙሉ ሀይድሮጂን የተጨመረበት የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብ እና ዘይት::

የዕቃው ዓይነት፡ እነዚህ ለ"ቀጥታ ፍጆታ" የሚውሉ የማብሰያ እና የአትክልት ዘይቶች ናቸው:: በሸቀጦች ምድብ ውስጥ ከ15.01 እስከ 15.15 ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፤ ነገር ግን እንደ ሰላጣ ዘይት/ድሬሲንግ የመሳሰሉትን ምርቶች ይጨምራሉ::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቁጥር 1 መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

15.17: ለምግብነት የተዘጋጀ ከ100 ግራም ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ወይም 0.5 ግራም ወይም የበለጠ ለጤና ጎጂ የሆነ ቅባት የያዘ ማርጋሪን::

የዕቃው ዓይነት: ከ100 ግራም ምርት ውስጥ 40 ግራም ወይም የበለጠ ሳቹሬትድ ስብ የያዘ ማርጋሪን የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልበታል:: በምዕራፍ 4 ስር የተመደበው ቅቤ የኤክሳይዝ ታክስ አይጣልበትም:: ስለሆነም ምርቱ ማርጋሪን በሚሆን ጊዜ የተለጠፈው መለያ ትክክል መሆኑን እና ከኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ለማምለጥም ቅቤ እንደሆነ ተደርጎ መለያው አለመለጠፉን አልፎ አልፎ ያረጋግጡ::

---

2. ስኳር እና ከስኳር የተገኙ ጣፋጭ ምግቦች

1701.1200 1701.1400 1701.9100 1701.9900 1702.2000	ማንኛውም ዓይነት ስኳር (በአንኳርም ሆነ በፈሳሽ መልክ የተዘጋጀ) ሞላሰስን፣ ማፕል ስኳርን እና ማፕል ወለላን ሳይጨምር

የዕቃው ዓይነት: በማንኛውም ዓይነት የዕቃ መያዣ መጠን ውስጥ ያለ ማንኛውም ዓይነት ስኳር ወይም ወለላ:: ይህ ሰፋ ያለ ፍቺ በመሆኑ እነዚህን ዓይነት በመሰሉ ዕቃዎች ላይ ያለ ማንኛውም ማሸጊያ መለያው ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ መፈተሽ ይኖርበታል::

1704.1000 ማስቲካ፣ ስኳር ቢቀባም ባይቀባም
1704.9000 ከስኳር የተገኙ ጣፋጭ ምግቦች ነጭ ቸኮሌትን ጨምሮ፤ ካካዎ የሌለባቸው

የዕቃው ዓይነት: ማናቸውም ጣፋጮች ወይም ከስኳር የተገኙ ጣፋጭ ምግቦች - ቸኮሌት ባር/ማስቲካ (ከስኳር ነፃ የሆነ ማስቲካ ቢሆንም)::

---

3. ቸኮሌት እና ካካዎ ያለባቸው የምግብ ዝግጅቶች

1806.1000, 1806.2000, 1806.3100, 1806.3200,. 1806.9090	ቸኮሌት እና ካካዎ ያለባቸው የምግብ ዝግጅቶች፤ የህፃናት እና የህመ·ማን ምግቦችን ሳይጨምር

የዕቃው ዓይነት: በተለይ ለህፃናት እና ህመ·ማን/አካል ጉዳተኞች ከተዘጋጁ ምግቦች በስተቀር ማናቸውም ካካዎ/ቸኮሌት ያለባቸው የምግብ ዝግጅቶች::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዕቃ መላኪያትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation

4. ዱቄት ለስላሳ መጠጦች

2106.9040 ዱቄት ለስላሳ መጠጦች

የዕቃው ዓይነት፡ ይህ በ2106.9040 ስር በዱቄት ለስላሳ መጠጦች ላይ ተመሠረተ የተወሰነ የኤክሳይዝ ታክስ ነው፡፡ የዱቄት ለስላሳ መጠጦችን ብቻ ማለትም ጣዕም ያለው ለስላሳ መጠጥ ለማዘጋጀት ፈሳሽ የሚጨመርበትን ዱቄት የሚመለከት ነው፡፡

---

4. መጠጦች

2201.1000
2201.9000

ውሃዎች፣ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ የማዕድን ውሃዎች እና ጋዝ ያላቸው ውሃዎች፣ ስኳር ወይም ማጣፈጫ ያልተጨመረባቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው ያልተደረጉ በፋብሪካ የታሸጉ፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ ሁሉም ጣዕም እንዲኖረው ያልተደረገ የማዕድን ውሃ - ጋዝ ያለውም ሆነ የሌለው፣ የሶዳ ውሃን ጨምሮ ::

2202.1000
2202.9990
2202.9100

ስኳር ወይም ሌላ ማጣፈጫ ያላቸው ወይም ጣዕም እንዲኖራቸው የተደረጉ የማዕድን ውሃዎች እና ጋዝ ያላቸው፣ እና ማናቸውም አልኮል አልባ መጠጦች፤ ከአትክልት እና ከፍራፍሬ ጭማቂ እንዲሁም የሰዎችን ጤንነት ለማሻሻል ከተዘጋጁ መጠጦች ውጪ፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ ይህ ካርቦኔትድ ለስላሳ መጠጦችን (ለምሳሌ፡ ፔፕሲ/ኮካ ኮላ ወዘተ.) ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም ይህ ምድብ ከንፁህ ውሃ የተለየ ጣዕም እንዲኖራቸው የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ ጣዕም የተጨመረባቸውን የማዕድን ውሃዎችን ያካትታል፡፡ ቶኒክ ውሃ እና መደባለቂያዎች በዚህ ምድብ ውስጥ ናቸው፡፡

በተጨማሪም አልኮልን ከቢራ ውስጥ በማስወገድ የተመረተን አልኮል አልባ ቢራ ያካትታል፡፡ አልኮል አልባ ቢራ ከ0.5% ያነሰ የአልኮል ይዘት መጠን ያለው ቢራ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
የመዛግብትና ሰነድ አስተዳደር ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ቢራ

2203.0000: ከብቅል የተሠራ ሁሉም ዓይነት ቢራ

የዕቃው ዓይነት፡ ከብቅል የተሠራ ቢራ - በአብዛኛው ከውጪ ከሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች፡፡

ከመታሸጉ በፊት በማንኛውም መጠን የአልኮል መጠጦችን መጨመር ይህንን ምርት የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልበት የአልኮል መጠጥ ያደርገዋል፡፡

2203.000	- ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ በበቀለ ገብስ የተመረተ ቢራ፡፡ - ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ (ግብዓት) የተመረተ ቢራ፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ በሀገር ውስጥ በተመረተ ጥሬ ዕቃ (ለማንኛውም የአልኮል ጥንካሬ) የተመረተ ቢራ ብቻ በዚህ ምድብ ውስጥ ሊወድቅ ይችላል፡፡ ጥቅም ላይ የዋለውን የገብስ ብቅል የሰሪት ሀገር ለማረጋገጥ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

ከመታሸጉ በፊት በማንኛውም መጠን የአልኮል መጠጦችን መጨመር ይህንን ምርት የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣልበት የአልኮል መጠጥ ያደርገዋል፡፡

ከወይን እሸት የተዘጋጀ ወይን፡

2204.1000 2204.2100 2204.2200 2204.3000	ማናቸውም ከወይን እሸት የተዘጋጀ ወይን፣ ጠንካራ ወይን፣ የወይን ጠጅ ድፍድፍ፣ የሚፈላ የወይን ጠጅ እና ፍራፍሬዎችን በማፍላት የሚገኙ ሌሎች የአልኮል መጠጦችን ጨምሮ፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ ይህ ምድብ ከድፍድፍ/ከሚፈላ የወይን እሸት የተዘጋጀን ሁሉንም ወይን ያጠቃልላል፡፡ እንዲሁም ጠንካራ ወይንን (ማለትም የአልኮል ጥንካሬውን ከፍ ለማድረግ የአልኮል መጠጦች ተጨምረውበት የተመረተን ወይን) ያካትታል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ★ Ethiopian Ministry of Revenues ★ Records & Documentation No.1

በሀገር ውስጥ ከተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች የተዘጋጀ ወይን

2205.1000 2205.9000	ውሃን ሳይጨምር ቢያንስ ከክብደቱ 75% የሚያህለው በሀገር ውስጥ ግብዓት የተመረተ የወይን ጠጅ፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ ለኤክሳይዝ ታክስ ዓላማዎች ሲባል ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተመረተ የወይን እሸት እና ፍራፍሬ ለሚመረት የሚፈላ ወይን እንዲቀንስ የተደረገ መጣኔ ነው፡፡ የወይን እሸቱን የፍራፍሬውን የስሪት ሀገር ለማረጋገጥ በአምራቹ ማስረጃዎች መቅረብ አለባቸው፡፡

ማስታወሻ፡ በጉምሩክ ታሪፍ ኮድ 2205 ሼርሙጥን ያጠቃልላል (እነዚህ እንደ ሲንዛኖ፣ ማርቲኒ ወዘተ ያሉ ምርቶች ናቸው፤ ስለዚህ በእነዚህ ምርቶች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ ከ2204 ምርቶች መጣኔ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን፤ ምክንያቱም እነዚህ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎችን መመዘኛ አያሟሉም)፡፡

በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ያልተገለፁ ወይም ያልተመለከቱ የሚፈሉ መጠጦች

2206.0000 2208.90.10	ሌሎች የሚፈሉ መጠጦች (ለምሳሌ ሲዳር፣ ፔሪ፣ ሜድ፣ ኦፔክ ቢራ)፤ የሚፈሉ መጠጦች እና አልኮል አልባ መጠጦች እና የአልኮል መጠጦች ድብልቅ፣ ስታውት፣ ሌሎች ከቢራ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ መጠጦች፣ ዱቄት ቢራ፡፡ የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ ለመጠጣት ዝግጁ የሆኑ ድብልቅ መጠጦች

የዕቃው ዓይነት፡ ይህ ከቢራ በስተቀር ሁሉንም የሚፈሉ መጠጦች ይመለከታል፡፡ የአልኮል መጠጦች የሚፈሉ መጠጦች ላይ ሊጨመሩ ይችላሉ ነገር ግን የሚፈላው መጠጥ ዋነኛ ባህርያት እስኪልተቀየሩ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ትንሽ መጠን ያለው የሚፈላ መጠጥ ላይ የበዛ የአልኮል መጠጥ ሊጨመርበት አይችልም፡፡

እንዲሁም የአልኮል ይዘታቸው ከ7% ያልበለጠ ድብልቅ አልኮል እና ጣዕም ያላቸውን የአልኮል መጠጦች ያጠቃልላል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብት አስተዳደር ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

ባህሪው ያልተለወጠ ኤቲል አልኮል

2207.2000: ማናቸውም ዓይነት ንፁህ አልኮል

የዕቃው ዓይነት፡ በጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር 2207.2000 በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት የማይውል አልኮልን የሚመለከት በመሆኑ ማናቸውም ባህሪው ያልተለወጠ ኤቲል አልኮል 10% የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት መሆኑን ግልፅ ማድረግ አለብን፡፡

የአልኮል መጠጦች

2208.3000
2208.2000
2208.4000
2208.5000
2208.6000
2208.7000
2208.9090

ማንኛውም የአልኮል ጥንካሬ ያለው ዊስኪ፣ ጂን፣ ጂኔቫ፣ ቮድካ፣ ሩም እና ከተጠቀሱት የሸንኮራ አገዳ ውጤት በማጣራት የሚገኙ ሌሎች መጠጦች እንዲሁም ሊከርስና ኮርዲያልስ መጠጦች፡፡

---

5. ትምባሆ እና የትምባሆ ምርቶች

2401.1000
2401.2000
2401.3000

የትምባሆ ቅጠል

የዕቃው ዓይነት፡ በጥሬ ዕቃ መልክ ያለ የትምባሆ ቅጠል - የተፈበረከ ወይም ያልተፈበረከ - ወደ ሀገር ውስጥ እንደገባ የትምባሆ ውጤቶችን ለማምረት ጥቅም ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልበታል፡፡

ሲጋራ

2402.2000 ሲጋራ

የዕቃው ዓይነት፡ በማናቸውም ርዝመት/ምጠና ትምባሆ የያዙ ሲጋራዎች፣ ማጣሪያ ያላቸውም ሆነ ማጣሪያ የሌላቸው፡
፡

ይህ በትምባሆ የተሠሩ ሲጋራዎችን ብቻ የሚያጠቃልል በመሆኑ ከተፈጥሮ ዕጽዋት የተዘጋጁ ሲጋራዎችን ወይም የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎችን ያካተተ አይደለም፡፡ በመሆኑም እነዚህን በኤክሳይዝ ታክስ መረብ ውስጥ ለማስገባት አዲስ ምድብ ወደ ሥራ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ፅ/ት መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

ሲጋሮች፡

2402.1000 2402.9000 2403.1900 2403.9100 2403.9900	ሲጋር፣ ሲጋሪሎስ፣ በቱቦ የሚጨስ ትምባሆ፣ ሱረት እና ሌሎች ማናቸውም የትምባሆ ውጤቶች

የዕቃው ዓይነት፡ ይህ ምድብ ሲጋር፣ ቼሩትስ፣ በቱቦ የሚጨስ ትምባሆ፣ ሱረት እና ትምባሆን "ከሚተኩ" ምርቶች የሚሠሩ ሲጋራዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን ይህም ሺሻ እና ሌሎች ከተፈጥሮ ዕጽዋት የሚዘጋጁ የትምባሆ ምርቶችን ያካትታል::

እዚህ ላይም ከ"ትምባሆ" ጋር የተገናኘ እንደመሆኑ - የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎች አልተካተቱም፤ በዚህም ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ አልተጣለባቸውም:: እነዚህ ወደ ኤክሳይዝ ታክሱ እንዲገቡ በመመሪያ ሊገለፁ እና በወደፊት መርሃ ግብር ሊካተቱ ይችላሉ:: ሊመደቡባቸው የሚችሉ የተወሰኑ የሽቀጦች ምድቦችም ይኖራሉ::

---

6. ጨው

2501.0010 2501.0090	ጨው

የዕቃው ዓይነት፡ ማንኛውም ዓይነት ጨው፣ የገበታ ጨው፣ የባህር ውሃ፣ ጠጣር/አንኳር ጨውን ጨምሮ::

---

7. የማዕድን ነዳጅ፣ የማዕድን ዘይት እና የማዕድን ውጤቶች

2710.1200 2710.1910 2710.1920 2710.1950 2710.2010 2710.2020 2710.2050	ቢንዚን ተራ ወይም ሱፐር፣ ፔትሮል ተራ ወይም ሱፐር፣ ጋዞሊን እና ሌሎች የሞተር ስፒሪቶች፣ የአውሮፕላን ነዳጅ

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም ዓይነት የማዕድን ዘይት/ነዳጅ ሲሆን ይህም እንደ መንገድ ነዳጅ የሚያገለግል እና ማናቸውም ስያሜ ያላቸውን ሞተሮች የሚያንቀሳቅስ ነው:: ፔትሮል፣ ታፍጣ፣ ኬሮሲን፣ ፈሳሽ ፓራፊን፣ የአውሮፕላን ነዳጅ የኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ ውስጥ ይጠቃለላሉ:: ይሁን እንጂ የአውሮፕላን ነዳጅ ለዓለም አቀፍ ጉዞዎች ጥቅም ላይ ሲውል ነፃ ይሆናል::

ማለስለሻ ዘይቶች የኤክሳይዝ ታክስ አይጣልባቸውም - ለሞተር ወይም ማሞቂያ ነዳጅነት የሚያገለግሉ ዘይቶች ብቻ የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸዋል::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ዋና መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

8. ሽቶዎች፣ ቶይሌት ዋተርስ፣ የመዋቢያ (የቁንጅና እና መኳኳያ) ምርቶች፣

3303.0000
3304.1000,
3304.2000,
3304.3000,
3304.9100,
3304.9900,
3305.2000,
3305.3000,
3305.9000

ሽቶዎች እና ቶይሌት ዋተርስ

ሰን ስክሪን እና ሻምፖዎችን ሳይጨምር የውበት መጠበቂያ (የቁንጅና እና መኳኳያ) ምርቶች

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም አስፈላጊ ዘይቶች፣ ሽቶዎች እና አፍተርሼቮች:: እንደ የከንፈር ቀለም፣ የፊት ቀለም፣ የዓይን መኳኳያ፣ የጥፍር ቀለም እና የእጅ ወይም የእግር ማሳመሪያዎችን የመሳሰሉ ማናቸውም የመዋቢያ ምርቶች:: ሻምፖዎች የኤክሳይዝ ታክስ አይጣልባቸውም፤ ነገር ግን የፀጉር ቀለም፣ የፀጉር ስፕሬይ እና ዝግጅቶች፣ ፀጉር ማለስለሻ ወይም ማከርደጃ ዝግጅቶች የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸዋል::

9. ርችቶች

3604.1000: ርችቶች

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም "ርችት" የሚል ትርጉም የተሰጣቸው ምርቶች፤ የፓይሮቴክኒክ ምልክት መስጫ ሆነው እንዲያገለግሉ የተመረቱ:: ለህዝብ እይታም ሆነ ለግል አገልግሎት የሚገዙ ርችቶች የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸዋል::

10. የፕላስቲክ ከረጢቶች (ፌስታል)

3923.2110,
3923.2910,
3923.2910,
3923.2920

የፕላስቲክ ከረጢት (ፌስታል)

የዕቃው ዓይነት፡ ከፕላስቲክ የተሠሩ ማንኛውም የውፍረት መጠን ያላቸው የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ የኢትሊን ፖሊመሮችን ጨምሮ::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ቁ.1 መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.1

11. ጎማዎች

4011.1000 እስከ 4013.9090	ከላስቲክ የተሠሩ የተሸከርካሪ ጎማዎች

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም ከላስቲክ የተሠሩ የተሸከርካሪ ጎማዎች፤ ለአውቶሞቢሎች፣ ለአውቶብሶች፣ ለጭነት መኪናዎች፣ ለሞተር ሳይክሎች፣ ለብስክሌቶች፣ ለአውሮፕላኖች፣ ለትራክተሮች ወዘተ. የሚያገለግሉ አዲስ እና ያገለገሉ በጎፋስ የሚሞሉ ጎማዎች የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸዋል::

---

12. በፋብሪካ የተፈበረኩ ጨርቃ ጨርቅ እና የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች

5007.1010 5007.1090 5007.2010 5007.9010 5007.9090 5111.1110 እስከ 5113.0090 5208.1100 እስከ 5212.2500 5309.1190 እስከ 5311.0090 5407.1010 እስከ 5408.3400 5512.1110 እስከ 5516.9400 5801.1000 እስከ 5811.0000 (Except 5802.1100, 5804.1010) 5901.1000 እስከ 5911.9000 (ከ 5902.1000, 5902.2000, 5902.9000 በስተቀር)	ሽምን ጨርቆች፣ የተሸመነ የተፈጥሮ ሐር፣ ሐር የመሰለ ጨርቅ፣ ናይሎን፣ ሐር፣ እንዲነጣ የተደረገ፣ በግራጫ ወይም በነጭ በከፊል ወይም በሙሉ ከጥጥ የተሠራ ጨርቅ፣ ቀለም የተነከረ ወይም የታተመበት ጨርቅ፣ በማንኛውም ቁመት እና አርብ ሽፋት የተቆረጠ (ከአጎበር እና አቡጀዲ ውጪ) ብርድልብስ፣ አንሶላ፣ አልጋልብስ፣ ፎጣ፣ የጠረጴዛ ልብስ እና ሌሎች በፋብሪካ የተፈበረኩ ተመሳሳይ ጨርቆችን ጨምሮ::

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም ከጨርቅ የተሠሩ ጨርቃ ጨርቅ እና ዕቃዎች ፎጣዎችን፣ ብርድልብሶችን፣ አንሶላዎችን ወዘተ ጨምሮ::

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

የሚከተሉት ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ናቸው፡ ቴሪ ፎጣ፣ (ናፒዎችን ለመሥራት የሚያገለግል)፤ አጎበር፤ ከፍተኛ ጥንካሬ ካለው ከናይለን ወይም ከሌሎች ፖሊፕሮፒይድ፣ ፖሊስተር ወይም ከቪስኮስ ሩዮን ድርና ማግ የተሠሩ ለጎማ ሥራ የሚያገለግሉ የኢንዱስትሪ ጨርቆች፡፡

---

13. **ምንጣፎች**

5701.1000 እስከ 5705.0000	ምንጣፎች

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም ምንጣፎች እና ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ የወለል መሸፈኛዎች፤ ከሱፍ ወይም ከለስላሳ የእንስሳት ፀጉር የተሠሩ፡፡

ምንጣፎች እና ሌሎች ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ የወለል መሸፈኛዎች፣ የተሸመነ፣ መደላድልነት የሌላቸው፣ የተዘጋጁ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ "ከለም"፣ "ሹማክስ"፣ "ካራሚነ" እና ተመሳሳይ በእጅ የተሸመኑ አነስተኛ ምንጣፎች ጭምር (ከሰው ሠራሽ ግብዓት ወይም ከእንስሳት ፀጉር የተሠሩ)፡፡

ምንጣፎች እና ሌሎች ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ የወለል መሸፈኛዎች፣ ፀጉራቸው የተበተነ፣ ከሰው ሠራሽ ግብዓት ወይም ከእንስሳት ፀጉር የተሠሩ፡፡
ምንጣፎች እና ሌሎች ከጨርቃ ጨርቅ የተሠሩ የወለል መሸፈኛዎች፣ ከፊልት የተሠሩ (ታይልስን ጨምሮ)፡፡

---

14. የተሰፉ ልብሶች

6001.1000 እስከ 6006.9000 6201.1100 እስከ 6217.9000 6301.1000 እስከ 6304.9990	የተሰፉ ልብሶች

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም የተሰፉ ልብሶች፤ የውስጥ ልብሶችን፣ ጃኬቶችን፣ ቲሸርቶችን፣ ሱሪዎችን፣ ሙሉ ቀሚሶችን፣ ጉርድ ቀሚሶችን ጨምሮ፤ ከጫማ ውጪ፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሬኮ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1

10. አርቴፊሻል አበባዎች፣ ከቅጠሎች እና ከፍሬዎች የተሠሩ ዕቃዎች

6702.1000, 6702.9010, 6702.9090	አርቴፊሻል አበባዎች፣ ቅጠሎች እና ፍሬዎች እና የእነዚህ ክፍሎች፣ ከአርቴፊሻል አበባዎች፣ ከቅጠሎች ወይም ከፍሬዎች የተሠሩ ዕቃዎች፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ በእጅ የተሠሩም ይሁን በፋብሪካ የተመረቱ አርቴፊሻል አበባዎች፣ ከፕላስቲክ ወይም ሌሎች ማናቸውም ማቴሪያሎች የተሠሩ፡፡

---

15. የሰው ፀጉር እና ዊጎች

6703.0000 6704.1100, 6704.1900, 6704.2000, 6704.9000	የሰው ፀጉር፣ የሰው ፀጉር ውዳቂ፣ ዊግ፣ የውሸት ሂም፣ የውሸት ቅንድብ፣ የውሸት ሽፋሎች፣ የእንስሳት ፀጉር፣ ከሴንቴቲክ ጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያሎች የተሠሩ ፀጉሮች፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ ከሰው ፀጉር ወይም ሌሎች ማቴሪያሎች የተሠሩ ማናቸውም ዊጎች፡፡

የውሸት ፀጉር፣ የውሸት ጢሞች፣ የውሸት ቅንድቦች እና ሽፋሎች፣ ተቀጣይ ፀጉሮች፣ መቀየሪያዎች እና የመሳሰሉ፣ ከሰው ወይም ከእንስሳት ፀጉር ወይም ከጨርቃ ጨርቅ ማቴሪያል የተሠሩ፤ በሌላ ስፍራ ያልተገለፁ ከሰው ፀጉር፣ ከሰው ፀጉር ውዳቂ ወይም ከሴንቴቲክ ማቴሪያል የተሠሩ ዕቃዎች፡፡

---

16. **አስቤስቶስ እና የአስቤስቶስ ውጤቶች**

6811.4000, 6812.9100, 6812.9200, 6812.9300 6812.8000, 6812.9900, 6813.2000	ከአስቤስቶስ ሲሚንቶ፣ ከሴሉሎስ ፋይበር ሲሚንቶ ወይም እነዚህን ከመሳሰሉ የተሠሩ ዕቃዎች፣ በፋብሪካ የተሠሩ የአስቤቶስ ፋይበሮች፣ መደባቸው አስቤስቶስ ወይም ማግኒዢየም ካርቦኔት የሆኑ ድብልቆች፣ ከእነዚህ ድብልቆች ወይም አስቤስቶስ የተሠሩ ዕቃዎች (ለምሳሌ ክሮች፣ ሽምን ጨርቆች፣ ልብሶች፣ በራስ የሚጠለቁ፣ ጫማዎች፣ ጋስኬቶች)፣ የተጠናከሩ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ አስቤስቶስ ያላቸው የፍትጊያ መሣሪያዎች፡፡

የዕቃው ዓይነት፡ አስቤስቶስ ያለው የአስቤስቶስ ሲሚንቶ፤ በፋብሪካ የተሠሩ የአስቤቶስ ፋይበሮች፣ መደባቸው አስቤስቶስ ወይም አስቤስቶስ እና ማግኒዢየም ካርቦኔት የሆኑ ድብልቆች፣ ሌሎች መሰል ከአስቤስቶስ ቅይጦች (ለምሳሌ ክሮች፣ ሽምን ጨርቆች፣ ልብሶች፣ በራስ የሚጠለቁ፣ ጫማዎች፣ ጋስኬቶች)፣ የተጠናከሩ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ እንደ መከላከያ ቆብ/ሄልሜት ያሉ አልባሳት እና ተያያዥ ዕቃዎች፡

የፍትጊያ መሣሪያዎች ከእነዚህ የተሠሩ ዕቃዎች (ለምሳሌ ዝርጎች፣ ጥቅሎች፣ ጥብጣቦች፣ ከፋዮች፣ ዲስኮች፣ ዋሽሮች፣ ፓዶች)፣ ያልተገጠሙ፣ ለፍሬን፣ ለፍሪሲዮን እና ለመሳሰሉት አገልግሎት የሚውሉ፣ መደባቸው አስቤስቶስ፣ ሌሎች የማዕድን ሰብስታንስ ወይም ሴሉሎስ የሆኑ፣ ከጨርቃ ጨርቅ ወይም ከሌሎች ማቴሪያሎች ጋር ተጣምረው የተሠሩ ቢሆንም ባይሆንም፡፡



17. የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ ዕንቁዎች እና የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች

7101.1000 እስከ 7117.9090 (ከ 7108.2000, 7115.1000, 7115.9010 በስተቀር)	የተፈጥሮ ወይም ካልቸርድ ዕንቁዎች፣ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮች፣ ከከበሩ ብረቶች እና የከበሩ ብረቶች ከለበሱ ብረቶች የተሠሩ ጌጣጌጥ እና ዕቃዎች፤ ቅንስናሽ ገንዘቦች መገበያያ ገንዘብ የሆነውን ሳይጨምር።

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም የከበሩ ብረቶች እና ጌጣጌጥ (ከወርቅ፣ ብር፣ ፕላቲኒየም፣ ዕንቁ፣ አልማዝ፣ ሩቢ ወዘተ.) ለመገበያያ ሳንቲም/ገንዘብ፣ ወይም ፕላቲኒየም በላቦራቶሪ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ወይም ለሽቦ ማልበሻ ወይም ግሪል ሲውል ካልሆነ በስተቀር።

በጌጣጌጥነት ሲሠሩ ብቻ የኤክሳይዝ ታክስ ይጣልባቸዋል።

18. የበዓል እና የካርኒቫል መጫወቻዎች እና የቁማር ማሽኖች

9504.2000 እስከ 9505.9000	የበዓል እና የካርኒቫል መጫወቻዎች እና መቀለጃዎች፣ የቁማር ማሽኖች እና የመጫወቻ ካርታዎች

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም ዓይነት የቪዲዮ ጌም ኮንሶሎች እና ማሽኖች፣ የመዝናኛ ዕቃዎች፣ የጠረጴዛ ወይም የቤት ውስጥ መጫወቻዎች፣ ፒንቴብልስ፣ ፑል እና ቢሊያርድ፣ ለካዚኖ ጨዋታዎች የሚያገለግሉ ልዩ ጠረጴዛዎች፣ አውቶማቲክ የቦውሊንግ መጫወቻ መሣሪያዎች እና የመጫወቻ ካርታዎች ጭምር።

የበዓል፣ በተጨማሪም የካርኒቫል ወይም ሌሎች የማስተናገጃ ዕቃዎች፣ የአስማት መጫወቻዎች እና መቀለጃዎችን እንዲሁም ለገና በዓል የሚሆኑ የማሸብረቂያ ዕቃዎችን ያጠቃልላል።

19. የትምባሆ ፒፓዎች እና የሲጋር ወይም የሲጋራ መያዣዎች

9614.0010	የትምባሆ/ሺሻ ፒፓዎች (ጋያን ጨምሮ)፤
9614.0090	የሲጋር ወይም የሲጋራ መያዣዎች እና የእነዚሁ ክፍሎች።

የዕቃው ዓይነት፡ ማናቸውም ዓይነት የተለመዱ የትምባሆ ፒፓዎች፣ የሲጋር እና የሲጋራ መያዣዎች እንዲሁም በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር።

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ደህንነት ጥበቃ ዳ/ደ
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.1